# ጉዞ
# ወደ እግዚአብሔር

(The Spiritual means)

## ክፍል ፩ እና ፪

አዘጋጅ:- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ተርጓሚ
ዲያቆን ግርማ ባቱ

ያለተርጓሚው ፈቃድ መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው
All rights reserved

## ምስጋና

በምንም የማይተካ ወርቃማ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ ረቂቁን በማረም፣ የሀሳብ፣ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ለተባበሩኝ በቅድሥት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚገኙና ሌሎችም ወንድሞቼ፣ ቤተሰቦቼ ሁሉ ልባዊና መንፈሳዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ተርጓሚው

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓት የጠበቀ
**፲፩ኛ እትም**

## ማስታወሻ

በቃለ እግዚአብሔር ላሳደጉኝ ለሆለታ ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን እና ለመምህሬ መሪጌታ ተክለብርሃን በጅተሃል ይሁንልኝ::

መጽሐፉን ለማግኘት
በስልክ ቁጥር 0911- 64 77 26
ይጠይቁን
ስለመጽሐፉ አስተያየት ለመስጠት
0911 88 42 58 ይጠቀሙ

## ማውጫ

መግቢያ

መቅድም

ምዕራፍ አንድ

1. ጸሎት ምንድ ነው ........ 9
2. እውነተኛ ጸሎትና አቀራረቡ ........ 16
3. መንፈሳዊ ሕይወትህን በጸሎት ለማሳደግ ........ 19

ምዕራፍ ሁለት

4. መጽሐፍ ቅዱስ ........ 24
5. መጽሐፍ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን ........ 31
6. አንተና መጽሐፍ ቅዱስ ........ 33
7. የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይልና ውጤቱ ........ 40
8. መጽሐፍ ቅዱስን ........ 47

ምዕራፍ ሦስት

9. ገድለ ቅዱሳንን ማንበብ ........ 49
10. አርአያነት ........ 52
11. እምነት ማጠንከር ........ 54
12. የትሕትናና የተሰበረ መንፈስ ........ 55
13. ጥበብና ማስተዋል ........ 57
14. የማያቋርጥ መንፈሳዊ እድገት ........ 57

ምዕራፍ አራት

15. ተመስጦ ........ 60
16. የተመስጦ ዓለሞች ........ 61
17. መጽሐፍ ቅዱስ ........ 61
18. ተፈጥሮ ........ 67

19. ክስተቶች .................... 71
20. ጸሎት .................... 73
21. የእግዚአብሔር ባሕርያት .................... 73

*ምዕራፍ አምስት*

22. የሕይወት ለውጥ በመንፈሳዊ ልምምድ .................... 75
23. የሕይወት ለውጥ እንዴት ይመጣል? .................... 75
24. እግዚአብሔር ቅዱሳኑን አለማምዷቸዋል .................... 77
25. ጠቃሚ ምክሮች .................... 78

*ምዕራፍ ስድስት*

26. ጾም .................... 85
27. ምን ዓይነት ጾም? .................... 88
28. ከምግብና መጠጥ መከልከል .................... 89
29. ከሥጋዊ ፍላጎት መታቀብ .................... 89
30. ጾምና ሥነ ምግባራት .................... 91

*ምዕራፍ ሰባት*

31. ምጽዋት /ሥጦታ .................... 93
32. እንዴት መስጠት አለብን .................... 96
33. ምጽዋት ብዛት ወይስ ጥራት .................... 99
34. አሥራት .................... 100
35. በኩራት .................... 102
36. ሥእለት .................... 103
37. ቁርባን/መባ .................... 104

*ምዕራፍ ስምንት*

38. ንስሐ .................... 105
39. ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝ .................... 105
40. ኃጢአትን ለንስሐ አባት/ለካህን መናዘዝ .................... 106
41. ኃጢአትን ለበደልከው ሰው መናዘዝ .................... 106
42. ኃጢአትን ለራስ መናዘዝ .................... 107
43. የንስሐ መንፈሳዊ ጥቅም .................... 110
44. የንስሐ ስነልቦናዊ ጥቅም .................... 110
45. የንስሐ ማሕበራዊ ጥቅም .................... 111
46. የንስሐ አካላዊ ጥቅም .................... 111
47. ጠቃሚ ምክሮች .................... 112

*ምዕራፍ ዘጠኝ*

48. ሥጋ ወደሙ .................... 114
49. ለሥጋ ወደሙ የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት .................... 116
50. የተሰበረ ልብ .................... 118
51. ንስሐ .................... 118
52. አካላዊ ንጽሕና .................... 119
53. የሕሊና ንጽሕና .................... 119

*ምዕራፍ አሥር*

54. አገልግሎት .................... 122
55. የአገልግሎት ዓይነቶች .................... 123
56. መንፈሳዊ .................... 123
57. ማህበራዊ .................... 123
58. የአገልግሎት መንፈሳዊ ፋይዳ .................... 125
59. የማይታይ አገልግሎት .................... 126
60. የአገልግሎት ሁኔታዎች .................... 127
61. ስኬታማ የአገልግሎት ሕይወት .................... 128
    ፍቅር .................... 128
    ጽናት .................... 129
    ቅንዐት .................... 130
62. ማጠቃለያ .................... 132

## መግቢያ

"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።" (ሮሜ 8÷14)

የሚከተሉትን በመንገዶቹ ላይ ሲመራቸው እነርሱም ወደእርሱ ይጓዛሉ። በዚህም ጉዞ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጠንካራ ሕብረት ይመሠርታሉ (2 ቆሮ 13÷14)

ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር የሚጓዙባቸውን መንገዶች መንፈሳዊ መንገዶች የጸጋ መንገዶች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚሠራው በእነዚህ የጸጋ መንገዶች ውስጥ ነውና።

በዚህ መጽሐፍ ከእነዚህ መንፈሳዊ መንገዶች በጥቂቶቹ ላይ እንድንነጋገር እወዳለሁ።

እነዚህ መንገዶችና ጉዞው ለክርስቲያን ሁሉ እጅግ ጠቃሚ ናቸው። የሰው ልጅ ምንም ያህል የጠነከረ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ቢገኝ ያለ እነዚህ የመንፈሳዊ ጉዞ መንገዶች በሕይወት ሊኖር አይችልም። እኚህ የማይነጥፉ የመንፈሳዊ ምግብ መገኛዎች ናቸው። የሚንቃቸው የሚያቃልላቸው ቢኖር እንኳን ራሱን ለአደጋ ያጋለጠ ሰው ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያስቀመጥኳቸው እያንዳንዳቸው መንገዶች በየራሳቸው አንድ አንድ መጽሐፍ ሊፃፍባቸው የሚችሉ ናቸው። ይሁን እንጂ ለአንባቢያን የተሻለ መንፈሳዊ ዕውቀት ለማስጨበጥ ይቻል ዘንድ በዚሁ መልኩ አጠር ባለ ሁኔታ መቅረቡን መርጫለሁ።

የምታነባቸውን ነገሮች ሁሉ ወደ ሕይወትህ አስገብተህ የመንፈሳዊ እድገት መልመጃዎች አድርገህ ተጠቀምባቸው።

እያንዳንዷን የጉዞ እርምጃህን ወደእርሱ በመምራት እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ
የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን
ፓትርያርክ

## መቅድም

በራሱ ምሉዕ ያልሆነና በነገሮች ሁሉ አጋዥ የሚሻ የሰው ልጅ አምላኩን የሚፈልግባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው። ለሰው የእስትንፋሱ ቀጣይ፣ የሕይወቱ ዋስትና፣ የባዶነቱ ሙላት፣ በጥቅሉ ሁለንተናው እግዚአብሔር ነው። ሰው ያለ እግዚአብሔር ምንም ነው። ለዚህም ነው ፈጣሪው «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ያለው። (ዮሐ 15÷5)

ሰውም ይህን መረዳት የሚችልበት ሕሊና በውስጡ ስላለ ከእግዚአብሔር የሚያርቁት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ሰላሙን ያጣል፣ ይጨነቃል። በሥጋዊ ሕይወት ብቻ ተወስኖ በዚህ ምድር የማይቀር መሆኑንም ስለሚያውቅ ከሞት ባሻገር ያለው ሕይወት ያሳስበዋል።

ይህ እንዳለ ሆኖ የሰው ልጅ በተለይም ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የሚያርቀው ነገር ምን እንደሆነ፣ ወደ እግዚአብሔር የሚመለስባቸው መንገዶችም ምን ምን እንደሆኑ የሚያውቅባቸው ሁኔታዎች ተመቻችተውለታል። ከእነዚህም መካከል ከመጻሕፍት የሚያገኛቸው መረጃዎች ጠቀሜታቸው የጎላ ነው።

ሁላችንም እንድን ዘንድ እንጂ ምንም እንዲጠፋበት የማይፈቅደው አምላካችን እግዚአብሔር ሰው ወደእርሱ እንዲጓዝባቸው ያዘጋጃቸው መንፈሳዊ መንገዶች እጅግ ብዙዎች ናቸው። ይሁን እንጂ ባለማወቅም ይሁን በግድ የለሽነት ሰዎች የተሰጣቸውን ይህን ጸጋ በአግባቡ ሲጠቀሙበት አይታይም።

ስለዚህ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የተጻፈው (The Spiritual Means) የተሠኘው መጽሐፍ ስለእነዚህ መንፈሳዊ መንገዶች እና ክርስቲያን ወደ አምላኩ ስለሚያደርገው መንፈሳዊ ጉዞ ጥቅል ግንዛቤ ያስጨብጣል። በእርግጥም የተሠጠንን ጸጋ እና እንዴት ልንጠቀምበት እንደምንችል ያስረዳል።

በመሆኑም ነው አንድ ወንድሜ እንዳነበው የጋበዘኝን ይህን መጽሐፍ ‹‹ጉዞ ወደ እግዚአብሔር› በሚል ርእስ ተርጉሜ፣ እኔ የተጠቀምኩበትን ያህል ወገኖቼ ለክርስቲያናዊ እድገታቸው ምንጭነት ይጠቀሙበት ዘንድ ለንባብ ያቀረብኩት።

መጽሐፉ፡- ከዚህ ቀደም በሁለት እትሞች ለንባብ የበቃ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን እነሆ አሁን ደግሞ በአንባቢያን አስተያየት መሠረት የበለጠ አመቺ በሆነ መልኩ ሁለቱን ክፍሎች በአንድ ጥራዝ በማዘጋጀት ታትሞ ለንባብ ቀርቧል።

ይህን መጽሐፍ ያነበበ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ውስጥ የሚታዩትን ድክመንቶች አሸንፎ ወደ ቀጣዩ የእድገት ደረጃ እንደሚሸጋገሩ እምነቴ ነው።

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳኑ በተጓዙበት መንገድ ተጉዘን የዘለዓለም ሕይወትን እናገኝ ዘንድ የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንልን!

ተርጓሚው

ዲያቆን ግርማ ባቱ

(0911-88 42 58)

2004 ዓ.ም



# ምዕራፍ ፩

## ጸሎት

**ጸሎት ምንድን ነው?**

ሰው ወደ እግዚአብሔር መቅረብና መነጋገር የሚችልበት የመጀመሪያ መንፈሳዊ መንገድ ጸሎት ነው::

ጸሎት እንዴት ወደእግዚአብሔር ያቀርባል?

በምን ዓይነት ሁኔታዎች መቅረብ አለበት?

ጸሎት የተባለ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ ሊሆን አይችልም::

ሰማይ ዝናምን እንዳይሠጥ የከለከለ ደግሞም እንዲዘንም ያደረገው በቅንነት በመንፈሳዊነት፣ በእምነት የቀረበ የኤልያስ ጸሎት ነበር:: «ኤልያስ እንደእኛ የሆነ ሰው ነበረ:: ዝናምም እንዳይዘንም አጥብቆ ጸለየ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነመም:: ሁለተኛም ጸለየ ሰማዩም ዝናምን ሰጠ:: ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች::» (ያዕ 5:17::) ጸሎት ኃይል ሊኖረው የሚችለው፣ ስኬታማ የሚሆነው በዚህ መልኩ በፈሪሃ እግዚአብሔርና በፈቃዱ ሲጠየቅ ብቻ ነው::«የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች::» (ያዕ 5:16)

ጸሎት እግዚአብሔርና ሰዎች የሚገናኙበት ድልድይ ነው:: ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ እንዳየው መሠላል (ዘፍ 28:12) ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ መወጣጫ ነው:: ጸሎት የቃላት ማነብነብ ብቻ ሳይሆን የውስጣዊው ሀሳብ ከእግዚአብሔር ጋር የሚመሠርተው ጽኑ ግንኙነት ነው::

ለጸሎት በተነሳህበት ጊዜ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆምክ አስብ «በፊቱ የቆምሁት የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር....» (1 ነገ 17:1) እንዳለው ኤልያስ በፊቱ እንደቆምክ የምታስብበት እርግጠኛ ሀሳብ ከሌለህ ጸሎትህ ጸሎት አይደለም::

ይህን የሚያስተውል ጸሎተኛ በእግዚአብሔር ፊት በቆመባት ሰዓት በሕሊናው የነበረው ሀሳብ ሁሉ እግዚአብሔርን ብቻ በማሠብ ስለሚተካ ሁሉን የተወና ሁለንተናው የእግዚአብሔር የሆነ ይሆናል።

ጸሎት ከውስጥ የሚመነጭ የልብ መቃተት ስለሆነ ቃላት ብቻ ሊገልጹት አቅም የላቸውም። በተመሰጠ ልብ፣ በመንፈሳዊ ሀሳብ፣ በተሰቀለ ሕሊና ወደ አምላካችን የምንነጠቅበትና ከፈጣሪያችን ጋር የምንነጋገርበት ስለሆነ ጸሎት ከቃላት በላይ ነው። በዝምታ እያለን በሕሊናችን ልንመሠጥ እንችላለን። ጸሎት እግዚአብሔርን የናፈቀ ልብ ሲቃ ነውና ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ይለካበታል። ሰውና እግዚአብሔርን ማገናኘት የሚችለው በዚህ ዓይነት ከልብ ፈንቅሎ የሚወጣ ጸሎት ስለሆነ ከዚህ መንፈሳዊ ሕብረት ውጪ ሆኖ የሚጮኹት ጩኸት ረብ የለሽ የቃላት ጋጋታ ነው።

እግዚአብሔር አምላክህን የምትወድ፣ የምታፈቅር ከሆነ ትጸልያለህ። ከጸለይክ ደግሞ ፍቅረ እግዚአብሔር በውስጥህ ያድጋል። እስቲ በዚሁ ፍቅር የተቀጣጠለና ልብ የሚነካውን የዳዊትን ጸሎት አስተውል። «አምላኬ አምላኬ ወደአንተ እገሠግሣለሁ። ነፍሴ አንተን ተጠማች....» (መዝ 62:1)።

«ዋላ ወደውሃ ምንጮች እንደሚናፍቅ አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች፣ ነፍሴ ወደሕያው አምላክ ተጠማች። መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ? (መዝ 41:1-2)። በእውነት ዝናምን እንደምትናፍቅ ደረቅ መሬት እግዚአብሔርን መናፈቅና መጠማት ይህ አይደለም?

ፍቅር የተለየው የቃላት ብቻ የሆነ ጸሎት ፍሬ ቢስ ስለሆነ ፍቅርን የማያውቁ ሰዎች ይጸልያሉ። ነገር ግን መጽናናት አይሰማቸውም። ደግሞም እግዚአብሔር የዚህ ዓይነት ሰዎችን «ይህ ሕዝብ በአፉ ወደእኔ ይቀርባል፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው።» ይላቸዋል። (ኢሳ 29:13)

ስለዚህ ወንድሜ ሆይ ጸሎትህ በፍቅር የተቀመመና የጣፈጠ ይሁን! ውሱን ፍጡር ሆነህ ሳለ ለማይወሰነው አምላክ ያለህን ናፍቆት የምትገልጽበት መንፈሳዊ መንገድህ ስለሆነ፣ ውሳጣዊት ነፍስህ ወደመገኛዋና





እረፍቷ የምትጠማው ጥማት ስለሆነ በተሰበረ መንፈስና በትሑት ልቡና ከጌታህ ጋር ተነጋገር።

እግዚአብሔር የሚቀበለው ጸሎት በንጹሕና በተሰበረ ልብ የሚቀርበውን ብቻ ነው። «የኃጥአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፣ የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው።» (ምሳ. 15:8)

በከንቱ ለሚደግሙ፣ ክፋት ለመላባቸው ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።«እጃችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዐይኔን ከእናንተ እሠውራለሁ፣ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም። እጆቻችሁ በደም ተሞልተዋልና» (ኢሳ 1:15)

ስለዚህ ኃጢአት የከበደው የተጨነቀ ሰው ምን ማድረግ አለበት? «መልሰኝ እኔም እመለሳለሁ» ይበል (ኤር 31:18) ጸሎት ኃጢአተኛን ወደንስሓ፣ ወደ አምላኩ ረድኤት እንዲገባ የሚረዳ በር ነው። ማር ይስሐቅ ስለዚህ ነገር ሲናገር «ከጸሎት በቀር ንስሓ መግቢያ በር አለ ብሎ የሚናገር ቢኖር እርሱ በሰይጣን የተታለለ ነው።» ይላል። ታዲያ ምን ትጠብቃለህ? የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ጸልይ፣ በንስሓ ወደ ክርስቶስ ቅረብ! እርሱ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ብሏልና። (ዮሐ. 15:5)።

ጸሎት እግዚአብሔር እንዲያነጻን እንዲቀድሰን ልባችንን የምንከፍትበት ቁልፍ ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ምሕረት ሽቶ በተሰቀለ ሕሊና፣ በተከፈተ ልብ ጌታውን የለመነውንና የሚፈልገውን ተቀብሎ በደስታ ወደቤቱ የተመለሰውን የቀራጩን ጸሎት ያስታውሰናል። (ሉቃ 18:13)።

አንተም ዛሬ መጸለይ ያለብህ ጸሎት ይህ ነው። «ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና።» (መዝ 50:2)። ይህን እያልክ ከልብህ የሚመነጭ እንባህን ብታፈስ «አዲስ ልብ እሰጥሃለሁ፣ አዲስም መንፈስ በውስጥህ አኖራለሁ የድንጋይንም ልብ ከሥጋህ አወጣለሁ» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል መስማት ትችላለህ።

ጸሎት የአንደበትን፣ የሀሳብን፣ የነፍስን መስዋዕት ማቅረቢያ ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ ሊያነጋግረው ስለማይችል ጸሎት ደግሞ የመታረቂያው መንገድ ነው:: ተሰሚነት ያለው መልካም ጸሎት ለመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲኖርህና ስለእርሱም በቂ ዕውቀት ለመጨበጥ እንድትችል መጣር አለብህ:: የማይጸልይ ሰው እግዚአብሔርን አላወቀውም:: የሚጸልይ ግን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የፈለገና፣ የቀደመው ክፉ ሥራው እየታወሰው በትሕትና የተሰበረ ልብ ያለው ነው:: ሰው ወደ ጤናማ ክርስቲያናዊ ሕይወት ምልክት ወደ ትሕትና ደረጃ መድረስ የሚችለው በጸሎት ነው:: የጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ፍሬ ትሕትና ነውና::

ጸሎት ክፉ ሀሳብ ከወስጣችን የሚወገድበት መንገድ ነው:: ከጨለማ ኃይላት ርቆ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት መግባት የሚቻለው በጸሎት ነው:: ጸሎት አጋንንት የሚፈሩትና የሚንቀጠቀጡበት መንፈሳዊ መሳሪያ ነው:: ከወጥመዱ ያመለጠ ጸሎተኛን ዲያብሎስ ይፈራዋል:: «ይህ ሰው በጸሎቱ ኃይል እያገኘ ነው::በመንፈሳዊ ሕይወቱ እየጠነከረ ነው:: ስለዚህ አሁን እኔን ሊዋጋኝ ይነሳል» እያለ ይርዳል ይንቀጠቀጣል:: ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት የሚፈጠረውንም ጥልቅ ግንኙነት እርሱ አስቀድሞ ያጣው ነውና ይቀናበታል ይመቀኘዋል:: ስለዚህ ዲያብሎስ በሚችለው አቅም ሁሉ ጸሎትህን ለማስተው ይጥራል:: ጊዜ እንደሌለህ፣ እንደተጣበብክ፣ እንደደከመህና እረፍት እንደሚያስፈልግህ እያሳሰበ ጸሎትህን ለማስቆም ይታገላል:: በጸሎትህ የምትታመን የምትተጋ ብትሆንበትም ከመንገድህ ለማሳት ሀሳብህን ለመበተን ሰይጣን የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም::

የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! ምንም ውጊያው ፈታኝ ቢሆንብህ በሙሉ ሀሳብህ በፍጹም ልብህ በጸሎትህ በርታ! ጽና! ሐዋርያው እንዳለው ዲያብሎስን ተቃወመው ከአንተም ይሸሻል:: (ያዕ 4:7) ራሱ ጠላትህ እንደተናገረው ጸሎት የማይቋቋመው፣ የማይችለው ኃይለኛ መሳሪያ ስለሆነ ሙሉ ትግሉ ሊያስቆምህ ነውና በፍጹም መንገድ አትስጠው፣ ተዋጋበት እንጂ ትጥቅህን አትፍታው:: የቱንም ያህል ቢፈታተንህ የመንፈሳዊ





ትግልህን ቁርጠኛነት አይቶ አፍሮ እንዲተውህ ጸልይ! ጸልይ! እግዚአብሔር በጸጋ አይለይህም!

በጸሎትህ ውስጥ የውሳጣዊት ነፍስህን ጉድለት እግዚአብሔር እንዲመላልህ ክፍት አድርግለት:: የምትለምነውም ያጣኸውን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን እንደዳዊት «አቤቱ ፊትህን እሻለሁ ልቤ አንተን አለ ፊትህን ከእኔ አትሠውር» እያልክ ይሁን! (መዝ 26:8-9) እግዚአብሔር ፍጹም ምሉዕ ካላደረጋት በቀር ነፍስህ ባዶ እንደምትሆን እርግጠኛ ሁን:: በዓለም ካለው ነገር ሁሉ ነፍስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ትሻዋለች:: የነፍስን ጥማት ያለፈጣሪዋ ማርካት የሚችል የለም:: (ዮሐ. 4:13)::

«ጌታዬ ሆይ የውስጤን የሚረዳልኝ እንዳንተ ያለ ማንንም አላገኘም፣ ከአንተ ጋር ስሆን ብቻ ደህንነት ስለሚሰማኝ ለአንተ ለአምላኬ ልቤን ከፍቼ ምሥጢሬን አዋይሃለሁ:: ቃልህን የምሰማ ነገር ግን የማላስተውል ደካማ ነኝና፣ ናፍቆቴን ቢገልጽልኝ እንባዬን በፊትህ አፈሥዋለሁ:: ልቤን ከሚያጸናውና በኃይሉ ከሚደግፈኝ ጋር እንደሆንኩ አውቃለሁና ከአንተ ጋር ... ስሆን ብቸኝነት አይሰማኝም:: ያለ አንተ ግን ባዶነቴ ያስጨንቀኛል:: ከእኔ ጋር የሆንክ... አማኑኤል አምላኬ ሆይ ነፍሴ ከዓለምና በዓለም ካሉት ከቁሳዊ ነገሮች ይልቅ የአንተን ሁሉን ቻይነት ትናፍቃለች:: ውስጤ የማትወሰን አንተን ተጠምቷል:: ከአንተም በቀር ይህን የሚረዳልኝ ከቶ የለም» እያልክ ጸልይ!

ይህ ዓይነት ጸሎት ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በደረጃው ከፍ ያለና በእግዚአብሔር ፍቅር ያደገ ነው:: ጸሎት እግዚአብሔር ለሰዎች ከሚያደርግላቸው ጥንቃቄ ከጠባቂነቱ፣ ከወዳጅነቱ፣ ከቸርነቱ የተነሳ ለሰዎች ከሚሠጣቸው ነገር ሁሉ በመነሳት ለአምላክ ምሥጋና የሚቀርብበት መንገድም ይሆናል:: ስለዚህ ለአንተም እንደ ሱራፌል «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያልክ ልዕልናውን፣ ክብሩን ገናንነቱን የምትናገርበትና የምትመሠክርበት መንገድ ነው:: (ኢሳ 6:3)::

እንደ ቅዱሳን አበው የአንተም ጸሎት ከእግዚአብሔር ባህርይ የተስማማ ይሁን፡፡

ታላቁ አባት ቅዱስ ባስልዮስ «ጸሎታችሁን በጥያቄ አትጀምሩ» እንዳለው የእግዚአብሔርን ዕጹብ ድንቅ ባህርያት ዐውቀህ በተመስጦ የምትጸልይና የምትጠቀም ሁን፡፡ ጸሎትን ቅዱሳን አባቶቻችን «ጣዕመ መንግሥተ ሰማያት» እንደሚሏት አንተም መጸለይን በእግዚአብሔር ሕብረት ደስ እንደምትሰኝበት ልዩ ነገር ቁጠረው፡፡

በእርግጥም ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ደስታ ነው፡፡ በአባቱ እቅፍ እንዳለና መታቀፉን ብቻ ከምንም በላይ እንደሚመርጥ፣ ሌላ ምንም ነገር እንደማይጠይቅ ሕጻን፣ ምንም የመጠይቅ ቃል ከአንደበትህ ባይወጣም፣ በሕሊናህ ምንም ሀሳብ ባይኖርም ስትጸልይ በእግዚአብሔር ቸርነት እቅፍ ውስጥ ነህና እንዲሁ ደስ ይበልህ!

በመንግሥተ ሰማያት ስለሚሆነው ሕይወታችን የምንጠይቀው ምንድን ነው? ምንም የምንጠይቀው የለም! ምክንያቱም በዚያ የምናጣው ነገር የለምና፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ዳዊት እንዳለው በጣዕሟ /በጸሎት/ ደስ ይለናል፡፡ «እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም» (መዝ 33:8)፡፡ በጸሎት በላይ በሰማያት የሚጠብቅህን አስደሳች ሕይወት ዛሬ በምድር እያጣጣምከው ነው፡፡ ስለዚህ ነው ጸሎት፣ ምሥጋና የመላእክት ምግብ ነው የተባለው፡፡ እንደዚሁ በምድር ላሉ ቅዱሳንም መንፈሳዊ ምግባቸው ነው፡፡ ለገዳማውያን አባቶች፣ ለባህታውንም ስንቃቸው ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሕብረት ከፍቅሩ ጋር ለመንፈስ ደስታቸው ይመገቡታል፡፡ ይህ ደግሞ ለምድራውያኑ መላእክት ለቅዱሳን ከምንም በላይ የሚመርጡት ጸጋቸው ነው፡፡ (መዝ. 72:28)

በትሕትናው ከእርሱ ጋር እንነጋገር ዘንድ ፈቅዶ ይህን መንፈሳዊ መንገድ ጸሎትን የሰጠን መልካሙ ጌታችን በእውነት ቡሩክ ቅዱስ ነው፡፡ እኛን ልጆቹን በኃጢአታችን ሳይጸየፈን ሊሰማን መቻሉ የትሕትናውን ጥልቀት ሊመጥን የሚችል እንደሌለ ያስረዳናል፡፡ በእውነት እኛ ማነን? ወደእርሱ ለመቅረብና በፊቱ ቆመን ለመነጋገር እኛ እንደትቢያ፣





እንደአመድ አይደለንምን? በደለኞች ሆነን ሳለ በፊቱ እንደሚቆሙት ስሙን እንደሚያመሠግኑት መላእክት ሆነን እንጸልያለን፡፡ ይህም ከእርሱ ጋር የመሆን እድል ነውና ለእኛ ቅድስና ነው፡፡ በእውነት ይህ የፈጣሪ ፍጥረታቱን ይህን በመሠለ ቅርብ ግንኙነት እንዲናገሩና እንዲሰማቸው የፈቀደበት የማይነገር ቸርነቱ ነው፡፡

ስለዚህ ለጸሎት «ጊዜ የለኝም» ማለት እጅግ አስጸያፊና ዘግናኝ ኃጢአት ነው፡፡ አንድ አገልጋይ (ባሪያ) «ጌታዬን የማነጋገሪያ ጊዜ የለኝም» ቢል እንዴት ያለ ድፍረት ይሆን? ፍጡሩስ ከፈጣሪው ጋር ለመነጋገር «ጊዜ የለኝም» ቢል ምን ይደንቅ! ዋጋ ቢስ ለሆኑ በርካታ ነገሮች ጊዜ ታገኛለህ፡፡ ምንም ረብ ለሌላቸው ንትርኮች ከበቂ በላይ ጊዜ አለህ፡፡ ምነው ታዲያ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርን እንደጊዜ ማባከን ቆጠርከው?

ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ከታላቅ ቤተሰብ ጋር ሕዝብን፣ አገርን የሚመራ የሚያስተዳድር የሚፈርድ፣ መሪ፣ መስፍን ፈራጅ ንጉሥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ዳዊትን የምንሰማው እንዲህ ሲል ነው፡፡ «ስለጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሠግንሃለሁ» (መዝ 118:164) «በማታና በጠዋት በቀትርም እናገራለሁ» (መዝ. 54:17)

ከዚህ የምትረዳው ችግሩ የጊዜ ሳይሆን የፍላጎት እንደሆነ ነው፡፡ የመጸለይ ፍላጎት ያለው ጊዜ ስለማግኘቱ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ጸሎት ሳትሠጥ የምትቀበልበት ልዩ በረከትህ እንደሆነ ማወቅ አለብህ! በመጸለይህ ለእግዚአብሔር ጊዜ እንደሠጠህ ታስብ ይሆን? እውነት ጸሎትህ ለእግዚአብሔር የሚያስፈልገው ነው? በጸሎትህ የምትከብር፣ ጥንካሬን እርዳታን፣ በረከትን የምታገኝ አንተው አይደለህምን? በጸሎትህ መንፈሳዊ ደስታን፣የችግርህን መፍትሔ የምታገኝ አንተው ነህ፡፡

ጸሎት የምትመካበት፣ ያለእርሱ መኖር የማትችል እንደሆንክ የምታረጋግጥበት ነውና ስለጸሎት የምታስበውን ሐሳብ ሁሉ ዛሬውኑ መቀየር ይኖርብሃል፡፡ ይህን አረጋግጥና ጸሎትን እንደመንፈሳዊ መንገድ ተቀብለህ እምነትህን ጣልበት፡፡ አንተ የምትጸልየው ጸሎት እንደመልካም መዓዛ በወርቁ ጽና ወደእግዚአብሔር ፊት ያርጋል፡፡ ደግሞ መላእክት እስከሚደነቁ

ድረስ አብዝቶ የሚጸልይ ምንም የማያርግለትም አለ። (ራዕ. 5:8) እነዚህን ነገሮች ለመለየት እና ተሰሚ ለመሆን ደግሞ የሚከተለውን አብረን እንመልከት!

## እውነተኛ ጸሎትና አቀራረቡ

ጸሎት ሁሉ ጸሎት አይደለም። ራሱን ሲያከብር የነበረው ፈሪሳዊ ጸሎቱ ተሰሚነት እንዳልነበረው ስናስብ ጸሎት ሁሉ ተቀባይነት እንደሌለው እንገነዘባለን። (ሉቃ 18:14)። እግዚአብሔር «ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፣ እጆቻችሁ በደም ተሞልተዋልና።» ያላቸውም ሰዎች ጸሎታቸው ከንቱ ነበር (ኢሳ. 1:15)። ግብዞችንም አይሰማቼውም (ማቴ. 6)፣ በጸሎት ርዝመት የሚያምኑም በከንቱ ይደክማሉ (ማቴ. 23:14)።

ስለዚህ እግዚአብሔር የሚቀበለው ጸሎት ምን ዓይነቱን ነው?

በዚህ ብዙ ሁኔታዎችን ማንሳት እንችላለን። ነገር ግን በመንፈስ ስለሚጸለይ ጸሎት ብቻ መነጋገራችን መልካም ነው። ምክንያቱም በመንፈሳዊው መንገድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ተቀራርቦ የሚነጋገርበት፣ ሀሳቡ ከአምላኩ ጋር አንድ የሚሆንበት ይህ ዓይነቱ ብቻ ስለሆነ ነው። የሰማያትን በር ከፍቶ ጌታችን ወዳለበት የሚያስገባን፣ መንፈሳችን የሚሻውን፣ ነፍሳችን የተጠማችውን አግኝተን ደስ የምንሰኝበት ከዚህ ከመንፈሳዊው ጸሎት በቀር ሌላ የለም። መዝሙረኛው ዳዊትም እንደነገረን መንፈስ የሚታደስበትና እፎይ የሚልበት በመንፈስ የሚጸለየው ጸሎት ነው። «እንዲህ በሕይወቴ ዘመን አመሠግንሃለሁ። በአንተም ስም እጆቼን አነሣለሁ። ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች።» (መዝ. 62:4)

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው እኛ ወደእርሱ እንደምንደርስበት፣እርሱም ወደእኛ እንደሚመጣበት መንፈሳዊ መንገድ አድርገን አምነን የምንጸልየው ጸሎት ነው። ልባችን በመንፈስ ቅዱስ የሚጎለምሰው፣ ሐሳባችን ከእግዚአብሔር ጋር ሊስማማ የሚችለው በእምነት በሚቀርብ መንፈሳዊ ጸሎት ነው። ቅዱሳን እንደሚነግሩን ጸሎት የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ነፍሳችን መቅረብ የሚያመለክት ነው።





እውነተኛ ጸሎት በመከራ የተፈተነና በፍቅር የተቀጣጠለ ነው። መንፈሳዊ ጸሎት እንደቅዱሳን አባቶች ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት የነደደ ነውና በባህርዩ መንፈሳዊ ሙቀት አለው።

ጸሎት ብልህነትን፣ መንፈሳዊ ዕውቀትን ጽናትን ይጠይቃል። ጸሎተኛ ሀሳቡ እንዳይከፋፈል መንገዱን እንዳይስት ጽኑ መሆን ያስፈልገዋል። ዕውቀቱም የሚጸልየውን እንዲያውቅ፣ (ማቴ. 20:20-22) በፈተናው ውስጥ ጸንቶ ማለፍ እንዲችልና በፍቅር እንዲመላለስ ይደግፈዋል። ሀሳቡን ሳይሰበስብ የሚጸልይ ሰው ማስተዋልና ፍቅር በእርሱ ውስጥ ስለሌሉ ከልቡ የሚመነጨው የተለያየ ዓለማዊ ሀሳብ ጭንቀትና ጥበት ነው።

ንጹሕ ጸሎት ያለው ለዓለም በመሞት ውስጥ ነው። ልብ ለዓለማዊ ነገሮች የሞተ ከሆነ በጸሎት ውስጥ ትርፍ ነገሮችን ማሰላሰል ማውጣት ማውረድ አይችልም። ይህ ከሆነ ደግሞ ጸሎቱ በአንድ ልብ ባልተከፋፈለ ሀሳብ የሚጸለይ ንጹሕ ይሆናል።

ንጹሕ የሆነ መንፈሳዊ ጸሎት ለእግዚአብሔር ክብር ከሚደረጉ የቅድስና ሥራዎች አንዱ ነው። እግዚአብሔርን ማፍቀርና በፍቅር መጸለይ ለአምላክነቱ የሚገባውን ክብር ለመስጠት እንቅፋት ሊሆን አይችልም። ሞገስና ክብሩ ገናንነቱ የሚዘነጋበትም አይደለም። በንጹሕ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የመነጋገርን እድል እንድታገኝ አቀራረብህ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር የሚጠነቀቅ መንፈሳዊ ፍርሃት ያለው ይሁን! በእርግጥ የአንተ ፍርሃት ባሪያ ለጌታው የሚንቀጠቀጠውን ዓይነት ሳይሆን የልጅና የአባት ዓይነት፣ ከቅጣት በላይ ለፍቅር የመጠንቀቅ ፍርሃት ነው። አባትህ እግዚአብሔር ምድራዊ አባት ሳይሆን መላእክት ሁሉ በፊቱ የሚቆሙ ሰማያዊ አባት ነው። (ኢሳ. 6:2)

ማር ይስሐቅ እንዳለው «ለመጸለይ ስትቆም በእሳት ፊት እንደቆምክ ያህል በጥንቃቄ ይሁን» የአባቶች አባት አብርሃምም «እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ እነሆ አንዴ ጀመርኩ» አለ (ዘፍ. 18:27)። ስለዚህ አንተም «ጌታ ሆይ በፊትህ ለመቆም እኔ ማን ነኝ? በአንተ ፊት

የሚቆሙ መላእክት፣ ሊቃነ መላእክት፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌል፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኃይለ ሰማያት ናቸው:: እንዴት ራሴን ከእነዚህ ቅዱሳን ጋር አስተካክላለሁ?» እያልክ በትሕትና ጸልይ!

በሥጋም በመንፈስም ለእግዚአብሔር ክብር የተገዛህ ሁን:: በመቆም በመንበርከክ በመስገድ ሥጋዊ ክብርህን ግለጽ:: በግድየለሽነት እንድትቆም፣ ድካም የሚሠማው የተጨነቀ ሰውነት እንዲኖርህ፣ ለመተኛት እንድትቸኩል በማድረግ ለሚፈታተንህ ሰይጣን እጅ አለመስጠትህ በሥጋህ እግዚአብሔርን ማክበርህ ነው:: ለረጅም ሰዓታት ከወዳጆቹ ጋር ቆሞ ያልደከመው ሰው ለጸሎት ሲቆም ቶሎ ይደክመዋል:: ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ እንዳለው «ጸሎት ከሕመም የመፈወሻው መንፈሳዊ መንገድ ነውና ላለመጸለይ ፀሽታን እንኳን ምክንያት አታድርግ» ማር ይስሐቅም «ንጹሕ ጸሎት መጸለይ በጀመርክበት ጊዜ ለሚመጣውም ነገር ዝግጁ ሆነህ ጠብቅ» እያለህ ነው:: ማለትም ከጸሎትህ ሊያደናቅፍህ ዲያብሎስ ለሚከፍትብህም ጦርነት የተዘጋጀህ ሁን::

ለእግዚአብሔር የምትሠጠውን መንፈሳዊ ክብር ሰውነትህም ሊያንጸባርቀው ይገባል:: በመንፈሳዊነት ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅርና ክብር የሚገለጠው በሥጋችን ነው:: የመንፈስ ቸልተኝነትና ግድ የለሽነት እንኳ ቢሆኑ በሥጋችን ሌሎች ነገሮችን በመስማት በጸሎት ጊዜ ሌላ ነገር በማየት በመሳሰሉት ሥጋዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ይታያሉ:: በተሠበረ ልብና በሚቃትት መንፈስ ሆነን ስንጸልይ ደግሞ መንፈሳዊ ክብርን ለእግዚአብሔር እየሠዋን ነው::

በተሰበረ መንፈስ ለሚጸልዩ እግዚአብሔር ቅርብ እንደሆነ አስታውስ:: ከፈጣሪያችን፣ ከንጉሠ ነገሥት፣ ከጌቶች ጌታ ጋር እንደምትነጋገር ሳትዘነጋ ከአፈር የተገኘህ መሆንህንም አስብ:: (ራዕ 19:16):: የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ያሳዘንክበትን ፍቅሩን ያቃለልክበትን፣ ቅንነቱን በክፋት በውለታ ቢስነት የመለስክበትን ኃጢአትህንም አትርሳ:: ስለዚህ በተሰበረ ልብና በትሑት መንፈስ ቆመህ እንደ ዳንኤል ይህን ጸልይ! «ጌታ ሆይ ጽድቅ ለአንተ ነው::....ለእኛ ግን የፊት እፍረት ነው.......ጌታ ሆይ በአንተ ላይ ኃጢአት ስለሠራን.....በአንተም ላይ





አምጸናል......» (ዳን. 9:7-9) ለእኔ ምንም የተገባኝ አይደለም:: ነገር ግን እንደኃጢአቴ እንደክፋቴ ሳይሆን ትዕግስትህና ሁሉን ቻይነትህ ያፅናኑኛል:: አንተ የሚቹን ሞት ሳይሆን ተመልሶ በሕይወት መኖሩን የምትፈቅድ ነህና የምሕረትህ ብዛት በወደቅሁት በእኔ ላይ ተገልጿል:: (ሕዝ. 18:23.32)::

## በእምነት ጸልይ

እግዚአብሔር የለመንከውን እንደሚሰማህ፣ ይወድህልና መልስ እንደሚሠጥህ፣ መልካሙን ሁሉ ለአንተ እንደሚመርጥልህ በፍጹም ልብህ እመን (ማቴ. 21:22) ይህ እምነት ባይኖርህ እንኳን «ጌታ ሆይ አለማመኔን እርዳው» እያልክ ጸልይ (ማር. 9:24):: ደግሞም እንደሐዋርያት እምነት እንዲጨመርልህ ለምን (ሉቃ. 17:5) ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል የሚለውን ድንቅ ቃልኪዳንም አትርሳ (ማር. 9:23)::

እምነት ለጸሎተኛ ጽናትን የሚሠጥ ታላቅ ኃይል ነው:: ጸሎትም እምነትን ያሳድጋል:: አንድ ነገር እንዲሆንልህ ጠይቀህ፡ ለምላሹ ጌታን ጠ ብቅ እንጂ ያን ቶሎ ለማግኘት አትቸኩል:: ምንም እግዚአብሔር የሚዘገይ ቢመስልህ፣ የረሳህ ያህል ቢሰማህ፣ እርሱ ግን የራሱ ጊዜ አለውና ጥያቄህ እንደሚመለስ እርግጠኛ ሁን:: እስቲ ነቢዩ ዳዊትን ስማው! «እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ! በርታ ልብህ ይጽና! እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ» (መዝ 26:14)::

## ጸሎትህ ጥልቅና በማስተዋል ይሁን!

ለመጸለይ የምትጠቀመው ማንኛውም ቃልና እንቅስቃሴ በማወቅና በማስተዋል መሆን አለበት:: ከልብ ፈንቅሎ የሚወጣ ትክክለኛ መንፈሳዊ ፍላጎትን የሚገልጽ እውነት እንዲኖርበትም ያስፈልጋል:: የጸሎት ጥልቅነት የጋለ መንፈሳዊ ስሜትን ይፈጥራል::

## መንፈሳዊ ሕይወትህን በጸሎት ለማሳደግ፡

1. ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር የምትጠቀምበትን ሰዓት ለማራዘም ራስህን አለማምድ!

ቅዱስ ዳዊት ይህን ልዩ ሰዓት ለመግለጽ የተጠቀመውን ውብ ቃል ልብ በል! «አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ፣ ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።» (መዝ 118:97)። አሁን ራስህን ጠይቅ!! ምን ያህል ጊዜ በጸሎት ታሳልፋለህ? ያለጥርጥር መናገር የምችለው ለማይጠቅምህ ወሬ ብዙውን ጊዜህን እንደምታባክን ነው። ወንድሜ ሆይ በእርግጥ ጊዜህ በጣም እየባከነ ነው። ማድረግ የነበረብህ ረጅሙን ጊዜ ከአምላክህ ጋር ለመነጋገሪያ ነበር። ይህ የተለየና የተቀደሰ ሰዓት ደግሞ ከዕለት ዕቅድህ የመጨረሻውና ዝቅተኛው እንዳይሆን፣ ከፍተኛውን እና የመጀመሪያውን ደረጃ እንዲይዝ በየዕለቱ ልምምድህን መቀጠል አለብህ።

2. በማለዳ ለመነሳትና ዕለቱን በጸሎት ለመጀመር ራስህን አለማምድ

ይህ ሰዓት ልባችን ንጹሕ የሚሆንበት፣ በሐሳብ የማንጨናነቅበት፣ በኃላፊነት፣ በሥራ ብዛት የማንባክንበት ሰዓት ነው። ቤተሰቦችህ ምናልባት ተኝተው ያሉበትና ምንም ድምፅ የማይሰማበት ጊዜ ስለሆነ ያለምንም እንቅፋት ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ መሆን የምትችልበት ሰዓት ነው። ይህ ልምምድ ቀኑን ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ወይም መጀመሪያ የምታገኘውና የምትሰማው ድምጽ የእግዚአብሔር እንዲሆን የምታደርግበት፣ የተሟላ በረከት የምታገኝበት፣ ልዩ መንፈሳዊ እድገት ነው።

3. በየሰዓቱ መጸለይን ልመድ

ምንም እንኳ ቀኑን ሙሉ በጸሎት ለመሸፈን ባትችልና እድሉም ባይኖርህ ቢያንስ የዕለቱን ዋና ዋና የጸሎት ሰዓታት ለመጠቀም መለማመድ ትችላለህ። አሁን ካለህበት የኑሮ ትግልና ጭንቀት ለመገላገል በመንፈስህ ወደእግዚአብሔር ለምትነጠቅበት ለዚህ ጸሎትህ የምታውለው ትንሽ ጊዜ ኑሮህን እንደቀማህ ላለማሠብ እርግጠኛ ሁን። የጸሎት መጽሐፍ ተጠቅመህ መጸለይ በማትችልባቸው ሰዓታትም በቃልህ የምትጸልያቸው፣ የምታስታውሳቸው ጸሎቶች ይኑሩህ የእግዚአብሔርን ቃል በቀን በሌሊት አስበው.... ከአፍህ አይለይ (ኢያ. 1:8)





4. ባለህበት ሥፍራ ሁሉ መጸለይን ልመድ

በጊዜው ሁሉ የአምላክህን ቃል እያስታወስክ ወደቅድስት ቤተክርስቲያን መሄድ ባልቻልክበት ጊዜ በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች በምትገኝበት ቦታ ሁሉ ሳትታክት ጸልይ (ሉቃ. 18:1)። ከፈጣሪህ ጋር የምትወያይበት ዋጋን የሚያስጥ ልዩ ህብትህ ነውና ጸሎትህን አታቋርጥ (1 ተሰ 5:17)። እንደፈሪሳውያን ለመታየት አይሁን እንጂ በከንቱ መድገም ያልሆነ ከልብ የሚመነጭ ጸሎትህን በመንገድህም ጸልየው። ከሰዎች ጋር በምትሆንበት ጊዜ በተለይ የሚያደናቅፍህ ርእስ ጉዳይ አንስተው ሲያወሩ፣ የማይመለከትህ ሆኖ ስታገኘው፣ ወደቤትህ ስትገባና ስትወጣ፣ ሥራህን ስትጀምርና ስትጨርስ በማንኛውም ሁኔታ መጸለይን ቅዱስ ልምድህ አድርገው።

5. ለሌሎች መጸለይን ልመድ

ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ጸልይ። ለዘመዶችህ፣ ለወዳጆችህ፣ ለጓደኞችህ፣ ለአንዲቱ አርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ በተለይ ስለ አገልግሎት ጸልይ። የታመሙትን የሞቱትን፣ ንሥሐ መግባት የሚፈልጉትን አትርሳቸው። ስለዓለምና መንግሥታት ሰላምን ጠይቅ። በዚህ መንገድ ቀስ በቀስ ወደሚቀጥለው የእድገት ደረጃ ማለትም ለጠላቶችህ፣ ለሚቃወሙህ ጭምር ወደመጸለይ ትሯመዳለህ። (ማቴ. 5:44)።

6. በመከራ ውስጥ ሳለህ መጸለይን ልመድ

በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ እግዚአብሔርን ማንሣትና በችግር ውስጥ ስሙን መጥራት ተማር። በራስህ ማስተዋል ተደግፈህ ችግሮችን ለመጋፈጥ አትሞክር። ከጓደኞችህ ከወዳጆችህ አጠቃላይ ከሰው መፍትሔን አትጠብቅ። ምንም ምንም ቢሆን ያለእግዚአብሔር መሥራት እንደማትችል የሚያረጋግጥ ሀሳብ በውስጥህ ይኑር! ለችግሮችህ መፍትሔ ያለው ወደእግዚአብሔር በመጸለይ ሡስጥ ብቻ ነው። እግዚአብሔር የማይፈታው ቋጠሮ የለም። ምንም እንኳን ለአንተ ችግሩ ቀጣይ ቢመስልህ ወይም በመከራ ውስጥ ብትሆን አስፈላጊውን የልብ ጽናት እርሱ ይሠጥሀል።

የውስጥ ሰላም ካለህ ችግር ቢኖርም እንኳ እንደሌለ ቆጥረህ ላለመረበሽ ምክንያት ይሆንሃል። ይህ ሁሉ የንጹሕ ጸሎት ውጤት ነው።

### 7. በግል ጸሎት ራስህን አለማምድ

በቤተክርስቲያን ውስጥ በማሕበር ከሚደረገው ጸሎት በተጨማሪ አንተም በልብህ ያለውን አውጥተህ ለእግዚአብሔር በግልጽ ልትነግረው የምትችልበት ጸሎት እንዲኖርህ ራስህን አለማምድ። ለምሳሌ «እስከ መስቀል ሞት የወደድከኝ ጌታዬ ሆይ እኔ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ። ነገር ግን እንቅፋት የሚሆኑብኝን ሌሎች ዓለማዊ ነገሮችንም እንድወድ የሚገፉኝ ስሜት እንዳለ አስባለሁ። በራሴ ላስወግዳቸው ባሰብኩ ቁጥር የማውቀው ደካማነቴን ነው። ይህ ዓለምን መውደድ ደግሞ ከአንተ ጋር መጣላት መሆኑን ሳስብ እፈራለሁ። (ያዕ.4:4)፣ ስለዚህ አምላኬ ክርስቶስ ሆይ በፍጹም ልቤ አንተን ብቻ እንዳፈቅር እርዳኝ፣ አንተንም ከሚቃረነው ዓለማዊና ሥጋዊ ፍቅር ሁሉ በኃይልህ ታደገኝ» እያልክ መጸለይ ትችላለህ።

ስትጸልይም፣ የግድ የተመረጡ ቃላትን ያማሩና የተሳኩ ዐረፍተ ነገሮችን መጠቀም እንዳለብህ እያሰብክ አትጨነቅ። የሚያስፈልገው ከልብ ፈንቅሎ የሚወጣና ማስመሠል (artificial) ያልሆነ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚጠየቅበት ጸሎት ስለሆነ (ማቴ. 6:10) በትክክል ማንነትህን የሚገልጽ ሀሳብህ የሆነውን ብቻ ጸልይ። ጸሎትህ የልማድ ብቻ እንዳይሆንብህም ተጠንቀቅ።

### 8. በማስተዋል መጸለይን ልመድ

ስለጸሎት ምንነት ጠልቀህ በማሰብ ምን እነደምትጸልይ ዕወቅ። የጌታችን ሐዋርያት «እንዴትና ምን እንደምንጸልይ አስተምረን» (ሉቃ. 11:2) ብለው እንደለመኑ አንተም በጸሎትህ ስለራሱ ስለጸሎት ምንነትና እንዴት መጸለይ እንዳለብህ እጅግ ብዙ ነገር ትማራለህ።

ፍጹም ንጹሕ ጸሎት መጸለይ የምትችልበት ደረጃ ላይ ባትደርስ እንኳን ይህን ምክንያት አድርገህ መጸለይን አታቋርጥ።

ጸሎት እንደማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ ሁሉ ደረጃ በደረጃ የሚያድግና ከፍጹምነት የሚደርስ ሕይወት ነው። ይህን በተመለከተ ማር





ይስሐቅ የሚነግርህ ይህን ነው። «መጸለይ ሳትጀምር ፍጹም የሆነ የጸሎት ደረጃን የምትጠብቅ ከሆነ፣ ጭራሽ ሳትጸልይ ትቀራለህ። ምክንያቱም ከንጽሕናና ከፍጹምነት ደረጃ ላይ መድረስ የሚቻለው ባለማቋረጥ በመጸለይና በመጽናት ብቻ ነው።»

ከውስጥህ በቃ! በቃ ! የሚል ጩኸት ቢሠማህ እንኳን ጸሎትህን ለማቋረጥ አትስማማ። ያ! ድምጽ ከእግዚአብሔር ሊለይህ፣ መንገድህን ሊዘጋው የተዘጋጀ የዲያብሎስ ሽንገላ ነውና በእምነት ጸንተህ ተቃወመው (1 ጴጥ. 5:8-9)

### ወንድሜ ሆይ አሁንስ እንዴት ነህ?

ጸሎትን ለመተውና ያለእርሱ ለመኖር እንደማትችል ይሰማሀልን? ከሆነ ይህ ትክክለኛ የመንፈሳዊ እድገት ምልክት ነው። ምክንያቱም ጸሎት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር የምታደርገው ግንኙነትና ውይይት ነው። ስለዚህ የእያንዳንዷን የጸሎት ቃል ጣዕሟን ማጣጣም ስለቻልክ ማቋረጥ አያሠኝህም። አባቶቻችን ቅዱሳንም በአፋቸው ውስጥ ካለው የጸሎት ጣዕም የተነሳ ጸሎትን አቋርጠው ሌላ ነገር ለመናገር አይፈቅዱም ነበር። አንተም በዚህ ሥጋዊ ዐይን በማያየው ልዩ የጸጋ መንገድህ ወደፈጣሪህ ገሥግሥና ችግርህን፣ ደስታህን፣ ሁለንተናህን አዋየው። ጉድለትህን እንዲሞላ ባለማቋረጥ ጠይቀው፣ የምትሻውንም እንደፈቃዱ የጠየቅከውን ሁሉ ይዘህ ትገኛለህ።

እንድንጸልይ የፈቀደልን አምላክ የተመሰገነ ይሁን!

## ምዕራፍ ፪

### መጽሐፍ ቅዱስ

በባህርዩ ንጹሕ ቅዱስ ሆኖ ሳለ ከሰዎች ጋር ለመወያየት ራሱን ትሑት ያደረገው አምላካችን ቡሩክ ነው:: ሰው ሁሉ ለመንገዱ ብርሃን ይሆንለት ዘንድ ነፍስም ሕይወት አግኝታ እንድትኖርበት ነቢያቱን ያናገረ፣ የተናገሩትንም እንዲጽፉት ያዘዘ ፈጣሪያችን ቅዱስ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ «የመጽሐፎች መጽሐፍ» እውነትም «ታላቅ መጽሐፍ» ነው:: መጽሐፍ ሲባልም የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃሉ ነው:: በእርሱ አንተን ይናገርበታል:: መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸና በቅዱሳን ነቢያት እና ሐዋርያት አንደበት የተነገረ እውነት ነው:: «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ::» (2ጴጥ. 1:21) ጥቅሙም እንድትማርበት፣ ለእግዚአብሔር የቀና ልብ እንዲኖርህ፣ በአጠቃላይ የፈጣሪህን ፈቃድ ተከታይ እንድትሆን ለማድረግ ነው:: (2 ጢሞ 3:16)::

መጽሐፍ ቅዱስ ለአንተ ከእግዚአብሔር የተላለፈልህ መልእክት ነው::

በዚህ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር በመጣለት መልእክት ደስ የማይለው ማነው? በአንድ ወቅት ታላቁ ቅዱስ አባት አባ እንጦንስ ከንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የተላከ ደብዳቤ ደረሠው:: ደቀ መዛሙርቱም አባታቸው የንጉሥ ደብዳቤ ስለደረሠው እጅግ በጣም ተደሠቱ:: እርሱ ግን ምንም የተለየ ግምት ሳይሰጠው ወደጎን አለው:: አሁንም ተማሪዎቹ ከመደነቅ ብዛት ለማንበብ በጣም ጓጉ:: አባ እንጦንስ ግን «ልጆቼ ከሰው ለመጣ ደብዳቤ እንዴት እንደዚህ ደስ ይላችኋል? እነሆ የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር የብዙ ብዙ ደብዳቤዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልኮልናል:: ለምን በዚህ መልእክት እንደዚህ አትደሰቱም? ለማንበብስ እንዴት አያጓጓችሁም? ብሎ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ካስተማራቸው በኋላ ደብዳቤውን አነበበ:: ለንጉሡም የሚያስፈልገውን የበረከት መልስ ሰጠው::





አንተስ ከምትወደውና ከምትናፍቀው ሰው ደብዳቤ ቢደርስህ እጅግ ተደስተህ በየሰዓቱ ታነበው የለም? ከሆነ ደግሞ ከእግዚአብሔር ለመጣልህስ ይህን ያህልና የባለጠ መደሰትና መጓጓት በየሰዓቱ ማንበብ አይገባህም ነበር? ይህ ከእግዚአብሔር ወደአንተ የተላከው መልእክት በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ፣ ይመራቸው በነበሩ ነቢያት የተነገረ እና ቃሉ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ መልእክት ነው:: ይህን ደግሞ በውስጡ ባለው መንፈስና ሕይወት መረዳት ትችላለህ:: ጌታችንም «እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፣ ሕይወትም ነው::» ሲል ተናግሯል (ዮሐ. 6:፣63)

መጽሐፍ ቅዱስ ተመግበኸው ሕይወት እንድታገኝበት ከእግዚአብሔር የተሰጠህ መንፈሳዊ ምግብ ነው:: ጌታችን ዲያብሎስ ሊፈትነው በቀረበ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ (ዘጸ. 8:3) ጠቅሶ እንደተናገረው ሰው ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃል ጭምር እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም:: (ማቴ 4:4) ለሥጋዊ ሕይወትህ የሚሆን ሥጋዊ ምግብ አለህ:: ነገር ግን አንተ ሥጋ ብቻ አይደለህም:: በውስጥህ የማይሞት የማይበሰብስ መንፈስ አለ:: ስለዚህ መንፈሳዊውንም ምግብ መጽሐፍ ቅዱስን ተመግበህ ሕይወት ማግኘት አለብህ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው....» (ዮሐ. 5:24)::

ወንድሜ ሆይ! መኖር የምትችለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው የሕይወት ቃል ጭምር እንጂ በእንጀራ ብቻ እንዳልሆነ እርግጠኛ ሁን:: «ዛሬ የዕለት ምግባችንን ስጠን» እያልክ ስትጸልይም የሕይወት ምግብህንም የሚያጠቃልል እንደሆነና ስለሥጋህ ብቻ እንደማትጠይቅ ልብ በል:: የእግዚአብሔር ሰው ሆይ የአንተ ደስታ መሆን ያለበት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው:: (መዝ 1:2) ሌት ተቀንም አስበው:: ደስታህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሕግ የሚያስጨንቅ ግዴታ ሳይሆን የሕይወት ምንጭ መሆኑን መረዳትህን ነው::

መጽሐፍ ቅዱስና የእግዚአብሔር ሰው ያላቸው ግንኙነት ቋሚና የማያቋርጥ ነው፣ ሕጉን በቀንም በሌሊት ያስባል:: ይህን ለተወሰኑ ሰዎች

ብቻ የሚሠራ አነጋገር አድርገህ አትውሰደው። የአንተም የሌላውም የሁላችንም ነው።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲመራ ለተጠራው፣ ለሙሴ ተከታይ፣ ለነዌ ልጅ ኢያሱ በዚያ ሁሉ ሕዝብ አመራር ኃላፊነት ውስጥ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር የነገረውን ቃል አስተውል። «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌትም አስበው። የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል፣ ይከናወንልሃል (ኢያ 1:8)። እንግዲህ ያን ሁሉ ሕዝብ የመምራት ኃላፊነት ለነበረበት ሰው እግዚአብሔር «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ» ሲለው አንተ ምን ታስባለህ? ይህንንም ለኢያሱ ብቻ ሳይሆን ለእኔም ለአንተም እንደሆነ እመን። ለዚህም ነው መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት የእግዚአብሔር ሰው ደስታ በእግዚአብሔር ሕግ፣ እርሱንም ሌት ተቀን በማሰብ እንደሆነ በመዝሙሩ መጀመሪያ ላይ የተናገረው።

እርሱ ራሱ ንጉሥ ዳዊትም መሪና ንጉሥ፣ የኃላፊነት ሰው ሆኖ ሳለ «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው» አለ። (መዝ 118:105) እንዲሁም፣ የእግዚአብሔር ቃል ከማር ከሦከር ይልቅ ለእኔ ይጥመኛል አለ።

ንጉሥ ዳዊት እንዴት ሕጉን በቀንና በሌሊት የማሰቢያ ጊዜ አገኘ? አንተስ እንዴት አጣህ? አባቶቻችን ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስን ከልባቸው በፍቅር ይማሩት ስለነበረ በሕይወታቸው ሙሉ መጽሐፉ የተገለጠ ነበር። አንተም የእግዚአብሔርን ቃል እያወቅህ እየተማርክ በሄድክ ቁጥር በሌትም በቀንም እያሰብከው ትመጣለህ። መጽሐፍ ቅዱስን አንተ ተማረው፣ እርሱም ይጠብቅሃል። በቤትህ፣ በሥራህ፣ በመንገድህ፣ በሰዎች መካከል ሆነህ አስበው፣ ወዳጅህ አድርገው። አንተ የቃሉ ወዳጅ ስትሆን የቃሉ ባለቤት እግዚአብሔር ደግሞ የልብ ወዳጅህ ይሆናል።

ቃሉን ደጋግመህ አጥናው፣ ሁሌም አትርሳው። ይህ ከበጎ ምግባር ሁሉ የመጀመሪያው ነውና።





ይህን በተመለከተ አምላክህ የሚናገርህ አለው። «ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል» ማቴ 7: 24። በጸሎተ ቅዳሴያችንም ላይ ካህኑ «ቅዱስ የሆነ የወንጌልህን ቃል እንድንሰማና፣ እንደሰማንም እንድንሠራ በቅዱሳን ጸሎት የበቃን የተዘጋጀን አድርገን» ይላል። «የበቃን» ሲል ጥልቅ የሆነ ትርጉም አለው። ለሕጉ ለትእዛዛቱ ያልታመንን እኔና አንተ ቅዱስ የሆነውን የወንጌሉን ቃል ለመስማት እኛ ማነን? «የበቃን» ያደረገን፣ የሕይወትን መጽሐፍ ወደእርሱ የምንጓዝበት መንገድ አድርጎ የሠጠን አምላካችን ነውና፣ እርሱን «የበቃን» አድርገን ብለን፣ እንደፈቃዱ በኖሩት፣ ቃሉን በተመገቡት በቅዱሳኑ ስም እንለምነዋለን።

የእግዚአብሔር ሰው ክርስቲያን ሆይ! እጅግ ብዙ የተጠቀምክበትና፣ ብዙ ነገር የምታስታውስበት መጽሐፍ ቅዱስ በእጅህ ላይ ሊታይ ያስፈልጋል። ለእይታ ለጌጥ ብቻ ያልሆኑ፣ ብዙ የተነበቡ፣ የዘወትር አማካሪ የሆኑ መጻሕፍት የክርስቲያን መለያዎች ናቸው።

እባክህ ይህን የሕይወት መጽሐፍ ተጠቀምበት።

አንብበው፣ አስበው። ወደጥልቁ ዕውቀት ግባና ከነፍስህ ጋር አዋህደው። ቃል በቃል በሚሠጥህ ትርጉም ብቻ ተመስርተህ ባገኘኸው ነገር ደስ አይበልህ። ጠልቀህ ስታስብ አንዱን ቃል የውቅያኖስ ያህል እጅግ ሠፊ ሆኖ ታገኘዋለህ። ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረው ወሰን የሌለው ድንቅ ምሥጢር የሚገኝበት የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። «የሥራን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ፣ ትእዛዝህ ግን እጅግ ሠፊ ነው።» (መዝ 118:96)

ዳዊት ይህን የተናገረበት ጊዜ ገና ዘጠኝ የሚያህሉ መጻሕፍት የነበሩበት ነው። ዛሬ አንተ ሙሉ የሆነ፣ ነቢያትን፣ አዲስ ኪዳንን ያጠቃለለ መጽሐፍ ቅዱስ ከነትውፊቱ አለህ። እያንዳንዱ ቃል የእግዚአብሔር ነውና ጥልቅነቱን ሥፋቱን አስብና፣ የተሰጠህን ሀብት የመጽሐፉን ምንነት በደንብ ተረዳ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሐሳብ ምንጭ ብቻ ሳይሆን መጽናኛም ነው:: ዛሬ ላለህበት የትኛውም የሥነ አእምሮ፥ የሥነ ልቡና ሁከት እና ረሃብ መጽሐፍ ቅዱስ እንድትጽናናበት፣ እንድትረካበት የሚያደርጉህ ቃላት ይገኙበታል:: ያዘነ፣ የተከዘ ሰው ቢኖር የሚፅናናበትና ደስ እንዲለው የሚያደርግ፣ የተረበሸም ሰው ሰላሙን የሚመልስለት ቃል የሚገኝበት መጽሐፍ ነው:: ለአንተም በመከራህ ሰዓት መፍትሔን፣ ሰላም ባጣህበት ጊዜ የውስጥ ሰላምን ተስፋ ብትቆጥ የሚያበራ የተስፋ ብስራት ቃልን የምታገኝበት ድንቅ ሥጦታህ ነው:: ቃላቱ ሁሉ የሚለውጡህና ውጤታማ ናቸው:: እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ባነበብክ ቁጥር «አምላኬ ሆይ ይህን ስለኔ እንደተናገርክ ጥርጥር የለኝም» በለው:: በግል ለአንተ ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት አድርገህ ተቀበለው::

እግዚአብሔር ስለአንተ ነቢያቱን አናገረ:: መልእክታትም ለቆሮንቶስና ለሮሜ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለአንተም ተላኩ:: ቅዱስ አባት እንጦንስ የንጉሥ ቆንጠንጢኖስ ደብዳቤ ሲደርሰው ደቀ መዛሙርቱ ምን ያህል ተደስተው እንደነበረ እና እንዴት አስተምሮ እንዳሳመናቸው አስታውስ:: የነገሥታት ንጉሥ፣ የእግዚአብሔር መልእክት እነሆ ለአንተ ደርሶሃል:: ስለምን በእርሱ ደስ አይልህም?

የመጽሐፍ ቅዱሳችን ቃል መጽናኛ ብቻ ሳይሆን የጦር መሳሪያም ነው:: ለእያንዳንዱ ኃጢአት በፊቱ የሚቀመጥ «አታድርግ» የሚል ሕግ አለ:: በዚህ ምክንያት ከሕገ እግዚአብሔር ካገኘኸው ቃል የተነሳ ኃጢአትን ደካማ ሆኖ ታገኘዋለህ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነና በኃይል እንደሚሠራ ታውቃለህ? «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሠይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ 4:12)

ሰይጣን ፈታኝ ሆኖ በቀረበበት በዚያ ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ሊቋቋመው አልቻለም፤ ያገኘለትም ምላሽ አልነበረም:: (ማቴ.4:1-11)





የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተህ የማትሠራበት ከሆነ፤ በመጨረሻው ቀን በአንተ ላይ ይፈርዳል:: ቃሉ ለዕውቀት ብቻ ሳይሆን ለሕይወት ነው:: በሄድክበት የሚሄድ፣ ዘወትር በጆሮችህ የሚያቃጭል እና በተግባር ካላዋልከው ከባድ የሕሊና ወቀሳን የሚያስከትል ነው:: በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በአንደበትህ፣ በንግግርህ፣ ሁሉ ካለና በተግባርህ የሚገለጥ ከሆነ ለመንፈሳዊነትህና ለሃይማኖትህ ታማኝ እንደሆንክ ይመሰክራል:: ዓለማዊ ነገሮችን ብቻ የሚያወሩ ብዙ ሰዎች አሉ:: እንደዚሁ የእግዚአብሔር ቃል ከአንደበቱ የማይጠፋ፣ ሁሌም የሚጠቀመው፣ መጽሐፉ ራሱ እሱን ተቆጣጥሮት የአነጋገር ዘዬውን የቀየረውም ሰው ታያለህ:: ይህ ሰው የሕጉ መጽሐፍ ከአፉ አልተለየም (ኢያ 1:8):: አበው «ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀደዳል» እንዲሉ የሚሰማው ሁሉ ማንነቱን ያውቀዋል:: «አነጋገርህ ይገልጥሃል» (ማቴ. 26:73)::

ለልጆችህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እየነገርክ ባዩት፣ በሰሙት ነገር ላይ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እንዲጠቀሙ አስተምራቸው:: በመጽሐፍ ላይ፣ በዛፎች ላይ በመሬት ላይ፣ በበር፣ በወንበር፣ በጠረጴዛ፣ በማንኛውም ነገር ላይ ሊሆን ይችላል:: ይህን ልምድ አድርጎ ያደገ ልጅ መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ሕይወት ዘርቶ ይኖራል:: ስለዚህ የኃጢአትን ሀሳብ፣ የዓለምን ቋንቋ አያውቅምና እርሱም ኃጢአት አይሠራም:: ዳዊትም ያለው ይህንን ነው:: «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» (መዝ 118:11)::

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት፣ የስሜት፣ የፍቅር፣ የሀሳብ ማዕከል በሆነው ልብህ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው:: በአፋችን፣ በዕውቀት ማዕከል አእምሮአችን ውስጥ ብቻ መሆን የለበትም:: በልብህ ካለ ኃጢአትን ልታደርግ አትችልም:: ምክንያቱም ከስሜትና ከሀሳብህ ጋር ተቀላቅሎ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሉቃስ ወንጌል 2:9 የተጠቀመውን ውብ ቃል ከልብ አስተውለኸዋል? «ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር::»

እናታችን ሔዋን ደግሞ ሕጉን በአእምሮአቸው (በሕሊናቸው) ሸሽገው፣ በልባቸው ግን ካላኖሩት እና ከበደሉት ሰዎች የመጀመሪያዋ ናት:: ስለሕጉ እባብ በጠየቃት ጊዜም መልሷ ትክክለኛ ነበር:: ይሁን እንጂ ሕጉን በአንደበቷ እየተናገረችው ፈጣሪዋን ከመበደል አልተመለሰችም:: ስለዚህ አንተ ቃሉን በልብህ መዝገብ ልታኖረው፣ ልትጠብቀውና እየተናገርከ ልትሠራው ይገባሃል::

መጽሐፍ ቅዱስህን ዘወትር አንብበው:: በየዕለቱ አዲስ ነገርን እያገኘህ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ሀብቱ ሠፊና የማያልቅ ነውና:: የማያቋርጥና በቀጥታ ወደእግዚአብሔር ለሚያደርሰው ተመስጦም ምንጩ ነው:: «የሥራን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ፣ ሕግህ ግን እጅግ ሠፊ ነው::» (መዝ. 118:96) በሰው ዘንድ ለእያንዳንዱ ነገር ወሰንና ገደብ አለው:: የእግዚአብሔር ለሆነው ነገር ግን ከጥልቅነቱ የተነሳ ልትወስነው፣ ልትገድበው አትችልም:: ይህም የማይወሰነው አምላክ ቃል በመሆኑ ነው:: ባሰብከው ባሠላሰልከው መጠን መቆሚያ የሌለውን ስፋቱን ታያለህ:: ዘወትር ለአእምሮህ፣ ለመረዳትህ አዲስ ሆኖ የሚቀጥል ነው:: ነቢዩ ኤርምያስ ስለዚህ ነገር ሲናገር እንዲህ ይላል:: «ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ:: አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ» (ኤር 15:16)

«የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው:: ነፍስን ይመልሳል:: የእግዚአብሔር ምሥክር የታመነ ነው:: ሕጻናትን ጠቢባን ያደርጋል:: የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፣ ልብንም ደስ ያሰኛል:: የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፣ ዓይንንም ያበራል...... ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል:: ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል::» (መዝ 18:7-10)

የእግዚአብሔር ቃል ካለው ጥንካሬና ተጽዕኖ የተነሳ፣ አንተ ያነበብከው ማንኛውም ቃል በአንተ ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ እርግጠኛ ሁን:: ያለብዙ ጥረትና ትግል ቃሉን የተጠማውን ሁሉ ወደጥሩ ሰብእና የመቀየር ኃይል አለው:: ቃሉን ስታነበው ያለህ ስሜት እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንዳለና፣ ቃሉ ለመንገድህ ብርሃን እንደሆነ ነው:: ቀድሞውኑ





ለቃሉ ምንጭ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ዛሬም ከገቡ እንዲደርስ ኃይልና ብርታት ይሆነዋል:: በጰንጠቆስጤ ዕለት ብዙ ሕዝብ በሐዋርያት ሲነገር የነበረውን ቃል ከሰሙ በኋላ «ልባቸው ተነካ..... ወንድሞች ሆይ ምን እንናድርግ? አሉአቸው» የሚለውን እናስታውሳለን (ሐዋ. 2:37) ቅዱስ ጳውሎስም ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስን «ከሕጻንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን ዐውቀሃል» እያለ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት አበክሮ ሲያስገነዝበው ታነባለህ:: (2 ጢሞ. 3:15):: ስለዚህና ከዚህም በላይ ስለሆነው ነገር ሁሉ ነው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ክብርና ልዕልና ልትሰጥ የቻለችው::

## መጽሐፍ ቅዱስና ቤተክርስቲያን

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ክብር ትሰጣለች:: በየዕለቱ በሚቀደሰው ቅዳሴ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ ምዕራፎች ይነበባሉ:: ወንጌል ከመነበቡ በፊት የዳዊት መዝሙር በዜማ ይሰማል:: ወንጌል እየተነበበ ሳለም ሁለት ዲያቆናት የእግዚአብሔር ሕግ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችን ብርሃን ነው የሚል ምሥጢር ያለው የጧፍ መብራት ይዘው ይቆማሉ:: ከዚህም በላይ የብርሃናችን ብርሃን የዐይናችን ብርሃን የእግዚአብሔር ቃል ነው ሲሉ ነው:: ወንጌሉን ለመስማት በሚደረገው ጸሎትም ካህኑ «እኛንም እንደነርሱ ወንጌልህን ሰምተን ለመሥራት የበቃን ታደርገን ዘንድ በቅዱሳን ጸሎት እንለምንሃን» ይላል:: መጀመሪያውኑ ወንጌልን ለመሥማት የበቃን የተዘጋጀን መሆን አለብን:: ነገር ግን እኛ በራሳችን የበቃን አይደለንምና የቅዱሳን ጸሎት ያስፈልገናል:: ዲያቆኑም «ስለወንጌል ጸልዩ» ብሎ ሲያውጅ ሕዝቡ «ወንጌልህን ለመስማት የተዘጋጀን አድርገን» ይላል:: ሕዝቡ ሁሉ ለወንጌል ከሚሠጠው ክብር የተነሳ ወንጌል ሲነበብ አይቀመጥም:: የወንጌሉ ቃል ለዓለም ሁሉ መዳረስ ሲያመለክት ካህኑም ወንጌሉን ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ በመያዝ መንበሩን ይዞራል::

ምክንያቱም ደብዳቤው ለእርሱ እጅግ ውድ የሆኑ ቃላትን የያዘ ነው:: ለምንስ ይመስልሃል ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት «ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፣ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል» ያለው? (መዝ. 18:10)

መጽሐፍ ቅዱስን ከልብህ የምታፈቅረው ከሆነ ከማንበብህ ደስታ እርካታ ታገኛለህ:: ይህ ማለቂያ የሌለው መንፈሳዊ እርካታ ደግሞ ማንበብህን በጽናት እንድትቀጥልና እንድትመሠጥበት ያደርግሃል::

### 3. በትዕግሥትና ባለመሠልቸት አንብበው

ቅዱስ ዳዊት በመጀመሪያ መዝሙሩ እንደገለጸው መንፈሳዊ ሰው ደስታው በእግዚአብሔር ቃል ነው:: በቀን በሌሊት እያሠበው የሚመሠጠው በእግዚአብሔር ቃል ነው (መዝ. 1:2)

ቋሚ በሆነና በማይቀራረጥ መሠረት ላይ የተመሠረተ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ወደር የሌለው ከፍተኛ ጥቅም አለው:: በውስጡ ያለው የተቀደሰ መንፈስ እንዲዋሃድህ ከማድረጉም በላይ የሚያመጣው በጎ ተጽእኖና ለውጥም በውስጥህ የጸና ይሆናል:: በዚሁ ከቀጠልህ ማንበብህ በራሱ ቅዱስ ልምድ ይሆንልሃል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጡ በየዕለቱ ጠዋት ጠዋት፣ ከቤት ከመውጣትህ በፊት የምታነባቸው ክፍለ ንባቦች ይኑሩህ:: በማለዳ ይህን ማድረግህ ቀኑን ሙሉ ሕሊናህን በመግዛት እንድትውል ያስችልሃል:: በመግባትህም በመውጣትህም በውስጥህ የመላው የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል:: ከመተኛትህም በፊት ቢያንስ አንድ ምዕራፍ አንብብ:: እንቅልፍ እስከሚወስድህ ጊዜ ድረስ ትመሠጥበትና ከዚያም ሕልምህ የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል::

መጽሐፍ ቅዱስ በትዕግሥት፣ ዘወትር ለሚያነበው ሁሉ የደስታ ምንጭ ነው:: ከቃሉም ጋር የተሣሠረ ይሆናል:: ሁሌም በሀሳቡ ውስጥ የሚኖረው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል:: ስለዚህ ወንድሜ ሆይ በቀን በሌሊት ሕሊናህ በእግዚአብሔር ሕግ የተመሠጠ ልትሆን ትችላለህ:: ይህ ደግሞ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ለነበረው ንጉሥና ነቢይ ቅዱስ ዳዊት እንዲሁም ታላቅ መሪ ለነበረው ለኢያሱ እንኳን የተቻለ ነበር:: ከዚህ አንጻር ቀለል ባለ የኃላፊነት ሥፍራ ላይ ለምትገኘው ለአንተና ለሌላው እንዴት የተመቸ እንደሆነ አስበው::

### 4. በታላቅ አክብሮት አንብበው

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ማለት ለአንተ የሚናገረው እግዚአብሔርን መስማት ማለት ነው:: ስለዚህ ስታነበው ተገቢውን ክብር በመስጠት መሆን አለበት:: ለምታነበው ክቡር ቃል በምትሠጠው ክብር መጠን ደግሞ፣ ቃሉ በአንተ የሚያመጣው ለውጥ ይወሠናል:: ለዚህ እኮ ነው ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ወንጌል ከመነበቡ በፊት ዲያቆኑ እግዚአብሔርን በመፍራት ተነስታችሁ ቅዱሱን ወንጌል ስሙ (አድምጡ) የሚለን:: ካህኑም ከማንበቡ በፊት ለታላቁ ወንጌል ክብር እጣኑን ያሳርጋል:: «ወንጌልህን ለመስማት እንደሠማነውም ለመሥራት የበቃን የተዘጋጀን አድርገን» እያለ ሕዝቡን ወክሎ ይጸልያል:: ሰው ወንጌልን ለመስማት የመንፈስ ዝግጅት፣ ብቃት ያስፈልገዋል:: ሙሴ ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤልን አሥሩን ሕግጋት ለመሥማት ራሳቸውን እንዲቀድሱ፣ ለሦስት ቀናት ዝግጅት እንዲያደርጉ እና ለክብሩ የበቁ እንዲሆኑ ሲያዘጋጃቸው እንደነበረ እናስታውሳለን:: (ዘጸ 19:10-15)

መጽሐፍ ቅዱስን በግድ የለሽነትና በንቀት የሚያነበው ሰው ቢኖር በቃሉ ሊለወጥ አይችልም:: ይልቁንም ተናጋሪው እግዚአብሔርን ስለናቀ ይፈረድበታል:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስህን በታላቅ አክብሮትና በከፍተኛ ትኩረት ማንበብን ልትማር ይገባሃል:: ቤተክርስቲያን ስትሠጠው ያየኸውን ክብር ሁሉ አንተም ለመጽሐፍ ቅዱስ ስጥ::

### 5. በማስተዋል አንብበው

አምላካዊ ወደሆኑት ወደእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ጠልቀህ ግባና ምን እየነገሩህ እንደሆነ መርምረህ ተረዳ:: እንደተራ መጽሐፍ ሳይሆን፣ ሙሉውን ሀሳብህን አስገዝተህ፣ ተመስጠህ አንብበው:: «ጥበበኞቹም እንደሰማይ ጸዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደጽድቅ የሚመልሱ፣ እንደከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ::» (ዳን. 12:3) ፈሪሳውያን ከአይሁድ መካከል ሊቃውንት የሚባሉ ነበሩ:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል መረዳትና

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አልቻሉም ነበር:: ለምሳሌ «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» የሚለውን ቃል ይናገሩታል:: ይሁን እንጂ ምን ማለት እንደሆነ አይረዱትም:: ጌታችን ስለደጉ ሳምራዊ እስከነገራቸው ጊዜ ድረስም «ባልንጀራ» ምን ማለት እንደሆነ እንኳ አያውቁም ነበር::

መሠረታዊውና ለንባብ ጉልህ ሚና የሚጫወተው ማስተዋልና መረዳት ነው:: «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል» (ሆሴ 4:6) ማስተዋልና ዕውቀት ከሚያስፈልጉባቸው ነገሮች አንዱ፣ አንዲት ጥቅስ ላይ ተመሥርቶ ከመሳት ለመጠበቅ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መጽሐፍ እንጂ የጥቅሶች ክምችት አይደለም:: አንድ ነጠላ ጥቅስ ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ዓላማና ትእዛዝ በበቂ ሁኔታ አይገልጽም:: ስለዚህ ከምትፈልገው ርእስ ጋር የሚዛመዱ ብዙ ጥቅሶችን ከነሙሉ ንባባቸው ፈልገህ አሰባስብ:: በዚህ ነው ትክክለኛውን መልእክት መረዳት የምትችለው::

## ፮. የምታነበው ሁሉ በመንፈስና በጥልቀት ይሁን!

በቃሉ ሕሊናህ ሳይሰቀልና ሳትረዳው ከቀረህ ብዙ ማንበብህ ምንም ጥቅም የለውም:: የአንተ ጥቅም የሚወሠነው ወደቃሉ ውስጥ ጠልቀህ በመግባትህ ቃሉም የአንተን ውስጣዊ ስሜት እየበረበረ ሀሳብህን፣ ልብህን፣ ሁለንተናህን መንካትና ተጽእኖ ማሳደር እንዲችል ማድረግ ከመቻልህ ላይ ነው:: ስለዚህ በትክክል የሕጉ (የቃሉ) መንፈስ ምንድን ነው? ብለህ በመንፈስ መርምር:: ደግሞም ቃል በቃል በሚሠጥህ ትርጉም ላይ ብቻ ሳታተኩር፣ ወደውስጡ ግባ:: ጌታችን እንደተናገረው ቃሉ መንፈስና ሕይወት ነው:: (ዮሐ. 6:63):: ወሳኝ የሆነውን ጥቅሙንም የምታገኘውም በእውነት፣ በመረዳት ውስጥ ባለው በመንፈሳዊ መልእክት ብቻ ነው:: ቃል በቃል የሚተረጎመውንማ ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም ይጠቀሙበት አልነበረምን?

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሲገልጽ እንዲህ ይላል «በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሠጣል::» (2 ቆሮ 3:6)





ስለመንፈሳዊነትም ይሁን ስለእምነት ወይም ዶግማ በማስተዋል፣ በመንፈስ ማንበብ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው:: ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡታል:: ነገር ግን የሚያነቡት ስለማይገባቸውና ትክክለኛውን ትርጉም ስለማይረዱት ሀሳባቸው ይከፋላል:: «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት» የሚለውን አይገነዘቡትም:: (ራዕ 3:6) የክብር ባለቤት ክርስቶስም «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ» ነው ያለን:: (ማቴ 22:29) ስለዚህ እያንዳንዳቸውን የምታነባቸውን ቃላት ትርጉምና መልእክት ጠልቀህ በመንፈሳዊነት መርምረህ ተረዳ:: መምህራንንም ጠይቅ፣ አማክር::

ብዙ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡታል:: በአንዳንድ አላዋቂዎች ዘንድ እንዲያውም እንደሊቃውንት ይቆጠራሉ:: ነገር ግን ከማስተዋልና ከመረዳት ማነስ ከትክክለኛው መንገድ ስተዋል:: አንዳንዶቹም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዲት ጥቅስ ይዘው ስለሚነሱና የቀረውን ሙሉ ሀሳብ ስለሚዘነጉት ሙሉ የሆነ መረዳት የላቸውም::ይህን ቃል እንደምሳሌ ውሰድ «ከእኔ አብ ይበልጣል» (ዮሐ 14:28)

ይህን ለመተርጎም ቢፈልጉ እንኳን «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ. 10:30) ያለውን ቃል ከግምት ውስጥ አያስገቡትም::

ስለእምነት ለመናገር ሐዋርያው «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ» እንዳለ ይጠቅሳሉ (ሐዋ 16:31)፤ ነገር ግን ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ካለው ጋር አያይዘው ሲገልጹት አይታይም:: (ማር 16:16) ::

ስለዚህ ማንም «ተጽፎአል» ብሎ ቢጠቅስብህ እንደጌታችን «ደግሞ ተጽፎአል» ብለህ መልስለት:: አንድ ኃዘንተኛ ሰው «ከፊት ኃዘን የተነሳ ልብ ደስ ይሠኛልና» (መክ 7:3) ቢልህ ደግሞም «በጌታ ደስ ይበላችሁ፣ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ» የሚል ተጽፎአል ብለህ መልስለት:: (ፊልጵ 4:4) ደግሞም «ለሁሉም ጊዜ አለውና:: ለማልቀስ ጊዜ አለው፣ ለመሳቅም ጊዜ አለው::» የሚል ተጽፎአል (መክ 3:1,4):: በዚህ መንገድ ብትሄድ ያነበብከውን በማስተዋልና በመረዳት ጠቢብ ትሆናለህ::

አንድ አድቬንቲስት «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» (ዘጸ 20:8) የሚለውን ጠቅሶ ቢከራከርህ፣ ደግሞም «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለበዓል ስለወር መባቻ ወይም ስለሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ:: እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና::» (ቆላስ 2:16) የሚል ተጽፎአል ብለህ መልስለት::

በዚህ መልኩ የተሰባሰቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጥሩ የሆነ ሀሳብንና ጥልቅ የሆነ መረዳትን ይፈጥራሉ::

## 7. በቃልህ አጥናው

ይህም ሌላው በአንተና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት ነው:: ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ልዩ መንፈሳዊ መመሪያህ የሚሆኑትን፣ ወይንም መሠረተ እምነት (ዶግማ) የሆኑትን፣ የሚያበረታቱና የሚያጽናኑህን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች እና ለችግሮችህ ምላሽ የሆኑትን ቃላት ያለመጽሐፍ በአእምሮህ ውስጥ ቅረጻቸው:: በጣም አሳሳቢ እንደሆኑ ነገሮች በሕሊናህ አሰላስላቸው:: በዚህ ዓይነት ወደነፍስህ ዘልቀው ይገቡና በማስታወስህ ውስጥ ተተክለው በአስፈላጊው ጊዜ ሁሉ የረድኤት የመጽናናት ምንጮች ይሆኑሀል::

ለምሳሌ በዚህ መልክ ማጥናት ትችላለህ::

የተራራው ስብከት ማቴ 5፣ የፍቅር ባህርያት 1 ቆሮ 13፣ በሮሜ 12 እና በ1 ተሰ 5 የሚገኙትን በርካታ ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚበጁ ምክሮች፣ ወይም ከመጽሐፈ ምሳሌና መክብብ፣ 10ሩን ትእዛዛት ዘጸ 20 እና ዘዳ 5፣ የዳዊትን ምርጥ መዝሙሮችና ጸሎቶች፣ ስታነባቸው ልብህን የሚነኩትን ሌሎች ጥቅሶች፣ ስለጥሩ ሥነ ምግባር የሚነግሩህን እና የመሳሰሉትን በቃልህ ማጥናት ትችላለህ::

አስበው! አንድ መንፈሳዊ ሰው በቀን አንድ ጥቅስ ቢያጠናና በቃሉ ቢይዝ በአንድ ዓመት ምን ያህል ሊይዝ ይችላል?

ይህም ባይሆን በሳምንት እንኳን አንድ ጥቅስ ቢይዝ፣ ያለጥርጥር በዓመት 52 ጥቅሶች በ10 ዓመት 520 ጥቅሶች በአእምሮው ውስጥ ሊኖሩት ይችላል:: ይህ በጣም በጥቂቱና ሳይጨነቅ ሳይጠበብ የሚያደርገው ሲታሰብ





ነው እንጂ. እንደዚህ በከንቱ በሚባክነው ወርቃማ ጊዜያችን ምን ያህል የሕይወት ቃላት ልናከማች እንደምንችል ገምት!

ቀጣዩ ደግሞ እነዚህን ቃላት ወደሕይወት መቀየርና ተግባራዊ ማድረግ ነው:: እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው ነው::

አንተ ወንጌልን አጥናው፣ እርሱ ይጠብቅሃል::
መዝሙሩን አጥናው፣ መዝሙሩም አንተን ይጠብቅሃል:: እንዴት?
የሚቀጥለውን ተመልከት

## 8. ሕሊናህን በመግዛት /በመሠብሠብ/ አንብበው

ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ያጠናሃቸው ማናቸውም ቃላት ራስን የመግዛት፣ ሕሊናን የመሠብሠብ ምንጭ ሊሆኑህ ይችላሉ:: ቃላቱን ከነፍስህና ከሀሳብህ ጋር ታዋሀዳቸውና ቀጥሎ በሚበዛልህ የእግዚአብሔር ጸጋ ውጤቱን ታያለህ:: እያንዳንዱ ቃል ሠፊ ትርጉምና ጠቀሜታ እንደነበረው፣ በየዕለቱ አዲስ ሆኖ በልብህ ውስጥ እንደሚያድግና ፍፁም መንፈሳዊ ሁኔታ ውስጥ የገባህ እንድትሆን የሚያደርግህ መሆኑን ታያለህ:: ስለዚህ እኔ የምመክርህ እንድታነብ ብቻ ሳይሆን፣ ቃሉን እንደሥጋ ፈቃድ እንዳትተረጉመውና በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነህ፣ በመንፈስ መርምረህ እንድትረዳው ነው:: «ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፣ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ::» (2 ጴጥ 1:20)

በዚህ ጉዳይ ላይ በሠፊው የምንነጋገረው በምዕራፍ ፬ ስለሆነ አሁን ወደሚቀጥለው ነጥብ እንለፍ::

## 9. በጸሎት መንፈስ አንብበው

አምላክህ እግዚአብሔር ማስተዋልን እንዲሠጥህ፣ ፈቃዱን እንዲገልጽልህ በመጸለይ ጀምር:: እንደ ቅዱስ ዳዊት «ዐይኖቼን ክፈት ከሕግህም ተአምራትን እያለሁ» በለው:: (መዝ 118:19):: ስትጨርስም ጌታን ያነበብከውን ተግባራዊ ለማድረግ ጽናቱን እንዲሰጥህ፣ ማስተዋሉንና

ተነሳሽነቱን እንዲያድልህ ጌታን በመለመን አጠቃልል:: መጽሐፍ ቅዱስ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ::» ስለሚልህ ስታነበው በጸሎት የታጀብክ ሁን::
(ምሳ 3:5) ትክክለኛውን አምላካዊ መልእክት በጸሎትህ ለመቀበል ሞክር::

አንዳንድ ሰዎች አስቀድመው የወሠኑትን ነገር ለማረጋገጥ ሲሉ ብቻ ወይም ያንን የሚደግፍላቸውን ጥቅስ ለማግኘት ያነባሉ:: የተገለጸውን የእግዚአብሔር ሀሳብ ወደገዛ ፈቃዳቸው ለመቀየር ይጥራሉ:: አንተ ግን ለመረዳትህና እግዚአብሔር የሚልህን ብቻ ለመስማት ተዘጋጅተህ አንብብ:: ሃሳብህን ወደእግዚአብሔር ሃሳብ ለመቀየር እንጂ የእግዚአብሔርን ወደአንተ ለመቀየር አታንብብ ትሕትና ለጸሎት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ የሚያስፈልግህ ትልቁ ነገርም እርሱ ነው::
በትሕትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች መታዘዝ ትችላለህ::

ትሕትና ሀሳብህን መቀየር ማረቅ የምትችልበት መንገድ ነው:: ትሕትና ከዳዊት ጋር «አቤቱ መንገድህን አመልክተኝ ፍለጋህንም አስተምረኝ» እያልክ ዕውቀትን እንድትለምን የሚያደርግህ ነው:: (መዝ 24:4)::

ሕሊናህ ተሰቅሎ በቃሉ ተመስጠህ ስታነብ
«ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?» በለው::

በእርግጥ ምን ማድረግ አለብህ? ተከተለኝ::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይልና ውጤቱ

### በቤትህ ያለው ቦታና የአንተ ድርሻ

አምላካችን ስሙ የተመሠገነ ይሁንና ይህን በተመለከተ የሚነግረን ግልጽ የሆነ ቃል ይህ ነው:: «ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፣ የምሻውን ያደርጋል:: የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደእኔ በከንቱ አይመለስም::» (ኢሳ 55:11)::

በትክክል! የእግዚአብሔር ቃል ባዶውን አይመለስም:: የራሱ የሆነ ኃይልና ውጤት አለው:: ኃያል ቃሉን ሰምተው በሕይወታቸው ተግባራዊ ያደረጉት ሰዎች ኃይሉን ለሌሎችም ማስተላለፍ ችለዋል:: ሐዋርያው ቅዱስ





ጳውሎስ የቃሉን ኃይልና ተጽእኖ ሲገልጽ ያለውን ልብ ብለሃል? «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው:: ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፡፡ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ 4:12)

«ካልተነካሁበት ለምን አነበዋለሁ?» ብለህ ታስብ ይሆናል:: ችግሩ ግን ከምታነበው ቃል ሳይሆን ከአንተ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን:: ቃሉማ በሁለቱም ወገን የተሳለ ሰይፍ ነው:: ይሁን እንጂ ሰይፉ ሥጋን እንጂ ድንጋይን አይቆርጥም:: ለዚህ እኮ ነው ጌታ እግዚአብሔር በነቢዩ ሕዝቅኤል አድሮ «የድንጋዩን ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ:: የሥጋንም ልብ እሠጣችኋለሁ» ያለው (ሕዝ 36:26) ::

የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል የአንተ ልብ ምን ዓይነት ነው? ድንጋይ ወይስ አለት ነው? የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና ውጤታማ ነው:: የበለጠ የሚሠራው ግን ቃሉ እንዲሠራባቸው ፈልገው ልባቸውን ለከፈቱ ብቻ ነው::

የእግዚአብሔር ቃል በአንተ ላይ ዛሬ ባይሠራ ትንሽ ታገስ፣ ነገ ታየዋለህ:: ዋናው ነገር ቃሉ በፍጹም በከንቱ አይመለስም:: ሁኔታዎች እስከሚመቻቹለትና ልብህ ዝግጁ እስከሚሆን ድረስ በሕሊናህ ውስጥ ጸንቶ ይቆያል:: በተወሰነው ሰዓት ግን ውስጥህን ሠርስሮ ሲገባና ውጤታማ ሲሆን ታየዋለህ:: የመጀመሪያው ችግር የተፈጠረው ልብህ ስለቀዘቀዘና ፈጣን ምላሽ መስጠት ስላልቻለ ይሆናል:: ቀስ በቀስ ግን ራስህ ነቅተህ ትነሳለህ (መኃልይ 5:2-6)::

«.... ውዴ እጁን በቀዳዳ ሰደደ፣
አንጀቴም ስለእርሱ ታወከ::
ለውዴ እከፍትለት ዘንድ ተነሳሁ፣
እጆቼ በደጁ መወርመውሪያ ላይ ከርቤን አፈሰሱ
ጣቶቼ ፈሳሹን ከርቤ አንጠበጠቡ::
ለውዴ ከፈትሁለት ውዴ ግን ፈቀቅ ብሎ አልፎ ነበር::

ነፍሴ ከቃሉ የተነሳ ደነገጠች.....»

በምድር ላይ የሚዘራው ዘር ሁሉ ወዲያው በቅጽበት ፍሬ አይሰጥም:: ቀናት ወይም ወራት ሊወስድ ይችላል::

እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ቃል በልብህ ውስጥ ዝራው:: መልካም ጥንቃቄና ከፍተኛ ጥረት ባደረግህበት፣ ሥራውን ከሚገድብ ውስጣዊና ውጫዊ ችግር በታቀብክበት ጊዜ ላይ አድጎ ፍሬ ይሠጣል::

የእግዚአብሔር ቃል በመሬት ውስጥ ሆኖ ለማብቀል ውሃ እንደሚጠብቅ ዘር ነው:: ዘር ውሃ ሲያገኝ ፈጥኖ ይበቅልና ወጥቶ ይታያል:: ይህን ውብ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከዚህ ጋር አጣምሬህ ተመልከተው:: «እንጀራህን በውሃ ፊት ላይ ጣለው፣ ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህ::» (መክ 11:1)::

እንግዲህ ይህ! ከሆነ ቅጽበታዊ ፍሬዎችን አላየሁም ብለህ በአገልግሎትህ ተስፋ አትቁረጥ:: በመንፈስ ዝለህ እንዳትወድቅ እግዚአብሔርን በትዕግስት ጠብቀው:: ሰዎች ሁሉ አንድ ዓይነት አይደሉም:: ሁሉም ፈጣን ምላሽ አይሰጡም ሁኔታዎችም እኩል የተመቻቹ ሊሆኑ አይችሉም:: ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ የሚነካበት እንዳለ ሁሉ ቃሉ ለሚፈጥርበት ጥያቄ ብዙ ማብራሪያና አጥጋቢ ትምህርት የሚሻም አለ:: ለሕይወት ሳይሆን ለዕውቀት ብቻ የሚቀበለውም አይጠፋም:: ይህኛው ቃሉን የሚቀበለው ለነፍሱ መዳን ወይም ልቡን ለማንጻት ሳይሆን ዕውቀቱን ለማስፋት ስለፈለገ በአእምሮው ለመያዝ ብቻ ነው:: ልክ በአንድ ሳይንቲስትና በመናኝ ባህታዊ መካከል እንዳለው ልዩነት ማለት ነው:: ሳይንቲስቱ መጽሐፉን ያነባል፣ ያጠናል፣ ያብራራዋል:: እየተናገሩት እንደማያደርጉት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ይተረጉመዋል:: (ማቴ 23:2):: ባህታዊው ግን ቅዱስ ዳዊት «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» እንዳለው እንደትልቅ ሀብቱ ይጠነቀቅለታል፣ ይጨነቅለታል::

**መጽሐፍ ቅዱስ በአንተ ውስጥ የሚሠራው ሥራ**

የእግዚአብሔር ቃል በውስጥህ እንዲሠራ ምላሽ በሠጠህበት ጊዜ መለኮታዊው ቃል በውስጥህ እንዲሠራ የምትጠብቀው ነገር ምንድን ነው?





መቼም ውጤቱ እጅግ ብዙ መሆኑ ጥርጥር የለውም::
እስቲ ጥቂቶቹን አብረን እንመልከት:-

**1. የተበተነውን ሀሳብህን ሰብስቦ ከአምላክህ ጋር ያገናኝሃል**

ሀሳቦችህ የተበታተኑ ከሆኑ በየት እንዳለህ አታውቀውም:: በአጠቃላይ ማንበብ ግን ሕሊናህን ፍጹም አድርጎ በምታነበው መሠረተ ሀሳብ ላይ ብቻ እንድታተኩር ያደርግሃል:: በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ሰላም ወደሠፈነበት የጸጥታ ወደብ የሚመራህ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ወደእግዚአብሔር የምትጓዝበት መንገድህ ነው:: ንባብህ ክብር የተመላበት ከሆነ ድንቅ የሆነ መሠረታዊ ውጤት ለማየት የምትበቃበትን አትኩሮት ይፈጥርልሃል::

**2. አስተዋይና ብሩህ አእምሮ ያለው ሰው ያደርግሃል**

የማስተዋል ብርሃንና ዕውቀትም ይሰጥሃል::

ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ይላል «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው::» (መዝ 118:105) ደግሞም «የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው:: ልብንም ደስ ያሠኛል:: የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፣ ዐይንንም ያበራል» ሲል ታገኘዋለህ:: (መዝ 18:8)::

ወንጌል በሚነበብበት ጊዜ ጧፍ የምናበራበት ምስጢርም ይህ ነው:: ማንም ሊያስተምርህ ከሚችለው በላይ አስተዋይ የሚያደርግህ መጽሐፍ ቅዱስ ነውና ምስክሩ ትዝታህ ይሁን:: ይህን ብታደርግ የጌታን መንገድና እንዴት ጥበብን ማግኘት እንደምትችል ታውቃለህ:: በተለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን እንዴት ሠርተው እንዳለፉና እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር እንደኖሩ የማወቅ ፍላጎት ካለህ ሀብትህ እጥፍ ድርብ ነው:: «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው::» (ዕብ 13:7)

**3. ወደትክክለኛው እምነት ይመራሃል**

ይህ ሊሆን የሚችለው በማስተዋል፣ መለየት በመቻልና በመረ የምታነብ ከሆነ ብቻ ነው:: ለእያንዳንዱ የምታምንበት ነገር ሁሉ ጥርት አድርገህ የምታውቀው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ጥቅስ ከነሙሉ ሀሳቡ

አጥንተህ ብትዘጋጅ ከሀሰት ትምህርቶችና ከመናፍቃን የሚጠብቁህ መሳሪያዎች ይሆናሉ:: ይህ ደግሞ ታላላቅ የሃይማኖት አርበኞችና የእምነት ጀግኖች ቅዱሳን የተጠቀሙበት፣ ወደእግዚአብሔር የተጓዙበት መንገድ ነው:: በማስተዋላቸውና ድንቅና ጥልቅ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታቸው ከሀድያንንና መናፍቃንን መቋቋም እንደቻሉ ዕወቅ::

### 4. ወደንስሓ ሕይወትና ወደመንፈሳዊ እድገት ያደርስሃል

ድክመትና ኃጢአትህን ባለመሸፈን በትክክለኛው መንገድ ለራስህ የምትሠጠው ግምት ላይ መድረስ የምትችለው በዚህ ውድና ብርቅ መጽሐፍ ሕግጋት ብርሃንነት ነው:: የቅድስና ሕይወትና ፍጹምነት እንጂ ከኃጢአት መመለስ ብቻ እንደማይበቃህ የሚያሳውቅህ ይህ መጽሐፍ ነው:: እነዚህን ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃዶች የነገረህ ማነው? «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ፣ ተብሎ እንደተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» (1 ጴጥ 1:15-16፤ ዘሌ 11:44) :: አምላክህ ክርስቶስም «የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ» እያለ ሲመክርህ የምታገኘው በሌላ ሳይሆን በዚህ የሕይወት መጽሐፍ ብቻ ነው:: (ማቴ 5:48)::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለንስሓ ሕይወት፣ ቅድስናና ፍጹምነት በምሳሌ የተደገፈ በርካታ ዝርዝር መግለጫዎችን ይሠጥሃል:: ባለማወቅህ እንዳትስትም ያስጠነቅቅሃል:: (ማቴ 22:29)::

### 5. በኃጢአት ፈተና ውስጥ ብትሆን የአእምሮና የፈቃድ ትሕትናን ያስተምርሃል

በምታነብበት ጊዜ በመንፈሳዊነትና በእግዚአብሔር ቃል የተቀደሰው ሀሳብህ በቀላሉ በኃጢአት ሊረክስ አይችልም:: ይሁን እንጂ በተዘናጋህበት ጊዜ ላይ ጠላትህ አግኝቶህ እንዳይማርክህ እንዴ ተቀድሼአለሁ እንዳትል፣ መጠንቀቅ እንዳለብህ ሳልመክርህ አላልፍም:: «በመጠን ኑሩ ንቁም! ባለጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና:: (1 ጴጥ 5:8)::





### 6. በዲያብሎስ ውጊያዎች ውስጥ ብትሆን ኃጢአትን በሕግ እንድትመልስ ያስችልሃል

አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት በመጽሐፉ ስለሀሳብ ውጊያዎች እንደገለጸው ከምንም በላይ ክቡር የሆነው ጊዜህ በከንቱ ልፍለፋና ብዙ በማውራት ቢባክንብህ «በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስታውስ:: (ምሳ. 10:19)

መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊትም «አቤቱ፥ ለአፌ ጠባቂ አኑር፣ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ» ይላል:: (መዝ 140:3)

ዲያብሎስ ቁጡ፣ ብስጩ እንድትሆን ቢፈታተንህ «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን:: የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና» የሚለው የሐዋርያው ያዕቆብ መልእክት (ያዕ 1:19) እንዲሁም «ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን፣ ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ» የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን ምክር ትዝ ይበልህ (ምሳ 22:24)::

በተመሳሳይ መልኩ በዝሙት ሀሳቦች ቢዋጋህ የልዑሉን ጌታ ትምህርት አስብ:: «ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል::» (ማቴ 5:28):: «ከዐይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ:: እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ያለውን ጻድቅ ኢዮብን አትርሳው:: (ኢዮ 31:1) ጠላትህ በአንተ ላይ ያዘጋጀውን ማንኛውም መንፈሳዊ ውጊያ መመለስ የምትችለው የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት ማስተዋልና ሁሌም መጠቀም ስትችል ብቻ ነው:: ሕጉን ማስታወስ ከቻልክ ኃጢአትን ከመፈጸም ትጠበቃለህ:: ኃጢአትን የሠራ ማንም ሰው በአብዛኛው ምክንያቱ ሊሆን የሚችለው ሕግን መርሳቱ ነው:: ኃጢአትን መውደድ ሕሊናን ያደነቁራልና::

### 7. በጭንቀት ጊዜ መጽናናትን በድካም ጊዜ ብርታትን ይሰጥሀል

ይህ ቅዱስ ዳዊት በተደጋጋሚ አምላኩን ሲማጸንበት የነበረ ታላቅ ነገር ነው:: «ነፍሴ መድኃኒትህን ናፈቀች፣ በቃልህ ታመንሁ» (መዝ 118:81)፤ ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸውን ቃልህን አስብ፣ ቃልህ ሕያው

አድርጎኛልና ይህች በመከራዬ ደስ አሠኘችኝ» (መዝ 118:49)። በፈተና ውስጥ ሳለ እንኳን ይል የነበረው ይህንን ነው።«እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን፣ ሰዎች በእኛ ላይ በተነሱ ጊዜ፣ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር።...ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች። ወጥመድ ተሰበረ፣ እኛም አመለጥን። ረድኤታችን ሰማይና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።» (መዝ 123:2-8)።

ስለተስፋ የሚነግረን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዴት ብዙ ነው! ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው እነዚህን ቃላት አንብቦ በልቡ የሚጠብቃቸው፣ ሰላምን አግኝቶ፣ ዘወትር የተጽናና ይሆናል። «በተስፋ ደስ ይበላችሁ!» (ሮሜ 12:12)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምታነባቸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች ለውሳጣዊት ነፍስህ ሰላምና ጸጥታን የሚያጎናፅፉህ ናቸው። «እኔ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» (ማቴ 28:20)።

ይህን የመሳሰሉ መጽናኛዎችህ እጅግ ብዙ ናቸው። እነዚህን ብታጠናስ? «የእናንተስ የራሳችሁ ጸጉር ሁሉ እንኳን ተቆጥሮአል፣ እንግዲህ አትፍሩ» (ማቴ 10:30)

«እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሳብህ የለምና አትፍራ» (ሐዋ 18:10)

ስለነዚህ ሁሉ እንዳልተርክልህ ጊዜና ቦታ ያጥረኛል።

## 8. ለማንኛውም (ለሁሉም)

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ለሁሉም ሰው፣ ለሁሉም ሁኔታዎች፣ ለሁሉም ቦታ ሁሉንም ነገር ይዞ ይገኛል። በየትኛውም ቦታ ሁን፣ በየትኛውም የሥነ ልቡና ሁኔታ ሁን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የምትፅናናበትን ቃል ይሰጥሀል። የምትፈልገውን፣ አንተን የሚያረካህን ሁሉ ታገኝበታለህ። ለምሳሌ የዳዊትን መዝሙሮች ብትወስድ ሁሉንም ሀሳቦችና የጸሎት ዓይነቶች ያሳይሀል። መጽሐፈ ምሳሌም ከምክር ዓይነቶች የሚቀረው አንድም የለም። አንተ ከመረጥከውና ከወደድከው እያንዳንዱ መጽሐፍ ለአንተ የሚሆን ልዩ መልእክት የያዘ ነው።





### መጽሐፍ ቅዱስን

1. ለጸሎት ልትጠቀምበት ትችላለህ

ማንበብ ስትጀምርና ስትጨርስ ጸሎት አድርግ። በተጨማሪም ማንበብህ በውስጥህ ወደጸሎት ልትቀይራቸው የምትፈልጋቸውን ልዩ ሀሳቦች ያቀጣጥልልሃል። ለምሳሌ የዳዊት መዝሙር እንዴት መጸለይ እንዳለብህና በምን ዓይነት ሁኔታ ከአምላክህ ጋር መነጋገር እንደሚገባህ ያስተምርሃል። በተመሳሳይ መልኩ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የምታገኛቸው የእግዚአብሔር ሰዎችን ጸሎት ስታነብ ልትማር የምትችለው ነገር እጅግ ብዙ ነው። ከእነዚህም መካከል የነቢዩ ዳንኤል ጸሎት (ዳን 9)፣ የእዝራ ጸሎት (እዝ 9)፣ የናሆም ጸሎት (ናሆ 1)፣ የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት (1 ነገ 8)፣ የዮናስ ጸሎት (ዮናስ 2) እና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት (ሉቃ 1) ናቸው።

2. የተመሰጠ ምንጭ አድርገው

ታሪካዊ ከሆኑት መጻሕፍት አንዱን የተለየ ድርጊት መርጠህ በተደረጉት ተዓምራት ላይ ልብና ሀሳብህን ሰቅለህ ተመስጦ አድርግበት።

3. ለመንፈሳዊ እድገት መለማመጃ አድርገው

በሥነ ምግባራዊ ሕይወት ለማደግ እንድትችል አሁን ላለህበት መንፈሳዊ ደረጃና ፍላጎት የሚስማማህ ምን እንደሆነ ምረጥ። መንፈሳዊ ልምምዶች በሚለው ምዕራፍ (በክፍል ሁለት መጽሐፍ) ስለዚህ ጉዳይ ሰፊ መግለጫ ታገኛለህ።

4. የንስሓ መንገድ አድርገው

በምታነበው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሁሉ ንስሓ የመግባት ዕድል እንዲኖርህ «ለእኔ» ብለህ አንብበው። ጌታችንም ዮሐንስም «ንስሓ ግቡ» ያሉት ለአንተም እንደሆነ አስብ። ለምሳሌ ጌታችን «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ። አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ» ያለውን ቃል ብታነብ በውስጥህ

የበደልከውን ወይም የበደለህን እንድትታረቅ፣ ይቅር እንድትል፡ ይቅርታም እንድትጠይቅ የሚገፋህ ጠንካራ ኃይልን ስለምታገኝበት ተጠቀምበት:: (ማቴ 5:23)::

## ቤትህ፣ ቤተሰብህና መጽሐፍ ቅዱስ

በአራት ዘዳግም ላይ በተጻፈው በዚህ ትእዛዝ ተነስቼ የማስገነዝብህ ነገር አለኝ:: «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው:: በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም ስትነሳም፣ ተጫወተው:: በእጅህም ምልክት አድርገህ እሠረው:: በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው::»

(ዘጸ 6:6-9)::

እነዚህን ትእዛዛት ምን ያህል ትፈጽማቸዋለህ?

ሀ. ሚስትህ ልጆችህ ሁሌ ሊያስታውሱት የሚችሉት ሕግ በቤትህ ግርግዳ ላይ ተሠቅሏል?

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው በልብህ የያዝከውን ለልጆችህ ታስተምራቸዋለህ? «ለልጆችህም አስተምረው::» ልጆችህን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ጥለህ ራስህን ከኃላፊነት ነጻ ታደርግ ይሆን?

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስን በትእዛዙ መሠረት በቤትህ ውስጥ የሚነገር ቋንቋ አድርገህ ትጠቀምበታለህ? «በቤትህ ስትቀመጥ.....ተጫወተው»

መ. በየዕለቱ ከቤተሰብህ ጋር ታነበዋለህ?

በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ የተሰበሰበ ቤተሰብ አለህ?

ሠ. ለልጆችህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የመያዝ ውድድር አዘጋጅተህ በዚሁ መሠረት ታሠለጥናቸዋለህ?

እኔ በእግዚአብሔር ፊት የጠየቅሁህን ሁሉ ራስህን ጠይቅ!





# ምዕራፍ ፫

## ገድለ ቅዱሳን ማንበብ

ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሳደግ፣ ለእርሱና ለመንግሥቱ ያለንንም ፍቅር ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ በጸጋው የምንጠቀምበት ሌላው መንፈሳዊ መንገድ የቅዱሳንን ሕይወት የሚያሳዩንን፣ የገድላቸውን መጻሕፍት ማንበብ ነው::

ገድለ ቅዱሳን መንፈሳዊ መመሪያዎችን በተግባራዊ መንገዳቸው ያቀርብልናል:: ከእግዚአብሔር ሕግጋት አብዛኛዎቹ በቃል ደረጃ ብቻ የተቀመጡ የሚመስለው ቢኖር እንኳን የቅዱሳንን ገድል ሲያነብ ትእዛዛቱ ሁሉ በዕለት ከዕለት ተግባራቸው፣ በሕይወታቸው ተፈጽመው ለአርአያነት ቀርበው ያገኛቸዋል::

እነዚህ መጻሕፍት ለቃል ብቻ የተሠጠ ሕግ እንደሌለና ሁሉም ያማሩ የተወደዱ እና በተግባር ሊውሉ የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ:: ብዙ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች «እነዚህን ትእዛዛት ማን ሊፈጽማቸው ይችላል?» የሚል የመገረም ጥያቄ ያነሳሉ:: እውነት ቀኝ ጉንጭን በጥፊ ለሚመታ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙሮ መስጠት ይቻላል? (ማቴ 5:39)፣ ሳያቋርጡ ልብንም ሳይከፍሉ መጸለይስ ሁሌ የሚቻል ነገር ነው? (ሉቃ 18:1፤ 1ተሰ 5:17)፣ ሰው ያለውን ሁሉ ለድሃ ሰጥቶስ ምን ይሆናል? (ማቴ 19:21) እነዚህን ሁሉ እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ግን በቅዱሳን ሕይወት ውስጥ ተመልሰው የምታገኛቸው ስለሆነ ገድላቸውን አንብብ::

ጌታም እነዚህ ቅዱሳን ለእኛ ሥነ ምግባራት ሁሉ አርአያና ምሳሌ እንዲሆኑን ይፈቅዳል:: በእውነት እነዚህ ቅዱሳን ከሥጋዊ ሕይወት፣ ከቁስ አካላዊነት ተለይተው የተጠሩበት ጥሪ ድንቅ ነው:: በእግዚአብሔር መንፈስ መኖር ስለቻሉና፣ በማናቸውም የጠላት ፍላጻዎች ላይ ፍጹም ድልን ስለተቀዳጁ በእውነት ምድራውያን መላእክት ናቸው:: ያለመጠራጠር የሰው ልጅ መጀመሪያ የተፈጠረበትን የእግዚአብሔር አርአያና አምሳል መልሰው

እንደታዩ መናገርም ይቻላል፡፡ ለእኛም ሕይወታቸው በመንፈሳዊ መንገዳችን ላይ ያለጥርጥርና ፍርሃት መጓዝ እንድንችል ጽናትን ይሠጠናል፡፡ ገድላቸውንም በምናነብበት ጊዜ «እነርሱን የረዳ አምላክ እኛንም ይረዳናል» ብለን በእርግጠኝነት እናምናለን፡፡

የቅድስና ሕይወት ለፈለገውና ለመረጠው ሁሉ ይቻላል፡፡ አሁን ካለንበት ደረጃ ከፍ ብለን የእግዚአብሔር ጸጋ በየልባችን እንዲሠራ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነፍስን ወደእግዚአብሔር በመምራት፣ ልዩ ሀብቶችን በመስጠትና በረድኤት ከክርስቲያኖች ጋር ይሠራል፡፡ ቅዱሳን የሠሩት የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣቸው የሠራውን ነው፡፡ ታሪካቸውን ስታስብ በሕይወታቸው ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት እንደሠራና በእነርሱ እንደተመሠገነ አስተውለሃል?

የእነዚህ ሁሉ የጀግንነት ሥራዎቻቸው ምክንያትስ ገብቶሃል? በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጠንካራ ሕብረት እንደነበራቸው አትረዳም? (2 ቆሮ13:14)፡፡

የቅዱሳን ሕይወት በዘመናት ውስጥ ትውልድ ላይ ጥልቅ አዎንታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ በቅዱስ አትናቴዎስ የተጻፈው የቅዱስ እንጦንስ ታሪክም በሮም ሕዝብ ላይ እጅግ የሚያስገርም ለውጥ ያመጣና ለገዳማዊ ሕይወት መስፋፋት ትልቅ ምክንያት የሆነ ነበር፡፡ ቀድሞ ፈላስፋ የነበረው አውግስጢኖስም ይህንኑ ታሪክ ሲያነብ ነው ከልብ ተነክቶበት በንስሓ ለመመለስ የበቃው፡፡ በሲሐት በረኃ ይኖሩ የነበሩ መነኮሳትም ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው አርአያ የሆናቸው ከዓለም ተለይተው በበረሃ ይኖሩ የነበሩ አባቶች ሕይወት ነበር፡፡ በእነዚህ ምድራውያን መላእክት ቅዱሳን አባቶች ሕይወት ተስበው እነሱን ለማየት ከሩቅ አገር፣ ረጅም ርቀት አቋርጠው መጡ፡፡ መንፈሳዊ በረከት የሚያገኙበትን ምክራቸውን ሰሙ፡፡ ብዙዎቹም ምግባር ትሩፋትን ካዩትና ከሰሙት በልቡናቸው ቀርጸው ማቆየት ቻሉ፡፡ ይህም እስከአሁን ድረስ ለእኛ ከቅዱሳን ሕይወት መማር የምንችልበት ቅርሳችን ሆነ፡፡

ቅዱሳን የራሳቸውን ገድል አልጻፉም፡፡ ይሁን እንጂ በሌሎች አበው የተጻፈላቸው መጽሐፍ ዛሬ ለመንፈሳዊ ሕይወት ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና





ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ይህም አብረዋቸው በነበሩ አባቶች ተጽፎና ተነቦ ለቀጣዩ ትውልድ የተላለፈ ሕያው ታሪክ ነው፡፡ ነቢያትና ሐዋርያትም በመንፈሰ እግዚአብሔር ተነሳስተው ሲጽፉልንና ለእኛ ሲያደርሱን እራሳቸውን በስም ጠቅሰው ሳይሆን አብዛኛዎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገኙት ጽሑፎቻቸው ኋላ በስማቸው የተሰየመ ነው፡፡ መጻሕፍቱም እግዚአብሔር በእነርሱ አማካይነት ያስተላለፈውን መልእክትና ድንቅ ሥራውን የራሳቸውንም የቅድስና ሕይወት በግልፅ ያሳዩናል፡፡

ቤተክርስቲያናችን ለክብረ ቅዱሳን ታላቅ ሥፍራ ትሠጣለች፡፡ ለክርስቲያኖች መጽናኛ እና የጥንካሬ ምንጭ እንዲሆን ገድላቸው በመጽሐፈ ስንክሳር ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በጸሎተ ቅዳሴም ላይ ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ በተወለዱበት፣ ሰማዕትነትን በተቀበሉበትና እግዚአብሔር በእነርሱ አድሮ ታላላቅ ድንቅ ሥራዎችን ባደረገባቸው ዕለታት ቤተክርስቲያን አምላካቸውን ለማመስገን ስሙን ለማወደስ በስማቸው ታላላቅ መንፈሳዊ በዓላትን ታደርጋለች፡፡ ዋናው ዓላማ በክርስቲያኖች ውስጥ «ከእግዚአብሔር ጋር ሁሉም ይቻላል» የሚለውን መርህ ለማስረጽ ነው፡፡ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል» (ዮሐ. 15:5)፡፡

በየዕለቱ ሥራቸውን እንድናስታውስና ሕይወታቸው የመንፈስ ምግብ እንዲሆነን ስዕሎቻቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ በፊታቸው ከሚበራ መብራት ጋር ይቀመጣል፡፡ ይህ ደግሞ ለምእመኑ በተቀደሰ ተግባራቸው ሕሊናው እንዲመሠጥ ለበጎ ሥራ እንዲነሳሳ ምክንያት ይሆናል፡፡ ማር ይስሐቅ ስለዚህ ነገር የሚነግርህ እጅግ ያማረ አገላለጽ አለው፡፡ «አዲስ ችግኝ በውሃ ሕይወት የሚያገኘውን ያህል ገድለ ቅዱሳንም ለክርስቲያን ሕይወት የሚሠጥ ጣፋጭ ምግብ ነው፡፡»

በእርግጥም ማንም ያለእርሱ ምንም መሥራት የማይችልበት መንፈሳዊ ምግብ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርሰውን መንገድ እንድናገኝ የሚመራን፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ጠለቅ ብለን እንድናስብ የሚያደርገንም ነው፡፡ ከዚህም በላይ የሥነ ምግባር ሰዎች

መሆንን እንድንመርጥና፣ እነዚህን የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ አባትና እናት አማላጆቻችን እንድንቀበላቸው የሚያደርግም ነው:: ከቅዱሳኑ ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጠናከር እንድንነሳሳ፣ ልክ እንደ እኛ በምድር አብረውን ያሉ እየመሰለን ከእነርሱ ጋር እንድንነጋገር እንድንጠራቸው የሚያስችል እግዚአብሔርን የማመስገኛ መንገድ ነው::

ለቅድስና ሕይወታቸውና ለእነርሱ ካለን ፍቅር የተነሳ አንዳንዴ ራሳችንን በስማቸው እንሰይማለን:: ዛሬ እግዚአብሔር የተመሠገነ ይሁንና ብዙ ክርስቲያኖች በቅዱሳን ስም ይጠራሉ:: በፍቅራቸውና በሥነ ምግባራቸው ተስበው እንዲያድጉ ለልጆቻችንም መጠሪያ ብናደርግላቸው ጠቀሜታው የጎላ ነው:: ይህም ሁሉ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የገለጸውን ድንቅ ሥራ ለማድነቅና ለእኛም ይደረግልናል በሚል ተስፋ የምናደርገው ነው:: ለቅድስና ሕይወት ያለንን ታላቅ ክብር ለመግለፅ እና በቅዱሳን ስም ላይ ያለውን የእግዚአብሔር በረከት በማመን በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መነኮሳት ምንኩስናን ሲቀበሉ አብረው የሚቀበሉት የእነዚህን ቅዱሳን አባቶች ስም ነው::

እኛስ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እድገት ከቅዱሳን ያገኘነው ምንድን ነው?

1. **አርአያነት**

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ:: የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው» (ዕብ 13:7):: ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው በፊታችን የተዘረጋ ሠፊ ፕሮግራም አለ:: ማንም ለመያዝ ለፈለገው የትኛውም መልካም ሥነ ምግባር፣ የፈለገውን ወደሚያገኝበት የሚመሩትና በተግባር እያሳዩ፣እንደመልካም እጣን በቅድስና መዓዛ እየሳቡ የሚያደርሱት ብዙ ቅድሳንን በፊቱ ያገኛል:: በዘመንህ፣ በችሎታህ ሁሉ ክርስቶስን የመሠሉትን ቅዱሳን ምሳሌ አድርግ (1 ቆሮ 11:1)::

ለምሳሌ የሰማዕትነት ሕይወት ለእኛ እንደዚህ በቀላሉ የምናገኘው ላይሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ በእምነታቸው ጥንካሬ በትዕግስታቸው፣





በጽናታቸው፣ ለዘላዓለማዊ ሕይወት በነበራቸው ዝግጁነት፣ ዓለምንና ንብረቱን በመጥላታቸው ሰማዕታትን እየተከተልን መጓዝ እንችላለን::

እንደ ቅዱስ አባታችን አባ ተክለሃይማኖት፣ ቅዱስ ገብረመንፈስ ቅዱስ እንደ ቅዱስ መቃርዮስ ዘእሥክንድርያ ባለማቋረጥ መጸለይ ያቅተን ይሆናል:: ቢሆንም ቢያንስ ለጸሎት ያለን ፍቅር እንዲጨምርና ያለንበት ደረጃ በሚፈቅድልን መጠን እየጸለይን ለመቀጠል እንድንናፍቅ ያደርጉናል:: በበረሃ የነበሩት ቅዱሳን የሕይወት መንገዳቸው በዓለም ካለነው ከእኛ የአኗኗር ዘይቤ እጅግ የተለየ መሆኑን ማወቅ አለብህ:: ስለዚህ ሕይወትህን ለአደጋ እስከመዳረግ ድረስ በመጾም እነርሱን ለመምሠል መሞከር የለብህም:: ቅዱሳኑ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ ዓመታትን በመንፈሳዊ ተጋድሎ በትዕግስት ሕይወት አሳልፈው ጽናትንና ብርታትን አግኝተው ነው::

ስለዚህ በእምነት በምግባር ልትመስላቸው ስትሞክር በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አመራር ሥር ሆነህና ጥበብ የተመላበት አካሄድህን እለት በእለት እያሻሻልክ ይሁን:: ሁላችን ልናገኛቸው የሚቻለን መንፈሳዊ ሥነ ምግባራትም አሉ:: ለምሳሌ ትሕትና፣ ቅንነት፣ ራስን መግዛት፣ ሌሎችን መርዳት፣ መታገስ፣ ከቁጣ መራቅና የመሳሰሉትን ማዳበር እንችላለን:: (ገላ 5:22):: ፍጹም ዝምታ የሚስማማህና የሚመችህ ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን ከዝምታህ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ መናገርን፣ ገንቢና ጠቃሚ የሆኑ ቃላትን ብቻ መርጠ መጠቀምን ትማራለህ::

ከአቅምህ በላይ የሆነውንና ለአንተ ደረጃ የማይስማማውን በጎ ነገር ቢሆንም እንኳ ለመምሠል አትሞክር:: ይህ ማለት ሙሉ ለሙሉ አይቻለኝም ብለህ ወይንም ተስፋ ቆርጠህ ተወው ማለት አይደለም:: ነገር ግን የሚመራህ ባለበት የምትችለውን ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ይዘህ እደግ ማለት ነው:: (2 ጴጥ 3:18)::

በጎ ምግባራትን ውስጣዊና መንፈሳዊ የሆነ ዋጋቸውን እንጂ ለይስሙላ ወይም ለታይታ በሚሆን መልኩ ብቻ አትውሰዳቸው:: ለምሳሌ በንስሐ የተመለሱ አባቶችን ታሪክ ስታነብ ልክ እንደእነርሱ ጳግም ወደኃጠ

ሕት የማትመለስበት ፍጹም ከልብ የመነጨ ንስሐ ለመግባት ወስን! በጾጾት የተሰበረ ልብና በእንባ የረጠቡ ዐይኖች እንዲኖሩህ አባቶችህን ምሳሌ አድርግ:: ገድላቸውንም ስታነብ ቃል በቃል ብቻ የሚሠጥህን ስሜት ብቻ ይዘህ እነሙሴ ጸሊም፣ አውግስጢኖስ እንዳደረጉት ለንስሐ የግድ ገዳማዊ መሆን እንዳለብህ አስብህ አታፈግፍግ:: በደረጃህ ጀምር:: ንስሓ የሚገባ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር፣ እንዴት መመለስ መቻሉን፣ ጾጾቱን፣ ኃጢአት መጥላቱን እንደምሳሌ ውሰድ:: ነገር ግን በመጠንህ በችሎታህ በተሰጠህ ጸጋ መኖርን አትርሳ::

## 2. እምነት ማጠንከር

ጠንካራ እምነት ሊመጣ የሚችለው የእምነት ጀግኖች አባቶቻችን የሠፉትን አብነት በማድረግ ነው:: እስከሞት ድረስ ለሃይማኖት የታመኑ ሲሆኑ፣ በጾም በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ፣ የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ በትዕግስትና በደስታ ሲቀበሉ፣ ስናነብ የምናገኘው እጅግ ብዙ ነው:: ባላቸው ኃይልና ዕውቀት ሁሉ ቤተክርስቲያንን ጠብቀዋል:: በዚህ ምክንያት ለሚመጣባቸውም ምንም ዓይነት መከራ ጽኑዎች ሆነው በግዞት በእሥር ቤት ፈጣሪያቸውን እያመሠገኑ ኖረዋል:: ቤት አልባ ሆነው ማረፊያ እንዳጡ በስደት በየሀገሩ ተንከራተዋል:: ለምሳሌ ቅዱስ አትናቴዎስን ብንመለከት አራት ጊዜ ከፓትርያርክነት መንበሩ ተሰዷል:: በጣም አስፈሪ የነበሩ ክሶችን ሲከሰስ፣ ሲፈረድበት ብሎም «አትናቴዎስ አንተን ዓለም ሁሉ ጠልቶሃል» ሲሉት «እኔም ዓለምን ጠልቼዋለሁ» ብሎ ነበር የመለሰላቸው::

ስለዚህ ቅዱሳንን የናቀ ያ ትውልድም ሆነ የዛሬው የተነቀፈ መሆኑን እንረዳለን:: ምክንያቱም ይህ ሁሉ መሥዋዕትነት የተከፈለበት ሃይማኖቱን የሚመለከተው በግድ የለሽነት ነው:: ያለፈውን ተጋድሎ ረስቶ ስለእምነት ወይም ስለሃይማኖት ልዩነቶች ምንም ማሰብና መጨነቅ አይፈልግም:: በአባቶቻችን ዘመን ለእያንዳንዷ የሃይማኖት ነጥብ ብሔራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት ይጠሩ ነበር:: በዚህም ላይ ቅዱሳን ሃይማኖታቸው እንዲጠበቅ፣ ትክክለኛው መሠረታዊ ትምህርት እንዲታወቅ ድንቅ የሆነ ሚና ተጫውተዋል:: የሚያገኙት ግላዊ ጥቅም ሳይኖር፣ በግል





የሚጎዱበትም ነገር ሳይኖር ምንቸገረኝ ያሉበት አንድም ጊዜ የለም:: ክርስትና ፍቅር ነውና ቅዱሳንም በፍቅር ውስጥ ስላሉ ሁሉ ነገር ያሳስባቸዋል:: የሌላው ጭንቀት ጭንቀታቸው ችግሩ ችግራቸው ሆኖ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሲሉ ሕይወታቸውን ለመስዋዕትነት አቅርበው ያለእረፍትና ያለመሰልቸት ሠርተዋል::

ዛሬ ግን በጋብቻ ወይም በፍቺ ሃይማኖት በቀላሉ ይቀየራል:: በግድየለሽነት ወይም ባለማወቅ ከቤተክርስቲያን አገልጋዮችና አባላት ባለመስማማት ብቻ ቤተክርስቲያንና ትምህርቷን ጥሎ የሚወጣው እጅግ ብዙ ነው:: ቅዱሳን ለሃይማኖታቸው ምን ያህል እንደተጋደሉ ለእርሱ ግድ አይሰጠውም:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! በነፍስህ ጽናትንና እምነትን ለመትከል እና የማይናወጥ የማይከፋፈል ክርስቲያን ለመሆን የቅዱሳንን ሕይወት የሚናገሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት ማንበብ ያስፈልግሃል::

ቤተ ክርስቲያን በእውነተኛ ሃይማኖት ጥላ ሥር የተሰበሰቡና ትክክለኛውን ትምህርቷን የሚከተሉ ሰዎች ማህበር እንጂ የወገን ወይንም የወገናዊነት መሰባሰቢያ አይደለችም:: በየዘመናቱ ቅዱሳን ስማዕታት የተሠቃዩበት፣የተገረፉበት፣ የተሠየፉበት ምክንያት ሃይማኖት እንጂ ሌላ እንዳልነበረ አስተውል:: ይህን ደግሞ በየገድሎቻቸው ተጽፎ ምስክር ሆኖ እናገኘዋለን::

## 3. የትሕትናና የተሠበረ መንፈስን በውስጣችን መትከል

ቅዱሳን የነበሩበትን ፍጹም መንፈሳዊ ደረጃ ከየገድሎቻቸው ላይ በምናነብበት ጊዜ የሚሰማን ስሜት ትሕትና እና ከእነርሱ አንጻር እኛ ምንም እንዳልሆንን ነው::

ለምሳሌ የጻድቁ አባት የአባ አብራምን ሕይወትና የለጋስነት ጸጋውን ስታነብ ልብህ አልተሠበረም? አባ አብራም ለራሱ ምንም ሳይስቀር ያለውን ሁሉ የሰጠ የመጸወተ ቸር አባት ነው:: ከዚህም በላይ ሰው ለእርሱ የሠጠውን ሁሉ መልሶ ለድሆች የሚሠጥ ነበር:: ያለውን ሁሉ ሸጦ ለነዳያን የሰጠውን አባ ዮሐንስን ስታስብ ምን ትለለህ? ንብረቱ ሀብቱ ቢያልቅበት እንኳን ራሱን እንደባሪያ ሸጦ ዋጋውን ለድሆች የሰጠ ሰው ይህ ቸሩ አባ

ዮሐንስ (ዮሐንስ ሐጺር) ነው። ታዲያ እነዚህን የእግዚአብሔር ሰዎች ታሪካቸውን እያነበብክ ስታስባቸው ራስህን እንዴት ትመለከታለህ? ገና ብዙ እድገት እንደሚቀርህና እዚያ ለመድረስ የምትድህ ከሆነ ትሕትና በውስጥህ የሚያድግበትን መንገድ አገኘህ ማለት ነው።

ጠላትህ ዲያብሎስ ራስን ከፍ ከፍ በማድረግና በትዕቢት ቢፈትንህ እንኳን የቅዱሳንን ሕይወት ስታውቅ ድካምህ ከነፍስህ ይወገዳል። አንዳንዴ የራስህ ሀሳብ አገልግሎትህን ትልቅ አድርጎ በማሳየትና ከማንም በላይ ከደከመው ከቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት ጋር በማነጻጸር ይዋጋሃል። (1 ቆሮ 15:10)። ይሁን እንጂ ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም፣ በአንጾኪያ፣ በታናሽ እስያ፣ በግሪክ እና ሮም እንደሰበከ እንዲሁም እስከ ስፔይን እንደደረሰ፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ አብያተ ክርስቲያናትን በአንድ መሠረት ላይ እንደመሠረተ፣ በቃላት ሊገለጹ የማይችሉ ስቃይ መከራዎችን እንዳለፈ (2 ቆሮ 11) በእስር ቤት እንኳ ሳለ መልእክታትን ይጽፍ እንደነበረ፣ (ኤፌ 4:1) ስታነብና ስታስብ ውስጥህ በጸጸት አይኮማተርም? እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ ገድለ ቅዱሳን የትሕትና ምንጭ ይሆናል።

አሁን ባለህበት ደረጃ ምንም ያህል ትሑት ብትሆን ከቅዱሳን የፍጹምነት ደረጃ ጋር የምትነጻጸር አትሆንም። እነርሱ ይህን ሁሉ የቅድስና ሕይወት ይዘው በዚህ ሳይመኩ ዘወትር ስለኃጢአታቸው የሚያለቅሱ ናቸውና። ቅዱስ አርሳንዮስ ፀሐይ ለመጥለቅ ስታዘቀዝቅ ጀርባውን ሰጥቷት ወደምስራቅ ዞሮ ለጸሎት ይቆማል። ጸሎቱን ሳያቋርጥ እንደገና ፀሐይ ከፊት ለፊቱ እስክምትወጣ ድረስ ይጸልያል። ገድሉ እንደሚነግረን በእንባ ብዛት ቅንድቦቹ የረገፉና፣ ሽፋሽፍቶቹ የተላላጡ ነበረ።

ከእንባው ብዛት ቆሞ የሚጸልይበትን የዘንባባ ዛፍ ያረጥበው ነበር። እና የቱን ያህል ትሕትና ቢኖርህ ነው ከእነዚህ አባቶች ጋር የምትነጻጸረው።

የአስቄጥስን ገዳም የመሠረተው ቅዱስ አባ መቃርዮስ በሌላ ገዳም ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ሁለት አባቶች ባየ ጊዜ «እኔ መነኩሴ አይደለሁም፣ ግን እውነተኛ መነኮሳትን አየሁ» ነበር ያለው። እንግዲህ ራስህን ከሌሎች እያነጻጸርክ የተሻልክና የተከበርክ አድርገህ በመቁጠር በራስህ መፈተንህን





አቁም! ምክንያቱም ቅዱሳንና የሃይማኖት ተጋድሎአቸውን ብታውቅ የምትናገረው አይኖርህም። አሁን የምትረዳው ነገር ቢኖር በቤተ ክርስቲያን ጥላ ስር ማደግ እንዳለብህና ክርስቶስን የመሰሉትን ቅዱሳን በእውነት መምሠል እንዳለብህ ነው። «ወደእግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» (ሐዋ 14:21)።

## 4. ጥበብና ማስተዋል

ከቅዱሳን ሕይወት ተምረን የምናተርፈው 4ኛው ነገር የጥበብና የማስተዋል መንፈስን ነው። መከተል ያለብንንም ትክክለኛ መንገድ ያሳየናል። መጽሐፍ ቅዱስ ዳዊት የመሠዊያ ቦታ ለመግዛት በፈለገ ጊዜ የተናገረውን ጥበብ የተመላበት አነጋገር ያስነብብሃል። ኢያቡሳዊው ኦርናን ሁሉን ነገር ለዳዊት በነፃ ሊሠጠው ተስማምቶ ነበር። ይሁን እንጂ ዳዊት በጥበብ «እንዲህ አይደለም፣ ነገር ግን በዋጋ ከአንተ እገዛለሁ። ለአምላኬም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መስዋዕት ያለዋጋ አላቀርብም።» (2 ሳሙ 24:24) ብሎ እንደመለሠለት እናያለን። ሌላኛው ጥበብን የሚያስተምርህ አቢግያን ዳዊትን ከቁጣ ለመመለስና ለማስማማት የተጠቀመችበት ጥበብ ነው።(1 ሳሙ 25:23-35)

በወጣትነት ዘመናቸው በየበረሃው፣ በየጫካው ይንከራተቱ የነበሩ የእነ ዮሐንስ ሐጺር፣ የእነታድሮስ የቅድስና ሕይወትም ብዙ ጥበቦችን ሊያስተምርህ ይችላል። ከአረጋውያኑም አባ አጋቶን፣ አባ ኤስድሮን የመሳሰሉትን ብትመለከት ብዙ መማር ትችላለህ።

የአባቶቻችን መንፈሳዊ ጥበብ ሊማርበት ለሚወድ ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ነው።

## 5. የማያቋርጥ መንፈሳዊ እድገት

ከገድለ ቅዱሳን የምናገኘው ሌላው ጠቃሚ ነገር የማያቋርጥ መንፈሳዊ እድገት ነው። ምንም የሚገታው የሌለ፣ ሥጋን የሚገሉ የክርስትና ጠላቶች የማይገድሉት፣ መንፈሳዊ እድገታቸው ሁሌ ወደላይ የሚያድግ ነው። ከሥጦታው ሁሉ ጋር የቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት

እንዲሁም እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የመነጠቅ ብቃቱ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል:: እርሱ ግን እንዲህ ነበር ያለው::

«አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንኩ አይደለም:: ነገር ግን ስለእርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ:: ወንድሞቼ ሆይ ገና እንዳልያዝኩት እቆጥራለሁ:: ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ:: በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያሏውን ለመያዝ እዘረጋለሁ:: በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ::» (ፊልጵ 3:12)::

ቅዱሳን በደግነት፣ በጥሩ ምግባር የደረሱበት ከፍተኛ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃ አንተን ዛሬ ባለህበት እንዳትታበይ፣ ለሚበልጠው እንድትጥርና እድገትህ እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው:: በፊትህ ያለው መንገድ ረጅም ነው:: ነገር ግን የሚሠጥህን ጸጋ በእጅህ ልትቀበለው የቀረበ በመሆኑ ቅዱሳንን እግር በእግር እየተከተልክ በመከራ፣ በፈተና ውስጥ እንኳ ቢሆን በቁርጠኝነት ማለፍ እንድትችል ያበረታሃል::

የቅዱሳን ሕይወት የማይጠፋና ሊጨቁኑት የማይቻል የጋለ መንፈሳዊ ስሜትን የሚሰጥ ነው::

ከእነዚህ በተጨማሪ ገድለ ቅዱሳን በሌሎችም በተለያዩ መንገዶች በአንተ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖዎችን ማሳደር ይችላል::

የንስሓ ሕይወትህ ፍጹምና ትክክል እንዲሆንና፣ በውስጥህም ያለውን ጉድለት በጽድቅ ፍሬዎች ለመሙላት ምን ማድረግ እንዳለብህ ከቅዱሳን ትማራለህ::

በፍጹም ወዳጅነት፣ በትሕትናና፣ በፍቅር ይጸልዩት የነበረውን ጸሎታቸውን ከገድላቸው ስታነብ እንዴት መጸለይ እንዳለብህ ታውቃለህ ::

ሰዎች በመንፈሳዊ ጦርነት በነበሩበት ጊዜና ድል አድራጊዎች በሆኑበት ጊዜ እንዴት አብረህ መኖር እንደምትችል፣ ችግረኞችን እንዴት መንከባከብ እንዳለብህ ታይበታለህ::





የቅዱሳንን ሕይወት በመጽሐፋቸው ውስጥ ስትመለከት፣ በአነጋገርህ፣ ስለሰዎች ባለህ አስተሳሰብና፣ በአጠቃላይ በነገር ሁሉ የማያቋርጥ መሻሻል እያደረግህ ነው::

እባክህ ይህን ልምድ በውስጥህ እንዲያድግ ፍቀድለት?

እስከአሁን ያልኩህ ሁሉ የምሳሌ ያህል እንጂ ምሉዕ የሆነ ነገረ ቅዱሳን እንዲህ በቀላሉ የሚደፈር አይደለም:: ራሱን ችሉ እንኳን ቢቀርብ መጽሐፍ አሊያም መጻሕፍት የሚያስፈልገው ነው::

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ሆይ:- የቅዱሳንን ሕይወት እንድትጠቀምበት ይህን ሠፊ የተመስጦ ውቅያኖስ ለአንተ መተውን መርጫለሁ:: ምክንያቱም ይህ ጉዳይ ማናቸውንም የመንፈሳዊ ሕይወት እንቅስቃሴዎች የሚዳስስ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውምና ነው::

## ምዕራፍ ፬

### ተመስጦ

**ተመስጦ ምን ማለት ነው?**

አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ተመሰጠ ሲባል:- ይህ ሰው ነገሩን በቅርበት እየመረመረ፣ እያጠናው፣ እየፈተሸው፣ ጥልቀቱን ለማየት እየተነተነው ነው ማለት ነው::

ተመስጦ ማለት በሀሳብ ወይንም በመንፈስ ወደ ጥልቁ ምሥጢር መነጠቅ ማለት ነው:: ይህም ከተለመደው የዕውቀት ዓይነት ወደከፍተኛው ደረጃ መድረስ ነው:: ዕውቀቱም ከስሜት በላይ የሆነና ሁሌ አዲስ የሚሆን የመንፈስ ተድላና ደስታ ነው:: በዚህ ዕውቀት ውስጥ መንፈሳዊ ምግብና ደስታ አለ::

ተመስጦ፣ አእምሮን፣ ልብና መንፈስን ከላይ ብቻ የሚገኘውን አምላካዊ ዕውቀት ለመቀበል ማዘጋጀት ማለት ነው:: ወይንም በውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለማነሳሳት መፍቀድ ማለት ነው::

ለተመስጦ ፀጥታ፣ እርጋታ፣ ስሜትን መግዛትና መንፈስን ከሚያውኩ ማናቸውም ነገሮች መታቀብ አስፈላጊዎች ናቸው::

የሰው ስሜት ከውጪያዊ ሁከቶች ነፃ ሲሆን፣ ከሥጋዊ ሀሳብ ሲላቀቅና፣ ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ራሱን ሲያዘጋጅ ተመስጦው ጥልቅና ስኬታማ ይሆናል::

ለተመስጦ ስኬት የሚረዳው አንድን ነገር ለማወቅ ያለህ ፍላጎትና አምላካዊ ነገር ላይ ማተኮር ነው::

በመቀጠል በዝርዝር ልናያቸው የሚያስፈልጉ ብዙ የተመስጦ ክፍሎች አሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በመዝሙር፣ በዜማ ተመስጦ ሊመጣ ይችላል:: ወይም በሥነ ፍጥረት ውበትና ጥበብ፣ በሰማያትና በመላእክት፣ በሞት፣ በፍርድና ከዚያ በኋላ ባሉ ሁኔታዎች መነሻነት ሊጀምር ይችላል:: በድርጊቶች፣ በቅዱሳን ሕይወት፣ በውሱን ወይም በአጠቃላይ ሥነምግባሮች፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት የሚመጣም ሊሆን ይችላል:: ሌላ ታላቅ የሆነና





በእግዚአብሔር ድንቅ ባህርያት ለምሳሌ ወሰንየለሽነቱን፣ እውነተኛነቱን፣ ጸጋውን በማሰብ መመሰጥም አለ:: በአጠቃላይ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: የሚጠቅሙትን መንፈሳዊ ነገሮች ለመምረጥ በቁሳዊ ነገሮች ላይ እንኳን ሰው ሊመሠጥ ይችላል::

### የተመስጦ ዓለሞች

#### መጽሐፍ ቅዱስ

በእግዚአብሔር አነሳሽነት የተነገሩና የተጻፉት ቃላት መንፈስ የሆኑና በትምህርት በአካል ገዝፈው የሚታዩ ናቸው:: ፊደሎቹ ሳይሆኑ በውስጣቸው ያለው መንፈስ ደግሞ ሕይወት የሚሰጥ ነው:: (2 ቆሮ 3:6):: ለዚህ ነው ጌታችንም «ሕይወትን የሚሠጥ መንፈስ ነው» ሲል የተናገረው:: (ዮሐ 6:63)::

በውስጡ ሉል /የባህር ዕንቁ/ እንዳለው ቅርፊት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትም ጥልቅ የሆነ ምሥጢርን በውስጣቸው ያመቁ ናቸው:: ዕንቁው የቃላቱ መንፈስ ነው:: ስለዚህ በቃላቱ ወይም በቅርፊቱ ብቻ አትርካ:: ሽፋኑን ገላልጠህ ውስጣዊውን ሉል ውሰድ:: ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነትና እንደ ቅዱስ ዳዊት «ዓይኖቼን ክፈት፣ ከሕግህም ተዓምራትን አያለሁ» እያልክ በምትጸልየው ጸሎት ነው:: (መዝ 118:18) ወይም «አቤቱ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን እባክህ ግለፅ» ብሎ ስለ ደቀመዝሙሩ ግያዝ እንደጸለየው ዐይኖቹን እንዳስገለጠለት ኤልሳዕ በቅዱሳን የምልጃ ጸሎት የሚገኝ ነው:: (2 ነገ 6:17)::

ተመስጦ በመንፈስ ቅዱስ ግብር የሚመጣ የአእምሮ ብሩህነት ነው:: በዚህ ብርሃን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት ሽፋናቸውን ገልጦ ምሥጢሩን መፈለግና በጥልቀት መረዳት ይቻላል:: ይህም ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመመሰጥ በእግዚአብሔር ገላጭነት የተቀመጠውን አምላካዊ እውነት ለማግኘት መጣር ነው:: «በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው::» (ሉቃ 24:45)::

በእውነት አምላክ ሆይ በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን:: አእምሮአችንን፣ ልባችንንና ሀሳባችንን እንዲያበራልን ከዚያም ተነስተን

«መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት» የሚለውን ማስተዋል እንድንችል እንፈልጋለን። (ራዕ 2)

እንደዚሁ አንተም በሀሳብህ፣ በልብህ፣ በመንፈስ የምታደርገውን ጥረት ሁሉ አእምሮህ ብሩህ ሆኖ አባቶችህ የተቀበሉትን ለመቀበል የበቃህ ያደርግህ ዘንድ እንደምታቀርበው ጸሎት የሚቆጠር ነው። የአንተ ሥራ አእምሮህን ዝግጁ አድርገህ እግዚአብሔር ከጥልቁ ዕውቀትና ከማስተዋሉ እንዲሞላበት ማቅረብ ነው። ማድረግም ያለብህ ልብህን መክፈትና ጌታ ገብቶ ከአንተ ጋር እራት እንዲበላ መፍቀድ ነው። (ራዕ 3:20)። አዎን አንተ እና እኔ ከሰማይ ከወረደው ሕብስት ጋር እንበላለን። (ዮሐ 6:33)። በዚህ የሕይወት ሕብስትና ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃል መኖር እንችላለን። (ማቴ 4:4)

በተመስጦ ውስጥ ሕሊናህ የተጓዘው የመጀመሪያው እርምጃ ለመንፈስ ቅዱስ በር የመክፈት ያህል የሚቆጠር እርምጃ ነው።

ለዚህ ነው አባቶች ተመስጦን በጥልቀት እየተመለከቱ፦ «ከሰዎች ጥረት በላይ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ» የሚሉት። ቅዱስ ዳዊትም የሚለው ይህንኑ ነው። «አፌን ከፈትሁ፣ አለከለክሁም። ወደትእዛዝህ ናፍቄአለሁና» (መዝ 118:131)።

ተመስጦ በመንፈስ ቅዱስ የሚሠጥ የጥናት ክፍለ ጊዜ ነው። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ ሊሰጥህ የወደደውን እንዴት መቀበል እንደምትችል የምትለማመድበት መንገድ ነው።

ተመስጦ አእምሮ አንድን ነገር ለመረዳት /ለማወቅ/ ከሚያደርገው ጥረት በላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚናገረው በዕውቀትና በችሎታ መደገፍም አይደለም። «በራስህ ማስተዋል አትደገፍ» (ምሳ 3:5)

ዕውቀትንና ፍልስፍናን ሊያመጣ የሚችለው ምሁራዊ አስተሳሰብ እንኳን ቢሆን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሌለበት ተመስጦን ሊያመጣ አይችልም። በምሁርና በእምልኮ ውስጥ ባለ ሰው መካከል ሠፊ ልዩነት አለ። በሚያጠናና በሚመሠጥ፣ መጻሕፍትን በሚመረምርና ከመንፈስ ቅዱስ በሚቀበል ሰው መካከልም እንደዚሁ ልዩነት አለ። ተመስጦ ሀሳብ ብቻ





አይደለም። ሀሳብን ከልብ ጋር አዋህዶ ልብን እንደመሳሪያ በመንፈስ እጅ መተውና ከእግዚአብሔር መንፈስ ለመቀበል መቃተት ነው። በዚያን ጊዜ በመንፈስ ቁንካሬን ያገኘውን የቃሉን ጠንካራነት እንገነዘባለን። ከዚህ በኋላ ወንድሜ ሆይ ትክክለኛው የአእምሮ ደረጃ ላይ ደረስኩ ብለህ እንዳትቆም። ነገር ግን ሕሊናህን መንፈስ ጋር የመድረሻ መንገድ አድርገው። መንፈስም የዕውቀት ሀብቶች ሁሉ ወዳለው ወደእግዚአብሔር ስለሚመራህ እርሱ ሁሉን ይሰጥሃል።

ንባቡ ውጪያዊ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ሰው ያለተመስጦ ብዙ ሊያነብ ይችላል። መንፈሳዊው አንባቢ ግን ባነበባት ትንሽ ነገር የማይነጥፍ የተመስጦ ምንጭ ሊኖረው ይችላል። ባነበበው ላይ ይመሰጣል እንጂ ብዙ ስለማንበብ አይጨነቅም።

ቃልም ሆነ አገላለጽ በእጅጉ ስለሚስቡት በዚያው ወደጥልቁ ገብቶ ሲመረምር ይቆያል። «የሥራን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ ትእዛዝህ ግን እጅግ ሠፊ ነው።» እያለ ከዳዊት ጋር ያመሠግናል። (መዝ 118:96)። እግዚአብሔርም ልቡን ይከፍትለትና በአንዲት ቃል ምንም ያህል ቢወስድለት የማያልቅ ትልቅ ሀብትን ያያል። አሁንም በዚህ ከነቢዩ ጋር ደስ ይለዋል (ሐሴትን ያደርጋል።) «ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ» (መዝ 118:162)።

እንደመንፈሳዊው ልምምድ በቀን ቢያንስ አንድ ጥቅስ ለተመስጦ እንዲሆንህ ውሰድ። ስታነበው ከዚህ በፊት ምንም የልነካህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አገናዝብ። በዚህ ሳትገደብ በዝግታ እያጠናኸው እንደዓለመ ተመስጦ ውሰደው። በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ለሚሰጥህ ነገር እድል ስጥ። ወይንም አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ታሪክ ውሰድና እንደዓለመ ተመስጦ ተጠቀምበት።

እግዚአብሔር ለሰዎች የሚያደርገው ልዩ እንክብካቤም ሠፊ የተመስጦ ዓለም ነው።

እግዚአብሔር የሚወዳቸውን እነርሱም በፍጹም ወዳጅነት የሚያፈቅሩትን ከእርሱ ጋር የጠለቀ ሕብረት የነበራቸውን ቅዱሳኑን አስብ። ወይም በቸርነቱ በትዕግስቱ መጠን የተንከባከባቸውን በዚህ ተጠቅመው

ንስሐ የገቡ ኃጥአንን አስብ፡፡ ሌሎች ልባቸው የደነደነ በቅንነቱ ያልተጠቀሙትንም እንዴት ይጠብቃቸው እንደነበረ አስታውስ፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችም ሊመስጡህ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጥቅሶችን ማስታወስ መቻልም ሌላው ለተመስጦ የሚያነሳሳህ ነገር ነው፡፡ እርስ በእርሳቸው እየተፈጸሙና እየተሟሉ ተመስጦ በጀመርክበት ጊዜ ሁሉ ጥቅሶችን ታገኛቸዋለህ፡፡ እያንዳንዱ ቃል ልዩ ትርጉም ይሰጥሃል፡፡ ሁሉም የተመስጦን እቅፍ አበባ ያበረክቱልሃል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘህ «መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል አስታውስ (1ቆሮ 2፡13)፡፡

ይህን ብታደርግ ሙሉውን ቀን በመንፈሳዊ ሀሳብ ብቻ ትይዘዋለህ፡፡ እነዚህ መንፈሳዊ ሀሳቦች ውስጥህን ሰርስረው ይገቡና ንጹሕ ሀሳብህ ንጽሕናን ይወልዳል፡፡ ልብህ በተመስጦ የተመላ እና ንጹሕ የእግዚአብሔር ቃል የሚሠራበት ይሆናል፡፡ ተመስጦህ በራሱ በጸሎትህ ሰዓት እያጀበህ ከሰዎች ጋር እንኳን እያወራህ ባለህበት ሰዓት ወደቀናው ሊመራህ ኃይል ያገኛል፡፡ አድማጮችህም ግብዝነት የሌለው ጥልቅ የሆነ ነገርህን ሁሉ ይረዱልሃል፡፡

ተመስጦ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬም ይጠቅማል፡፡ ተመስጦ በሀሳብ፣ በመንፈሳዊ ስሜት፣ በውስጣዊ እርካታ፣ በዕውቀት፣ በደስታ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ወደሕይወትህ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችም የማደግ ባህርይ አለው፡፡ ስለዚህ የምታነበው መጽሐፍ ቅዱስም ይሁን የቤተክርስቲያን አባቶች ታሪክ /ገድል/፣ ራስህን በማንበብና በመመሠጥ ላይ ብቻ አትወስን፡፡ የነበብከውን ሁሉ ከሀሳብህ፣ ከልብህ ጋር አዋህደህ በተግባር አውለው፡፡

ተመስጦን ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ሕብረትና ከሰዎች ጋር ያለህን ግንኙነት የምታሻሽለበት መንገድ አድርገህ አስበውና በመንገዱ ለመጓዝ ራስህን አመቻች፡፡ የምታነበው ሁሉ በጸሎት የተደገፈ ይሁን፡፡ «ዐይኖቼን ክፈት ከሕግህም ተዓምራትን አያለሁ፡፡» (መዝ 118፡18) እንዳለ ዳዊት ተመስጦ አምላካዊ ገላጭነትን ይፈልጋል፡፡ አንዳንዴ ሰው





እግዚአብሔር በገለጸለት ምሥጢር ተገርሞ ሲያነበው ከዚህ በፊት ያላገኛቸው አዳዲስ ትምህርቶችንና ቀድሞ ሕሊናውን ያልሰቀሉትን ልዩ ምስጢራት ያገኛል፡፡

መዝሙረ ዳዊትን ስታነብ ወይም ስትጸልይ ይህን የመሠለ ነገር ያጋጥምሀል፡፡ ዘወትር በምትጸልየው ጸሎት ውስጥ በየዕለቱ አዲስ የሆነና ከዚያ በፊት ያላገኘኸው አምላካዊ ምሥጢር ሊገለጽልህ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር በሕሊናህ ውስጥ የሚበራ የብርሃን መስኮት ለአንተ ይከፍትልሃል፡፡ ይህ ብርሃን በአንተ ዕውቀትና የአእምሮ ብቃት የመጣ እንዳይመስልህ፡፡ ተመስጠህ ስታነብና ስትጸልይ እግዚአብሔር በአንተ ላይ ያዘነበው የማያልቀው ስጦታው ክፍል እንደሆነ እወቅ፡፡ ጸሎት የተመስጦ ምንጭ ይሆንህና እራሱ በተመስጦ ይታጀባል፡፡ በዚህ ዓይነት ጸሎት ውስጥ ቃላት ሁሉ ሠፊና ወሠን የለሽ ጥልቅ ምሥጢርን የያዙ መሆናቸው በየዕለቱ ይታያል፡፡

የተመስጦ ልምድ ወይም ጸጋ ከሌለህ የቅዱሳን አባቶችን የተመስጦ ሕይወት የሚናገሩ መጻሕፍትን አንብብ፡፡ ታላቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በማቴዎስ ወንጌል፣ በዮሐንስ ወንጌል፣ በሐዋርያት ሥራና በአሥራ አራቱ የጳውሎስ መልእክታት ላይ እጅግ ብዙ የአንድምታ መጻህፍትን ጽፏል፡፡ እነዚህ ሁሉ ተመስጦና ማብራሪያን የተመሉ ናቸው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍቱን በተመስጦ ያብራራበትን ያስተማረበትን ብሎም የተማረበትን መንገድ መርምርና ተከተለው፡፡

እንደዚሁ ከሌሎችም ቅዱሳንና ከሥራዎቻቸው ጋር ቆይታ አድርግ፡፡ በተለይም በዚህ በትምህርታቸው ጥልቀት ብቻ ሳይሆን በተመስጦ እውቅና ካላቸው እንደማር ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ከመሳሰሉት አባቶች ብዙ ተማር፡፡ ሥራዎቻቸውን እያነበብክ እንደተመሥጦ ትምህርት ቤት ተጠቀምበት፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌያዊ ጽሑፎች ላይ ልዩ ተመስጦ የነበራቸውን አባቶች ሕይወት ለማንበብ ራስህን አለማምድ፡፡ ምሳሌያትን ማንበብ፣ የነቢያትን መጽሐፍ፣ የሰሎሞንን መኃልየ ለመረዳት በጣም ጠ

ቃሚ ነው:: የመሥዋዕቱን የስእለቱን፣ የበዓላቱን፣ በርኩሰትና በመንጻት መካከል ያሉትን ሕግጋት ሁሉ ሊመጣው ያለው ነገር ጥላ መሆን ለመረዳት ያስችልሀል (ቆላስ 2:17)

ምንም ጥቅም በሌላቸው ሁከትና ጭንቀት በበዛባቸው ተራ ነገሮች እንዳትጠመድና በመልካምና ጠቃሚ በሆኑ ነገሮች የተከበብክ እንድትሆን ተመስጦን በተግባር ልመደው:: ጥሩም ይሁን መጥፎ ባቀረብክለት ነገር ይወሰን እንጂ፤ አእምሮህ ለተመስጦ ፈጣን መሆኑን እርግጠኛ ሁን:: ከዓለማዊ ነገር፣ ወይም ከውስጥህ የቀረቡ የተለያዩ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን መምረጥ ያለብህ ለመንፈሳዊ ሕይወትህ የሚጠቅመውን ብቻ ይሁን::

ይህ ጸጋ ለቅዱሳን ብቻ ሳይሆን ለአንተም ለሁላችንም እንዲያውም ለኃጥእንም ጭምር የተሠጠ መሆኑን ዐውቀህ ልትጠቀምበት ያስፈልጋል:: የሚያስገርም የተመስጦ ችሎታ ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: የሚያሳዝነው ግን በኃጢአት መሆኑ ነው:: ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች በአንድ የተለየ የኃጢአት ዓይነት ላይ መመሠጥና አድናቆት ውስጥ መግባት ቀላል ነው:: ያ የሚያስላስለውና የሚያስበው ኃጢአት ደግሞ ሀሳቡን፣ ስሜቱን ስለሚገዛው፣ በሕሊናው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል:: ይህ ብዙ ጸሐፊያን፣ ገጣሚያን እና የልብ ወለድ ደራሲያን የሚጠቀሙበት ዘዴ ማለት ነው::

የቅዱሳን የሆነው ግን በመንፈሳዊ ነገር ላይ ብቻ ያተኩረ ነው:: ስለዚህ በኃጢአት ውስጥ ሆነው በክፉ ሀሳብ የሚመሠጡት ሰዎች በንስሐ ቢመለሱና ይህን ጸጋቸውን ወደመንፈሳዊ መንገድ ቢቀይሩት አስገራሚ ውጤት ይገኝበታል::

ከኃጢአተኝነት ወደንስሓና መንፈሳዊ እድገት የተመለሰውን ከዚያ በኋላ ኃጢአቱን ሁሉ ዘርዝሮ "The confessions" በሚለው መፅሐፉ ላይ የጻፈውን ቅዱስ አውግስጢኖስን እንደምሳሌ ማየት ይቻላል::

ማንበብ ተመስጦን ከሚያመርቱ መሳሪያዎች አንዱ ነው:: ተመስጦ የተሠወረው ተገልፆ እንዲታይህ ከጥልቁ ምሥጢር ተካፋይ እንድትሆን የሚያደርግህ እንደሆነ ዘወትር አስታውስ:: ተመስጦ ከባዶነት ጠ





ብቆ ለውሳጣዊት ነፍስህ መንፈሳዊ ምግብ እና እግዚአብሔር ያደረገልህን ድንቅ ሥራ ሁሉ የምታስብበት ጥበብ ይሠጥሀል::

## ተፈጥሮ

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለአብርሃም ልጅ ይስሐቅ የተነገረው፣ ሌላውን የተመስጦ ዓይነት ማለትም በተፈጥሮ መመሠጥን ሊያመለክት ይችላል:: «ይስሐቅም በመሸ ጊዜ በልቡ እያሰላሰለ ወደሜዳ ወጥቶ ነበረ::» (ዘፍ 24:63):: ይህ ማለት በተፈጥሮ ውበት መማረክና መመሠጥ ሳይሆን ቅዱስ ዳዊት እንዳለው ከሚያስገኘው መንፈሳዊ ጥቅም አንጻር ነው:: «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ:: የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል......» (መዝ 18:1)::

በተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ፈጣሪነት እንዲሁም ለፍጥረቱ ካለው ከፍተኛ ጥንቃቄ የተነሳ ጽኑ ፍቅሩን ወደማሰብ ትሸጋገራለህ::

ይህ በዐይን የምታየው ሰማይ ታላቅ የተመስጦ ዓለም ሊሆንህ ይችላል ስለእግዚአብሔር ዙፋን ማሰብ ነውና:: (ማቴ 5:34)::

ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ በራዕይ መጽሐፉ ስለዚህ ነገር አብዝቶ ይናገራል:: በተለይ (በራዕይ 4:1) «ከዚያ በኋላም አየሁ:: እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ....» እንዲሁም (በራዕ 21) ላይም ስለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትና እግዚአብሔርና ሰዎች በአንድነት ስለሚያድሩበት ሥፍራ በተመስጦ እየተመለከተ ይናገራል::

ሕሊናን በሰማያትና በሰማያዊ ነገር ላይ መስቀልና መመሠጥ ያለ ጥርጥር የአንድን ሰው አእምሮ እና ልብ ከቁስ አካላዊ (ማቴሪያላዊ) ደረጃ ከፍ ያደርገዋል:: በሰማያት መመሠጥ በመላእክት መመሠጥን ያመጣል:: በተጨማሪም በሰማያት ኃይሎች ሁሉ፣ ኪሩቤልን፣ ሱራፌልን፣ ሊቃነ መላእክትን በመንበሩ ፊት ያሉትን እልፍ፣ አእላፍ የሚሆኑትን ሠራዊት፣ ሰውን ለማገዝ፣ ለመርዳት የሚላኩትን ሁሉ እያሰቡ ፈጣሪን በተሠቀለ ሕሊና መመልከት ነው:: (ዕብ 1:14)

አሁን ስለቁራ ስናስብ በውስጣችን ያለው ምስል ጥሩ አይደለም:: እንደ መጥፎ እጣም የሚቆጥሩት ብዙ ሰዎች አሉ:: እግዚአብሔር ግን ይህን የመሠለ ጥንቃቄ ያደርግለታል:: ከዚህም በላይ በዚያ የረሀብ ዘመን ላይ ለኤልያስ መጋቢ እንዲሆነው ተመድቦም ነበር:: (1 ነገ 17:6):: በገድለ ቅዱሳንም ለባህታዊው ጳውሎስ ምግብ ሲያመላልስለት ስታይ እግዚአብሔርን ዕጹብ ዕጹብ ያሰኝሃል:: እግዚአብሔር እንስሳትን፣ አዕዋፍን፣ ፍጥረታቱን፣ ወደቅዱሳኑ ይልካቸዋል:: እነርሱም መታዘዝንና ፈቃዱን መፈጸምን ያውቁበታል:: በእነዚህ ሁሉ የተገለጸውን የእግዚአብሔር ክብር ስታነብ ባዶ ከሆነው የመጀመሪያ ሀሳብህ ወደጥልቁ መንፈሳዊነት በተወሠኑ ደረጃዎች መሻሻል ታደርጋለህ::

እግዚአብሔር በጥቃቅን ነፍሳት ሳይቀር ያስተምርሃል:: ብዙ መንፈሳዊ መንገዶችንም አዘጋጅቶልህ በእነዚህ ወደ ፈጣሪህ ተጉዘህ ትደርስ ዘንድ አድርጎሃል:: «አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፣ መንገዱንም ትመልከተህ ጠቢብ ሁን....» (ምሳ 6:6):: በሕይወቴ አንድም ጉንዳን ሥራ ፈት ሆኖ አይቼ አላውቅም:: ባለማቋረጥ ይሮጣል፣ ይሠራል፣ አይቆምም::

ገብረ ጉንዳንን በማስተዋል ላሰበው፣ ሕብረታቸውን፣ ከመጠናቸው አስር እጥፍ የሚሆን ነገር ተሸክመው ሲጓዙ ለተመለከተ አስገራሚ ትምህርት ይሰጣሉ:: የሕብረት ሥራን፣ ሥነ ሥርዓት፣ እንዲሁም መስመራቸውን ጠብቀው ሲጓዙ፣ ሕግና ሥርዓት መከተልን ያስተምራል:: በመካከላቸው የሚታየው ድንቅ የሆነ መግባባትም ፍቅርንም ያሳስባል:: እንደዚሁ ንቦችም ብዙ ሊያስተምሩ ይችላሉ::

አስደናቂው የንቦች አኗኗርም ሌላው ሊመስጥ የሚችል ዓለም ነው:: እግዚአብሔር እንዴት ንቦችን ከዚህ ተሠጥኦና ችሎታ ጋር ፈጠራቸው? የአበባን ዱቄት ሰብስቦ እጅግ የሚጥም ማርን መስራት የሚገርም ነው ያን አስገራሚና በእውቅ ዲዛይነር የተሰራ የሚመስል ሰም የሚሰሩትስ እንዴት ነው? አበባን ፍለጋ የሚጓዙት ርቀትም አስደናቂ ነው:: ስለዚህ እነዚህን አስገራሚ ፍጡራን የፈጠረ እግዚአብሔር ሥራው ምን ያህል ድንቅ ነው?





መንፈሳዊ ሰው ትንሽ ምክንያትን አንስቶ ወደጥልቅ መንፈሳዊ ዓለም የመግባት ችሎታ ያለው ነው:: ከዚህም በላይ ቁስአካላዊ ከሆነው ነገር መንፈሳዊውን ትምህርት ለይቶ ማውጣት የሚችል ነው::

የሰው አካልም የፈጣሪን ታላቅነት የሚያስረዳ በመሆኑ ሠፊ የተመስጦ ዓለም ሊሆን ይችላል:: የእያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ልዩ ችሎታ አስተዋይን ሰው የመመሠጥ በቂ ኃይል አለው:: ለምሳሌ የአእምሮአችን የማየት፣ የመስማት የእንቅስቃሴና የንግግር አስገራሚ መዕከልነቱ፣ ከእነዚህ ለአንዱ ማዕከል የደም ዝውውር ቢቋረጥ የሚከሰተው ነገር እንዴት አይመስጥ!

መጠኗ የእጅ ጭብጥን የምታክለውን ልብንና ሥራዋንም ብናስብ እንደዚሁ ነው:: እንደመጠኗ ሳይሆን እጅግ በጥንቃቄ የሚከናወኑ ውስብስብ ተግባርት ይከናወኑባታል:: ልብ በአእምሮ እንደሚወሰን፣ ሕይወትም በልብ እንቅስቃሴ ሥር ነው:: ስለሰውነት ክፍሎቻችን ሁሉ አንስተን ርቀታቸውን፣ ሥራቸውን ብንተነትን ጊዜም ሁኔታዎችም አይፈቅዱልንም:: እነዚህ ሁሉ ግን በአንድ ሰውነት ውስጥ በስምምነት መሥራታቸው ዕጹብ ድንቅ የፈጣሪ ሥራ ያሠኛል:: ከእነዚህ አንዱ እንኳን ከጥቅም ውጪ ቢሆን ዛሬ ያለው የረቀቀ የሳይንስ ጥበብ እንኳን ወደቀድሞ የተፈጥሮ ሁኔታው ሊመልሰው አይችልም::

ታዲያ እነዚህ ሁሉ በሁሉን ቻይ አምላክ የሆኑ የሰውነት ክህሎቶች ከሆኑና ይህን ያህል የሚያስደምሙ ከሆኑ የመንፈስ ስጦታዎች ምን ያህል ይረቅቁ ይሆን?

## በክስተቶች /በድርጊቶች/ መመሠጥ

ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ጥበብና ዕቅድ፣ ሀሳቡን እንክብካቤውን የሚገልጹ በዕለት ተዕለት ኑሯችን ውስጥ የሚከሠቱትን ነገሮች በማሰብ መመሠጥና ወደእግዚአብሔር መጓዝ ማለት ነው:: ያለንበትንና በታሪክ የምናውቀውን የእግዚአብሔር እጅ ያለበትን ነገር ሁሉ የሚያጠቃልለውም የዚህ ዓይነቱ ተመስጦ ነው::

እግዚአብሔር፣ ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች» እያልክ ብታመሰግነው ባህርያቱ በተመስጦ ውስጥ ወደእርሱ እንድትጓዝ ያደርጉሃል።

በእግዚአብሔር ባህርያት ላይ ተመስርቶ የሚመጣውን ተመስጦ በሁለት መንገድ ልታየው ትችላለህ። የመጀመሪያው፡ ከላይ የተመለከተው ከእኛ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር የሚገለጸው ሲሆን ሁለተኛው የራሱን ባህርያት የሚገልፅ ነው። ለምሳሌ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት፣ ወሰንየለሽነት፣ ፈጣሪነት፣ ኃያልነት፣ እያሰብክ መመሰጥ ማለት ነው።

እነዚህ ሁሉ ክርስቲያን በንጹሕ መንፈስ ወደ ንጹሕ አምላካችን ወደእግዚአብሔር ሊጓዝ የሚችልባቸው መንገዶች ናቸው።

ኃጢአተኞች ሳለን ሳይንቀን ወደእርሱ ለመድረስ እንድንችል እነዚህን መንገዶች ያዘጋጀልን አምላችን እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ስም የተከበረና የተመሰገነ ይሁን።





# ምዕራፍ ፫

## የሕይወት ለውጥ

## በመንፈሳዊ ልምምድ

በመረጃ ወይም በእውቀት መሞላት ሐይማኖትን ሊወክል አይችልም። እውቀት ብቻውን በቂ አይደለም አንድ ሰው ስለበጎ ምግባራት ሁሉ የጠለቀ እውቀት ቢኖረውና ወደ ሕይወቱ ቀይሮ የማይጠቀምባቸው ከሆነ ምን ይጠቅመዋል?

ብዙ እናነባለን፣ ብዙ እንሰማለን ነገር ግን እየሠራን ያለነው ምንድን ነው? በየዕለቱ ቅዳሴ ላይ የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታት፣ የተቀሩትን 7 መልእክታት፣ የሐዋርያትን ሥራ መጽሐፍ፣ እንዲሁም ወንጌል ሲነበቡ እንሰማለን። በተጨማሪም የቅዱሳን ሕይወት እንዴት እንደነበረ እንድናውቅ መጽሐፈ ስንክሳር ይነበብልናል። በየቤታችንም እንደየተሰጠን ጸጋ መጠን የምናነበው የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ይኖር ይሆናል።

ይሁን እንጂ አሁን እኔና አንተን የሚያጠያይቀን ነገር አለ።

ይህ ሁሉ በሕይወታችን ላይ ምን ዓይነት ተግባራዊ ለውጥ ነው ያመጣው? ወይስ ማወቃችን ብቻ ያረካናል? ትልቁ ጉዳይ እውቀትን ለባሕርይ ብሎም ለሕይወት ለውጥ መጠቀሙ አይደለም? ክብር ምሥጋና ለእርሱ ይሁንና ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፣ ሕይወትም ነው»*። ብሎናል። (ዮሐ 6፣63)

### <u>ይሕ የሕይወት ለውጥ እንዴት ይመጣል?</u>

* በመንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ እውቀት ወደ ተግባር፣ መረጃ ወደ ሥራ ይቀየራል/ይሻገራል።

በእለት ከእለት ኑሯችን ውስጥ ዘወትር ወደቤተክርስቲያን የሚገሠግሡ፣ ኃጢአታቸውን ለካህን የሚናዘዙ፣ ሥጋወደሙን የሚቀበሉ ብዙ ሰዎችን እናያለን። ይህ ማንም የማይቀማቸው በጎ እድል ሆኖ ሳለ በተቃራኒው ደግሞ አብሯቸው የሚኖር ደካማ ባሕርይን ለመቅረፍ ጥረት ከማድረግ

ጌታችንን ሳምራውያን ባልተቀበሉትም ጊዜ «ጌታ ሆይ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህ?» ብለው የጠየቁት፣ ጌታ የገሠጻቸው እነዚሁ ሁለት ደቀ መዛሙርት ነበ:: *«ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም:: የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ::»* (ሉቃ 9፤51-56)

ነገር ግን ጌታ የነጎድጓድ ልጆችን እንደ አጀማመራቸው ሳይሆን የፍቅር ነበልባል እንዲሆኑ አለማመዳቸው::

ቅዱሳን ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወትን / መንፈሳዊነትን በአንዲት ቅጽበት የደረሱበት አይደለም:: ይልቁንም ራሳቸውን ቀስ በቀስ ለዚህ ታላቅ ደረጃ አለማምደው ነው:: በሁከት ውስጥ እርጋታን፣ በፈተና ውስጥ ትዕግስትን ተለማምደው ነው:: በብዙ ልፋትና ትግል ነው ቅድስናቸውን ያገኙት:: ስለዚህ በትግላቸው መጨረሻ የደረሱበትን ክብር በአንዲት ጀንበር ለማግኘት የምንጀምር አንሁን :: ደረጃ በደረጃ ለመሻሻል ፣ ለማደግ እንጣር እንጂ::

በአገልግሎት መስክም ጌታ ሐዋርያቱን አለማምዷል::

ካስተማራቸውም በኋላ ለአገልግሎት /ለተግባራዊ ልምምድ ላካቸው:: እነርሱም የአገልግሎታቸውን ውጤት ተመልሰው ነገሩት:: በገጠማቸውም ነገር እጅግ በጣም ተደስተው ነበር:: «ሰብዓውም ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት» ደስታቸው በዚህ መልክ መሆን ስለሌለበትም ጌታችን ስሕተታቸውን አረመላቸው :: *«መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ::»* (ሉቃ 10 17-20)

በሌሎች የተለያዩ መስኮችም ብዙ ተለማምደዋል::

ከእነርሱ አንዱ /ማንም ታላቅ ሊሆን የሚወድ ቢኖር ሊያደርግ የሚገባውን እንዲህ ብሎ ነበረ ያስተማራቸው:: *«ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን:: ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን:: እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም::»* (ማቴ 20፤26-28)

❖ <u>ለመንፈሳዊ ልምምድ ጠቃሚ ምክሮች</u>

በመጀመሪያ ምን ያህል ዐዋቂዎች ብንሆን ማወቃችን ብቻ ሊያስደስተንና ሊያረካን አይገባም:: ትልቅ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው





ያወቅነውን በሥራ ለምንተረጉምበትና ትዕዛዛትን መፈጸም ለምንችልበት ሕይወት ነው::

ጌታችን የተራራው ስብከቱን ሲያጠቃልል የተናገረው ቃል ይህ ነው::

*«ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል:: - - - ይህንም ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል»*:: (ማቴ 7፤24-26) ስለዚህ እንደሠማን ለመሥራት ለምግባራችን ትልቅ ትኩረት መስጠት አለብን:: ይህንንም ሲያረጋግጥልን «በሠማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም::» ብሏል ካህኑም በጸሎተ ቅዳሴ (ቅድመ ወንጌል) ወንጌልህን ለመስማት፣ እንደሰማንም ለመሥራት በቅዱሳን ጸሎት የበቃን አድርገን» እያለ የሚጸልየው ለዚህ ነው::

ስለዚህ እኛም እንደ ትእዛዛቱ ለመኖርና ቃለ ወንጌሉን ለመፈጸም ራሳችንን እናለማምድ::

መንፈሳዊ ልምምድ አንድ ሰው ለነፍሱ ድህነት ያለውን ተስፋ ያመለክታል:: ስሕተቶቹን፣ ድክመቶቹን ሁሉ ለይቶ አውቆ ለማስወገድ እየጣረ መሆኑን ይጠቁማል:: አንተም ወንድሜ ስሕተቶችህን ሌሎች አይተው እስከሚነግሩህ ድረስ መጠበቅ ሳይኖርብህ በራስህ ለይተህ ዕወቃቸው:: ምክንያቱም ያለብህን ችግር ሳታውቀው ለመንፈሳዊ ልምምድ መነሳት ስለማትችል ነው::

«በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም» ይባል የለም? «ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም::» (ማቴ 9፤12) ባንተ ያለውን ችግር ሌሎች ማወቃቸውም ቢሆን አያበሳጭህ:: ይልቁንም በየትኛው መንፈሳዊ መስክ ልምምድ ማድረግ እንደሚገባህ የሚጠቁም መረጃ አድርገህ ተቀበለው:: በእግዚአብሔር ሕግ ብርሃንነት ራስህን እየመረመርክ ድክመቶችህን ፈልግ:: ትንንሽ ድክመቶች እንኳ ቢሆኑ አትናቃቸው፣ ያድጋሉና:: *«ወይናችን አብቦአልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች፣ ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምዱችሁ ያዙልን::»* (መኃ. 2፤15)

ራስህን ከማዕደቅ ተቆጠብ ለስህተቶችህም ማስተባበያ አትፈልግ ራሱን የሚያፀድቅ ሰው ዘወትር ባለበት መሄድ እንጂ የሚያሻሽለው አንድም ነገር የለም:: ምክንያቱም ባይኑ ፊት ከርሱ በላይ ሰው የለም ለራሱ እንከን የለሽ ነው:: ለችግሮች መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ይህን ያደረኩት በዚህ ምክንያት ነው እያለ ሲያስተባብል ወድቆ ይቀራል ለራሱ ትክክለኛ ግምት ያለው የማይመፃደቅ ሰው ግን ድክመቱን መናዘዝ ብሎም ማስወገዱን መለማመድ ይችላል::

ችግሮችህ ስር ሰደው ለሎች ሊገልጡብህ የሚችሉበት ደረጃ ሲደርሱ የሚሰማህ መሸማቀቅ እጅግ ከፍተኛ ነው:: ነገር ግኔ ቀደም ብለህ ራስህ ገልጠሃቸው ለመፍትሔው ልምምድ ብታደርግ ይህ ሁሉ ነገር ባንተ ላይ አይከሰትም::

ሁሌም ራስህን ሆነህ ተገኝ:: በሕይወትህ ቅንነት የሚነበብህ ሰው ሁን:: መጻሕፍትን ስታነብም ሆነ ስብከት ስታደምጥ ጉድለቶችህን እየፈለግህ ይሁን:: ሰምተህ ለማድረግ ተነሳሳ (ምን እናድርግ?) ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚጠቅሙ ነገሮችን በሙሉ ተለማመዳቸው::

ከቻልክ በሣምንት ባይቻልህ በአንድ ወር አንድ ድክመት ለማስወገድ ብትለማመድ በአንድ አመት ውስጥ 12 ወይም ከዚያ በላይ ችግር ቀረፍክ ማለት እኮ ነው:: የኃጢአት ሥሩ አንድ ነው:: ብዙ መንገዶች ቢኖሩትም እርስ በራሳቸው የተያያዙ መሆናቸውንም እርግጠኛ ሁን:: አንድ የተወሰነ የኃጢአት ዓይነትን ለመቅረፍ ስትነሳ ሳታውቀው ሌሎችንም እየበጣጠስክ መሆኑን ዕወቅ::

አንድ በጎ ሥነ ምግባርን ለማዳበር ስትለማመድም ቢሆን ሌሎች ብዙ ሥነ ምግባራትን እያተረፍክ መሆኑን ልብ በል:: ሥነ ምግባራቱም በአንድ ሠንሰለት የተያያዙ ናቸውና::

ለዚሁም ምሳሌ እሰጥሃለሁ::

እንበልና ከማይጠቅም ጓደኝነት ብቸኝነትን መርጠህ እየተለማመድከው ነው:: በዚህ ውስጥ ደግሞ ራስህን በሥራ መጥመድና እንዳትጨነቅ ማድረግ ሊጠበቅብህ ነው:: ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ ታነባለህ::





ከዚያም ትጸልያለህ:: ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር በመሆንህ ደስ ብሎህ ትዘምራለህ:: እንዲሁም ካነበብከው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወይም ከሰማኸው ቅዳሴ ወስደህ በተመስጦ ወደ እግዚአብሐር የምትጓዝበት መንገድ ታደርገዋለህ:: ስለዚህ ለመልካም ሥነ ምግባር ማዳበሪያነት የተጠቀምከው አንዱ ልምምድ ብዙ ነገሮችን ይዞ መጣልህ ::

ወይም አንድ ቀን አርምሞን ያንተ ሀብት ለማድረግ እየተለማመድክ ቢሆን አዕምሮህን ጠቃሚ በሆኑ ነገሮች ብቻ መያዝ ያስፈልግሃል:: አርምሞውም በራሱ ጸሎትን ተመስጦና፣ ማንበብን ይዞልህ ሊያድግ ይችላል:: አንዱ እያደረግህ ያለኸው ልምምድ በእርግጠኝነት ሌሎችንም እያለማመደህ ነው::

## ልብ በል

አንተ ልምምድህን ስትጀምር የእግዚአብሔር ጸጋም በውስጥህ የሚሠራውን ሥራ ይጀምራል:: በልምምድህ ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር በፍጹም ብቻህን አይተውህም:: አምላክህ ከአንተ ጋር ይሠራል:: ምክንያቱም አንተ ሁሉን ትተህ ወደ እግዚአብሔር መጓዝን የሕይወት ምርጫህ አድርገሃልና ነው:: አምላካዊ ረድኤቱ ለዚህ የተቀደሰ ተነሳሽነትህ ምላሹን ይሰጥሃል:: ዲያብሎስ ልምምድህን ለማቋረጥ የሚከፍትብህንም ጦርነት በብቃት መክተህ ድል አድራጊ እንድትሆን ይረዳሃል:: ትልቁ ነጥብ ወዳጄ በፍፁም ወደኋላህ አትመለስ:: ቸልተኛና ሠነፍ አትሁን:: ጽና፣ በርታ፣ ታገሥ *«በምትሔድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፣ አይዞህ፣ አትፍራ አትደንግጥ. . .»* (መ.ኢያ 1፣9) ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባራትን የምትለማመዳቸው ከማወቅ አልፈህ ልትኖርባቸው ስለሆነ ጠቃሚ ነገር እንደጀመርክ ተረዳ::

ሰው በጎ መንገድን ለአንድ ለሁለት ቀን. . . እስከ ሳምንት መከተል ላይቸግረው ይችላል:: ላንተ ግን ትልቁ ነገር እነዚህን ሥነ ምግባራት የራስህ ልምዶች ሆነው እንዲቀጥሉ ማድረግና የባሕርይህ ክፍሎች ማድረግ ነው:: ስለዚህ ልምምድህ የፈለግከው እድገት በጥልቀት ተተክሎ ሥር እስከሚሠድድ የሚቀጥል መሆን አለበት:: *«ለረጅም ጊዜ ጸንተህ በመታገስ ለፍፃሜ የማታደርሰው ዕቅድ ሁሉ ፍሬ ቢስ ነው»* ይላል ማር ይስሐቅ::

❖ የልምምድህ ተግባራዊ መለኪያው ቀጣይነቱ ነው። ጊዜም ልምድህን የሚያደናቅፉ ነገሮችን ለማወቅና ለመቋቋም እንድትችል ዕድል ይሰጥሃል።

ስለዚህ ዛሬ ነጭ ነገ ጥቁር መሆን ወይም መለዋወጥ መንፈሳዊ ትርፍ የሌለው ከንቱ ነገር ነው ብዙዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ፍፁም ለመሆን ሲጥሩ አይተናል ውጤቱም ምንም እንደነበር ተረድተናል ወይም ብዙ አይነት ልምምዶችን በተመሳሳይ ጊዜ ለማድረግ እንደ እቅድ በፊታቸው አስቀምጠው ከአንዱም ሳይሆኑ ሲቀሩ ተመልክተናል። አንተ ግን የምትፈልገው ነጥብ ላይ ለመድረስ ልምምድህን በጥበቢ ይዘህ ቀስ በቀስ እደግ።

*** ልምምድህ የታወቀና ግልፅ ይሁን**

ለምሳሌ 14 ቱንም የፍቅር ባሕርያት /ሁኔታዎች ቅዱስ ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 13 ላይ እንደገለጻቸው ሁሉንም በአንድ ጊዜ ልምምድ ላድርግ ብለህ አትነሳ። ነገር ግን አንዱን ባሕርይ ለአንድ ጊዜ ልምምድ በቂ አድርገህ ያዘው። አያያዝህም ትልቅ ትኩረት ያደረግህበትና ውጤቱን የሚያመላክት እንዲሆን ታገል። የምትለማመደውን ነገር የቃሉን ትርጉም እንኳን ሳታውቀው አትጀምረው። በቅድሚያ ትሕትና፣ፍቅር የዋሕነት፣ አርምሞ የመሳሰሉትን ከነዝርዝር ምንነታቸው መርምረህ ተረዳ። ግልጽ ሆነው ካልታዩህ በቀር ውጤትህ ምንም ይሆናል። ልምምድህ ከሰዎች ሙገሳና ክብር ለመሻት አይሁን። ሰዎች ባመሠገኑህ ባከበሩህ ቁጥር ጉድለትህንና ኃጢአትህን አስብ። ዋጋህ በሰዎች አፍ ወስጥ በዚህች ምድር እንዳይቀርብህም ተጠንቀቅ።

ልምምድህ ተግባራዊ ፍሬ እንዲኖረው በአቅምህና በችሎታህ የተገናዘበ ይሁን። አንዳንድ ሰዎች ከአቅማቸውና ከደረጃቸው በላይ የሆነ ነገርን ለመሆን ሲጥሩ ይታያሉ። የፈለጉትን በጎ ነገር ለመለማመድም ያሉበት ጊዜና ቦታ የማይፈቅድ ይሆናል። ጀምረውትም ወደቀጣዩ ደረጃ ፈጥነው መሸጋገርን ብቻ የሚፈልጉ አሉ። እውነታው ሲታይ ግን ተሽማቀው ያፈገፍጋሉ።





ለምሳሌ አንተ ሰውነትን ከመቅጣት፣ የሥጋ ፈቃድን ከማድከም አልፈህ ሰውነትህን ለሞት እስከማጋለጥ ድረስ ለመፆም አትታገል። ያለህበትን ደረጃ አስተውልና በየጥቂቱ እደግ። ወይም የሥራ ፀባይህን፣ አካባቢህን፣ ቤተሰብህን ከግምት ውስጥ ያላስገባ ፅሙና /አርምሞን ለመለማመድ አትሞክር። ሌሎችንም እንደዚሁ።

ዛሬ በአቅምህ መጠን የያዝከው ትንሽ ነገር ነገ አድጎ የሚያሳድግህ ነው። መግባባትን አብሮ መኖርን በሚጠይቀው ማህበረሰብ ውስጥ ዝም ብለህ ብትኖር ሊያስቸግርህና የተገለልክም ሊያደርግህ ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ መናገር ያለብህን ነገር አጭርና ግልጽ ማድረግን መለማመድ ትችላለህ። ለሰዎች ብለህ ቃል የሚበቃውን በዐረፍተ ነገር፣ ዐረፍተ ነገር የሚበቃውን በረጅም አንቀጽ መግለጽ አይኖርብህም።

በዚህ መልኩ ብትለማመድ አንተ ራስህ «አስፈላጊ ካልሆነ በቀር አልቀባጥርም።» ትላለህ። በዚህ በዝግታ ወደመናገር ልምምድ፣ አላስፈላጊ ከሆነ ጩኸት መቆጠብን ወደመለማመድ ትሸጋገራለህ። (1 ነገ 19 ፥12) በዚህ መልኩ ከምላስ ወለምታም ቀስ በቀስ እየራቅህ ትመጣለህ።

❖ ልምምድህ በተግባራዊ የሕይወት እንቅስቃሴህ ውስጥ ጠልቆ የገባ ይሁን። ለሌላው ሰው እጅግ ተስማሚ የሆነው ልምምድ ካንተ ጋር ላይስማማ ይችላል። ስለዚህ አንተ የምትደክመው የራስህን ችግሮች ለማስወገድ ነውና፣ መንፈሳዊ ጉድለቶችህን ለመሙላት ነውና አቅምህን የሚመጥነውንና ለእድገትህ ተስማሚ የሆነውን ዐውቀህ ተለማመድ። ልምምድህም ውስጣዊና ውጪያዊ ተግባርህ የታረቁበት ይሁን።

- ምናልባት በልምምድህ ወቅት መውደቅ ቢያጋጥምህ አትደናገጥ። ተስፋም አትቁረጥ። ፈጥነህ ምክንያቱን ፈልግ። ከዚያም ልምምድህን ስትቀጥልበት ችግርህ ቀስ በቀስ ይወገዳል። ይህን በማድረግህ መንፈሳዊ ልምድህ እየካበተ ነው። ጠላትህ እንዴት ጦርነት እንደሚከፍትብህ እንዴት እንደሚወጋህ ጠንቅቀህ ዕወቅ። እናም ለመከላከል. . . ለማሸነፍ ተዘጋጅ (1 ጴጥ 5፥8) ይህን በመሰለ ልምምድ ውስጥ ብዙዎች ለሌሎችም ተርፈው ማስተማር ችለዋል። ከሕይወት ብዙ ተምራ ብዙ ልምድ ያላት ሆና ልጇን በሚገባ እንደምታስተምርና እንደምትጠቅም እናት ማለት ነው።

ከወደቅህባት ቅፅበትና ከሁኔታዋ ተማር ያቺን ስህተት ዳግመኛ ላለመፈፀምም ተለማመድ ይህች የትህትና ምንጭ ናት በዚህ መልኩ የምትማር ከሆንክ በመልካም ስራህ ብቻ የምትመፃደቅ ልትሆን አትችልም::

❖ በተጨማሪ ከስሕተትህ መማርህ ለደካማውና ለኃጢአተኛው ሊኖርህ የሚያስፈልገውን ርህራሄ ያፈልቅልሃል:: ኀደሉነትህ ለተሰፈ መቁረጥ ሳይሆን በመዳን ተስፋ በጌታ ፊት ተንበርክከህ/ሠግደህ እየጸለይክ ምህረቱን የምትጠይቅበት ግፊት ይሁንህ:: አሁንም ኃይሉና ጸጋውን እንዲያበዛልህ መለመንን አታቋርጥ:: ደግሜ እልሃለሁ በጭራሽ ወደኋላህ አትመለስ፣ እንዲያውም አትይ::

❖ <u>ልምምድ ተጋድሎ ነው</u>

ግልፅ በሆነ ገፅታው ልምምድ ለፍፁምነት የሚደረግ ተጋድሎ ነው:: ልብን ንፁህ ለማድረግና ትክክለኛ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን ለማስቻል የሚደረግ ጥረት ነው:: በአንድ መልኩም ተጋድሎ ብቻም ሳይሆን ማንነትን ለእግዚአብሔር ለማስረከብ የሚቀርብ መጠይቅ ወይም ፀሎት ነው:: ግን እንዴት?

በቃል ደረጃ ብቻ ፍላጎታቸውን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡ ብዙ ናቸው:: ልባቸው ይሻዋልና በጸሎታቸውም ይህንኑ ይጠይቁታል:: እነዚህን መሠል ሰዎች የሚያስፈልጋቸው ታላቅ ነገር መንፈሳዊ ልምምዳቸውን መቀጠል ነው:: ከማይነገር ፍቅሩ የተነሳ መንፈሳዊ ነገርን ስናስብ ስንሠራም በውስጣችን የሚሠራና የሚኖር እግዚአብሔር ነው:: ልምምዳችን ውጤታማ ሆኖ ተጋድሎአችንን ብንፈጽምና በእኛ የእግዚአብሔር ስም ቢከብር ከዚህ የበለጠ ደስታ የለም::

*«እግዚአብሔርን ለመምሠል ግን ራስህን አስለምድ ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፣ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል::» «ይህ ቃል የታመነ ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው::»* (1 ጢሞ 4፣7)





## ምዕራፍ ፮

## ጾም

ጾም ማለት መከልከል፣ መታቀብ፣ መወሠን ማለት ነው:: ከምግብና ከመጠጥ ብቻ ሳይሆን፣ ስኬታማ መንፈሳዊ ሕይወትን ከሚያደናቅፉ ማናቸውም እኩይ ተግባራት መራቅና መከልከል በራሱ ወደ እግዚአብሔር መጓዝ የሚቻልበት መንገድ ነው::

ራስን መግዛት፣ ስሜትን መግራት፣ ጸጋን መጠበቅ፣ ራስን መሆን የሚቻልበት ትልቁ የመንፈሳዊነት ቁልፍ ጾም ነው::

መመገብ ፣ መጠጣት ፣ ሰውነትን ደስ ማሰኘት ስሜትም ግዴታም ነው:: ይህን እያወቀ ራሱን ለተወሰኑ ጊዜያት መቆጠብ የቻለ ሰው በምንም ጉዳይ ላይ ቁርጥ ውሳኔን ወስኖ መፈጸም የሚችል ሰው ለመሆኑ አስረጂ ነው:: እውነተኛ ክርስቲያን ስሜት የሚመራው ሳይሆን ስሜቱን የሚመራ ነው:: ሕይወቱን በጾም የመራ ሰው ሌሎች የኃጢአት ጽንሶች ሊፈትኑት አይችሉም:: መከልከልና መታቀብን በሕይወት ስለተለማመዳቸው ኃጢአትንም ለመግደል ሁነኛ መሣሪያ ይሆኑታል:: የመታቀብና የመከልከልን ፈተና ያለፈ ሰው ምን ጊዜም አሸናፊ ነው:: ይህን የመንፈስ ጥንካሬ እግዚአብሔርም ከእኛ ፍሬ አፍርቶ ማየትን ይሻል::

በመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋንም ፊት ተቀምጦ የነበረ ነገር ቢኖር ራስን የመግዛት የመቆጠብ ፈተና ነው:: በገነት ካለው ፍሬ ሁሉ ብሉ ነገር ግን መልካምና ክፉውን ከሚያሳውቀው ከዚህ ዛፍ ፍሬ አትብሉ::. . .» ራስን የመግዛት ጥያቄ የሰው ልጆች ታሪክ መጀመሪያ ነው:: ለደካሞች እንደሚመስላቸው ራስን መግዛትና ታዛዥ መሆን ነፃነትን ጥያቄ ውስጥ የሚከትት ጉዳይ አይደለም:: ይልቁንም ራስን መግዛት የሥጋ ሳይሆን የመንፈስ ፍሬ ነው:: (ዘፍ 2፣16፣3፣3)

ጥበበኛው ሰሎሞን የራሱን ያልተገደበ የደስታ ፍላጎት በተመለከተ የተናገረው ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ይሆነናል:: «ዓይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኋቸውም ልቤም በድካሜ ሁሉ ደስ ይለው ነበር. . .» (መክ 2፣10) ስለዚህ ጥበቡን አጣ አምላኩንም በደለ:: «ሰሎሞንም ሲሸመግል ሚስቶቹ ሌሎችን አማልክት ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉት የአባቱ የዳዊት ልብ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር እንደነበረ የሰሎሞን ልቡ እንዲሁ ፈልነበረም» (1 ነገ 11 ፣4)

የሥጋ ፍላጎት ብዛት የመንፈሳዊ ሕይወት መሰናክል መሆኑን አየህ?

❖ ጾም ከሥጋ ፈቃድ በላይ ከፍ ለማለትህ ማረጋገጫ ነው:: በዚህ ወራት ለሥጋችን ያሻውን ሁሉ አንሰጠውም:: ጥያቄዎቹ ሁሉም አይመለሱም:: ለምን?

ራሳችንን ስለገዛን! ከዚህም በላይ ከቁስ አካላዊነትም ከፍ ብለናል። በጾም መንፈሳዊነት ጎልቶ ይወጣል።

መንፈስም የራሱን ዕድል የመወሰኛ መንገድ የሚያገኘውም ጾም ሲኖር ነው። *«ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ነገር ግን ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ።»* (ዮሐ 6፥27)

*«ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ፣ ስለመንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዘአብሔር ዘንድ ጥል ነውና»* (ሮሜ 8፥6)

❖ በመንፈስ ጠንካራ መሆን የሚመጣው ከጾም ነው።

በጾም ወራት ወደ እግዚአብሔር በተመስጦ የምንጓዘው ጉዞ እና ጸሎታችን ጥልቅ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ያድጋል። ምሥጋናችን ከልብ ይሆናል። የክፋት ምንጭ ይደርቃል። ለምሳሌ በሰሙነ ሕማማትና በሌሎች ጊዜያት ያለን መንፈሳዊ አቋም ፍፁም የተለያየ ነው። ጸሎት፣ ስግደት፣ ምሥጋና፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ማሰብ፣ ውለታውን መገንዘብ፣ በሌሎቹ ዘመናት ይህን ጥንካሬ ይዞ መኖር ከባድ ቢመስልም መጣር።

ጾም አላስፈላጊ ስሜቶችን ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን በፈቃደ እግዚአብሔር ለመኖር የሚደረግ ልምምድም ነው። ጾም የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ ነው። የሰዎችን መንገድ ሊያቀና፣ የደህንነት በርን ለመክፈት ወደዚህ ዓለም የመጣውና ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከኃጢአት በቀር እንደኛ ያለ ሥጋና ነፍስን የነሳው ጌታችን የሥራው ሁሉ መጀመሪያ ያደረገው ጾምን ነው። መምህራችን ክርስቶስ *«ከእኔ ተማሩ»* እንዳለ ከእርሱ የተማርነው የነገራችን ሁሉ መጀመሪያ ጾም ነው፡ «ማቴ 11፥29» ስለዚህም ዛሬ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለምትፈጽማቸው ምሥጢራት ሁሉ ጾም ቅድመ ሁኔታ ነው። በዓላትን ለማክበር ለሚደረገው ዝግጅት ጾም ዋነኛው ነው። ጌታችንን በልደቱ ለመቀበል እንጾማለን፣ የትንሳኤው ብስራት የሕይወታችን ብርሃን ይሆን ዘንድ ከሞት ሊያነሳን የተቀበለውን መከራ በማሰብ እንጾማለን። የእመቤታችንን፣ የዓለም ብርሃን ያላቸውን የቅዱሳኑን በረከት ለመቀበል እንጾማለን።

*« . . . እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።* (የሐዋ ሥራ 13፥2-3)

በአጋንንት ላይ ድልን የሚያቀዳጅ ኃይል ጾም ነው። የጌታችን ደቀ መዛሙርት ሊያደርጉት ተስኗቸው በጠየቁት ጊዜ የሰጣቸው ምላሽ *«ይህ ዓይነት ግን ከፀሎትና ከጦም በቀር አይወጣም።»* የሚል ነበር። (ማቴ 17፥21)





በጾም ውስጥ የሚጸለይ ጸሎት እጅግ የበለጠ መንፈሳዊ ኃይል አለው። የሚጾም ሰው ራሱን መግዛት የቻለ ስለሆነ ወደ እግዚአብሔር የቀረበና አጋንንትን መርታት የሚችል ነው።

ቅዱሳን መከራን ያለፉበት ሕይወት ጾም ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን በመጽሐፈ አስቴር ላይ የሠፈረው ታሪክ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ መሆን የሚችል ነው። (አስቴር 4፥16) በዚህ ወቅት የእግዚአብሔር ምላሽ ፈጣን ነበረ። ይሕም በጾም በጸሎት ስለጠየቁት የሆነ ነው እንጂ ሌላ ምክንያት አልነበረውም።

የኢየሩሳሌም ቅጽር መፈራረስንና የበሮችዋን መቃጠል በሰማበት ጊዜ ነህምያ የጾመውን ጾምም እንደዚሁ በመጽሐፉ እናነባለን። ምን ያህል የፈጠነ መልስ እንዳገኘም ጽፎልናል። ለህዝባቸው ሁሉ የመንጻት ምክንያት የሆነውን የዕዝራ፣ የዕንባቆም ጾም፣ የዳንኤልን ጾምና ውጤቱን ሁሉ ክርስቲያናዊ ሕሊና ከመዝገብ አይፍቀውም። (ዳን 9፥3 ፣ ዳን 10፥3) «ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ። ወደ አምላኬም ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ . . .»

በንስሓ ሕይወት ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወትም ጾም ነው። የነነዌ ሰዎች ንስሐ ገብተዋል። ንስሓቸው ግን በቀላሉ ከክፋት በመመለስ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ከንጉሡ እስከ ተርታው ሕዝብ ጾመዋል። እግዚአብሔርም በጾም በጸሎት የበረታ ንስሓቸውን ተቀብሎ ከኃጢአትና ከበደላቸው ነፃ የወጡ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። (ዮና 3)

ጾም የሰው ጥበብ ያላመጣው አምላካዊ የሕይወት መመሪያ መሆኑንም የነቢዩ ኢዩኤል መጽሐፍ ይነግረናል።

*«አሁንስ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ በፍጹም ልባችሁ፣ በጾምም፣ በልቅሶና በዋይታ ወደእኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ።»* (ኢዩ 2፥12)

ንጉሥ ዳዊትም ይህንን በሚያጠናክር አነጋገር *«ነፍሴንም በጾም አደከምኳት» ይላል።»* (መዝ 34 (35) ፥13) ፣ (መዝ 68 (69) ፥10)

አገልግሎትን ፍጹም የሚያደርግ ጾም ነው። ይህንን ከማብራራት ይልቅ ጌታችንን ምሳሌ ማድረጉ በእጅጉ የተሻለ ነው። 40 ቀናት 40 ሌሊት የጾመው አገልግሎትን ለመጀመርና ምሳሌ ለመሆን ነው።

ይህንም መሠረት በማድረግ አባቶች ጾምን የበጎ ምግባራት ሁሉ መጀመሪያ እንደሆነ አስተምረዋል። ሐዋርያትም የተጠሩለትን ዓላማ ማከናወን የቻሉት በጾም ነው። ጌታችንም ስለ እነርሱ አስቀድሞ የተናገረላቸው ስለሆነ በጾም መከራን ታገሡ፣ አጋንንትን አወጡ፣ ድውያንን ፈወሱ ሙታንን አስነሱ፣ በአጠቃላይ ጾም የተዓምራት

*ምንጭ ሆናቸው ። «. . . ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል። በዚያ ወራትም ይጦማሉ።»* (ማር 2፣20)

*«ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን። በብዙ መጽናት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመጦም. . . ራሳችንን እናማጥናለን. . .»* ሲል ቅዱስ ጳውሎስም ጾም ለአገለግሎት ያለውን ወሳኝነት ገልጾታል። (2 ቆሮ 6-4)

እና አንተስ ወንድሜ፣ የሕይወትህን እንቆቅልሽ ለመፍታት፣ የችግርን ባሕር ለማቋረጥ፣ አገልግሎትህን፣ አምልኮህን ፍጹም ለማድረግ ጾመሃል? ካልጾምክማ ሕይወትህ ባዶ መሆኑን ተረዳ ። ስለሕይወትህ ማሰብ ከቻልክ ግን ጹም!

## ምን ዓይነት ጾም ?

ምናልባት በነቢዩ በኢሳይያስ ዘመን እንደሆነው ፋይዳው የማይታይ እንዳይሆን። *«ስለምን ጾምን፣ አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን ? አንተም አላወቅህም? ይላሉ»* (ኢሳ 58-3) ጌታም እንዲህ ሲል ይመልስላቸዋል። *«እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፣ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፣ እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ፣ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ። ድምጻችሁንም ወደላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም። እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን?. . .»* (ኢሳ 58፣5)

ወንድሜ በመጀመሪያ ጾም ሁሉ እግዚአብሔር የሚቀበለው እንዳልሆነ ማወቅ አለብህ። በሳምንት ሁለት ቀን የሚጾመው ፈሪሳዊ የቀራጩን ያህል እንኳ ዋጋ አላገኘም። (ሉቃ 18፣12)። ስለኃጢአት ሳይሰቀቁ፣ ራስን በትህትና ሳያዋርዱ የጾሙት ጾም ረብ የለሽ ነው። በኤርምያስ ዘመን የተደረገው የኃጥአንም ጾም እንደዚሁ ከንቱ ነልነበረም? *«በጾሙ ጊዜ ጸሎታቸውን አልሰማም»* (ኤር 14 ፣11)

ምክንያቱም ራሣቸውን መግዛት ተሥኗቸዋል። ይጾማሉ፣ ነገር ግን ከሕገ እግዚአብሔር ርቀዋል። ለሰዎች ይታዩ ዘንድ በግብዝነት እንጾማለን የሚሉ ሁሉ አሁን ሊያስቡበት ይገባል። ዋጋቸው በምድር፣ በሰው ፊት ቀርቶባቸዋልና (ማቴ 6፣16-18)

አሁን አንተም ቆም ብለህ ራስህን መርምር። እጾም ነበር ነገር ግን ምንም አላተረፍኩም እንዳትል። ይልቁንም የሚጎድለኝ ምንድን ነው? ብለህ መርምር። የአምላክህንም ፈቃድ ፈጽም። ዋጋ አጥተህ ከሆነ የጾምህን ዋጋ የሚያስቀር የኃጢአት ቅሪት አለ ማለት ነው። ሌሎችም የሚጎድሉህ ነገሮች ይኖራሉ። ስለዚህ :- እንዴት ልጹም፣ የእውነተኛ ጾም ትርጉምስ ምንድን ነው እና ከጾም የማተርፈው ነገር





ምንድን ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ታገኝ ዘንድ በጥቅሉ ስለጾም መነጋገራችንን እንቀጥል:- ተከተለኝ።

## ❖ ከምግብና መጠጥ መከልከል

ብዙዎች ጾምን የምግብ ለውጥ ወራት ብቻ አድርገው ያስቡታል። ከሥጋ ምግቦች ወደ አትክልት፣ ከቅባት ወደ ደረቅ የሚደረግ ሽግግር። ጾም ስላለው መንፈሳዊ ፋይዳ ግድ የሌላቸው ጥቂቶች አይደሉም።

በመሠረቱ ጾም ለተወሰኑ ጊዜያት ራስን ከምግብ መከልከል፣ ከዚያም በአልሚ ምግብ ይዘታቸው ዕውቅ ከሆኑ ምግቦች በስተቀር በጥቂቱ መመገብን መነሻ ያደርጋል።

አንተ ከምግብና ከመጠጥ መከልከልን ሞክረኸዋል?

ከባድ የረሀብ ስሜት ደረጃ ላይ ደርሰህስ ታግሰኸዋል?

ይህ የመጀመሪያ መልመጃ ነው። *«ረሀብና ጥምን መታገስ»* ጌታና አምላክህም *«ተራበ» ተብሏል - ተርቧልም።* (ማቴ 4፣2)፣(ሉቃ 4፣2)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም *«በድካምና በጥረት፣ ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም በብርድና በራቁትነት ነበርሁ» ይልሃል።* (2 ቆሮ 11፣27)

ስለ ቅ. ጴጥሮስ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ም 10.ቁ 10 ላይ «ተርቦም ሊበላ ወደደ» የሚል ተጽፎልሃል። እና ወንድሜ ረሀብን በጾምህ ተምረኸዋል?

በተራብክ ጊዜ ደካማነትህን ትረዳለህ። በኃይልህ መመካትህ ይቀራል። በእግዚአብሔርም መደገፍ ትጀምራለህ። እየራበህ ሳለህ ስትጸና ትዕግስትና ራስን መግዛት የተባሉትን የመንፈስ ፍሬዎች እያፈራህ ነው። ስለዚህ እየጾምክ ሳለህ የረሀብ ስሜት ስለተሠማህ አትብላ። ይልቁንም ትዕግስትና፣ ጽናትን፣ ራስን መግዛትን ተማርበት። የረሀባቸውን ዋጋ በትዕግስት ካገኙ አባቶች በረከት ተካፈል። ከዚህም በላይ በረሀብህ ምንም የሚቀምሱት ምግብና መጠጥ አጥተው የሚሠቃዩ ወገኖችህን ስቃይ ታስብበታለህ - ትረዳበታለህ። ታዝንላቸዋለህ፣ ባትጾም ትበላው የነበረውን ትሠጣቸዋለህ። እና ወንድሜ ለተወሰኑ ሰዓታት ከምግብ መከልከል ማለት ይህ ነው። ወደሚቀጥለው እንለፍ - ተከተለኝ።

## ❖ ከሥጋ ፍላጎቶችህ መታቀብ

ስለአስፈለገህ ብቻ አታድርገው ዳንኤል ይጾም ስለነበረው ጾም የተናገረውን አስታውስ።

ይህ ባይሆን ግን *«በሣምንት ሁለት ቀን እጾማለሁ »* እያለ ሲታበይ እንደነበረውና ያለ ዋጋ እንደተመለሰው ፈሪሳዊ በከንቱ ትቀራለህ። (ሉቃ 18፥11) ትሕትና በሕይወትህ ከሌለ ጾምንም ከክርስቶስ አልተማርክም ማለት ነው።

*«ከእኔ ተማሩ፤እኔ የዋሕ በልቤም ትሑት ነኝና»* (ማቴ 11፥29)

*«ወደእኔ ተመለሱ፤ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ»።* (ኢዩ 2፥13)

እነዚህን ሁሉ መሠረት በማድረግ በጾም ተጠቅመህ ወደላይኛው ደረጃ ከፍ እንደምትል እምነቴ ነው። ይህም ፍጹም ይሆን ዘንድ ጾምህ የግብዝነት አይሁን።

## ❖ ጾምህ ከበጎ ሥራ ሁሉ የተባበረ ይሁን

ጾምህ በእርግጠኝነት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስህ መንገድ መሆኑን የምታምንበት ይሁን።

## ጾምህ የልማድ አይሁን

ወንድሜ ስለጾም እንደዚህ በአጭሩ ማስፈር ቢከብድም አንተ ግን ይህን መነሻ በማድረግ ሌሎች የእግዚአብሔር ቃል የሆኑትን መጻሕፍት እንድትመረምር ማድረግ በመቻሉ በኩል ይበቃል እላለሁ። በቀረው ራስህ እየጾምክ - ከጾምህ ተማር።





# ምዕራፍ ፯

## ምጽዋት /ሥጦታ/

*«ከሚቀበል ይልቅ የሚሠጥ ብፁዕ ነው።»* (ሐዋ 20 ፥35) ጌታችን ለምን መስጠትን መረጠ?

## ❖ መስጠት የፍቅር መግለጫ ነው

ምጽዋት ያለህን ከሌላቸው ጋር የምትካፈልበት ፍቅራዊ ተግባር ነው። ፍቅር ያለው እግዚአብሔር አለውና ይህ ምጽዋት ወደ እግዚአብሔር የሚወስድህ ሌላው መንገድ ነው። መስጠት፡- ያለህን ከእግዚአብሔር ጋር መካፈል ነው ብልህ ይደንቅህ ይሆን? ሊደንቅህ አይገባም። ለምን? ጌታችን ራሱ ስለተናገረው።

*«ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፤ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና. . .»* ከዚህ የሚቀጥለውን ወርቃማ ቃል ልብ በለው *«. . . እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት. . .»* (ማቴ 25፥35-40)

ስለዚህ አንተም ከሌላቸው ወንድሞችህ ጋር የተካፈልከው እያንዳንዱ ጥሪትህ ለአምላክህ እንዳደረግኸው ሆኖ መንገድ ይሆንሃል።

ወንድሜ፡- መስጠት እጅግ ጥንቃቄ ልታደርግበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ለጽድቅ ያሰብከው መርገምን ሊያተርፍም ይችላል ። ለምሳሌ ራበኝ ለሚልህ አንተ የማትበላውን ብትሰጠው ፤ በረደኝ ለሚልህ የማትለብሰውን ብትሰጠው መስጠት ሳይሆን በማጣቱ ላይ መመጻደቅና የበላይነትህን ማሳየት ነው። ምጽዋት ወይም መንፈሳዊው ስጦታ ግን ያለህን ማካፈል -ማለትም ከምትበላው ማብላት ፤ ከምትለብሰውም ማልበስ ነው።

*«እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው»* (ማቴ 7፥12)

ምጽዋት በዚህ ብቻ የተሰወነ ሳይሆን በሀሳብ ለተቸገረ፤ ማህበረሰቡ ላገለለው፤ በሽታ ላጠቃው ለመነሰሰው ሁሉ ፍቅር መስጠት / ማካፈል ነው። ለተጨነቀ፤ መፍትሔ ላጣ፤ መላ መጠቆም መውጫ ማሳየት ሁሉ ያለህን ማካፈል ነው።

ምጽዋት ያለህን ብቻ ሳይሆን አንተነትህን ለሌሎች መስጠት ነው:: ለራሱ ብቻ በመኖር ከክርስትና ጀርባ የቆመ ሰው መቀበልን እንጂ መስጠትን አያውቅም:: ራሱን ያገለለው ደግሞ አይቀበልም አይሰጥም:: ማህበራዊ ሕይወትን በግርድፉ የሚኖረውም የሚቀበል -የሚሰጥ ነው:: ክርስቲያን ግን መቀበሉን ሳያስብ የሚሰጥ ነው:: ቢሰጥም ከራሱ የተቀበለውን ነው:: ወይም ነገ የሚጠብቀው ምላሽ ሳይኖር ነው:: ምክንያቱም እውነተኛው ክርስትና «እኔ» ሳይሆን «እኛ» እያሉ የሚኖሩት ሕይወት ነው :: ይህ ዓይነቱ ሥነ ምግባር ደግሞ ራስን የመካድ ደረጃ ላይ ለደረሱ የሚቻል ስለሆነ በጀመርከው ጉዞ ቀጥልበት:: «በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» (ማር 8፣ 34) ክርስቶስን የተከተለ ሰው ግላዊነት ያጠቃው ሊሆን አይችልም:: ወንድሞቼ፣ ወገኖቼ ማለት የቻለ ብቻ እውነተኛ ክርስቲያን ነው::

እጅግ ረሀብ በጸናበት ዘመን ላይ ሆና፣ ካላት ትንሽ ነገር ላይ አካፍላ ለኤልያስ የሰጠችውን፣ እግዚአብሔርም ቤቷን በበረከት የሞላላትን የሰራፕታዋን መበለት ተግባር አስተውል:: (1ነገ17፣11-19) የሰጠችው የተረፋትን ወይንም የማትፈልገውን አይደለም:: ልጇና እሷ በልተዋት ለሞት ከተዘጋጁባት ጥቂት ዱቄት ከፍላ እንጎቻ አድርጋ ሰጠችው:: ማካፈልና እኛ ማለትን የሚያውቁትን የእግዚአብሔር በረከት ይጎበኛቸዋል

ጌታችን ከሁሉ የሚበልጥ ስጦታ እንደሰጠች የመሠከረላት መበለትስ ምን ዓይነት ስጦታ አቅርባ ነው? (ሉቃ 21፣1-4)

«ዐይኑንም አንስቶ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለጠጎችን አየ አንዲትም ድሃ መበለት ሁለት ሳንቲም በዚያ ስትጥል አየና:- እውነት እላችኋለሁ፣ ይህች ድሃ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች:: እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና:: ይሕች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አለ::»

እንግዲህ መስጠት ከማግኘት ከማትረፍ አይደለም ማለት ነው:: ከዚህች መበለት በቁጥር በመጠን አብልጠው የሰጡ አሉ:: ያላትን በመስጠት ግን ይህች መበለት በለጠቻቸው:: ምክንያቱም እነርሱ ከትርፋቸው ሰጥተዋልና:: የዚህች መበለት ተግባር ከላይ የሰፈረውን ሁሉ በጉልህ አንጸባርቆ የሚያሳይ ነው» ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም መኖርን የሚያስተምር ነው:: ደግሜ እልሃለሁ «ክርስትናም ፍቅር ነው:: እንደ ቅዱስ አባት ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እንደነቅዱስ ባስልዮስ የድሆች ቁስል ከተሰማህ ረሀባቸው ከራበህ አንተ ክርስቲያን ነህ:: እስከ መስዋዕትነት ለመድረስ ከችግረኞች ጎን ከቆምክ፣ የሚያስፈልግህ ሁሉ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ካመንክ እውነትም የክርስቶስ ተከታይ ነህ::





- እግዚአብሔር የሥጦታህን ብዛት ሳይሆን ምንጩን እንደሚመለከት ተማርክ? ለጋስነትን ለማሳየት ከሚደረግ ዕልፍ ምጽዋት በፍቅር የሆነች አንድ ሳንቲም ልዩ ሥፍራ አላት:: የምትሰጠውንም ሰው ስጦታህንም እየወደድክ አድርገው:: ከአንተ እንዲወጣ ብቻ ወይም እንደግዴታ ቆጥረኸው ብትሠጥ ወደ እግዚአብሔር አይወስድህም:: ደስ እያለህ ለመንፈስህ እርካታ የሚሆን ስጦታን ስጥ::

## ❖ በደስታ የሚሰጥን እግዚአብሔር ይወደዋል

«እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጥን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ:: በኃዘን ወይም በግድ አይደለም::» (2ቆሮ 9፣7)

ችግረኛን ለመርዳት ስትነሳ በፍቅር ተገፍተህ ተነሳ:: ራሱ ችግረኛው ሰው ከምትሰጠው ስጦታ ይልቅ ያሳየኸው ፍቅር ደስ ያሰኘዋል:: ፍቅር አልባ ስጦታ ብትሰጠው ግን የጠቀምከው እየመሰለህ ስሜቱን ታቆስለዋለህ:: ስላለህ ወይም ከማግኘት ተነስተህ የምትሰጠው ቢሆን ታናሽነቱን በሌላ ቋንቋ እየነገርክ ትጎዳዋለህ:: ስለዚህ በልጁ ደስታ ለመደሰት የአቅሙን ሁሉ እንደሚያደርግ ደግ አባት በፍቅር ደስ እያለህ ስጥ:: ለወንድምህ ያደረግኸው ለእግዚአብሔር እንዳደረግኸው ይሆንልሃልና:: በዳዊት ዘመን የእግዘአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ሕዝቡ ሁሉ ያላቸውን ሲሰጡ የነበራቸውን ደስታ መጽሐፍ ቅዱስ ያስነብብሃል::

«ሕዝቡም ፈቅደው ሰጥተዋልና፣ በፍፁም ልባቸውም ለእግዚአብሔር በፈቃዳቸው አቅርበዋልና ደስ አላቸው:: ንጉሡም ዳዊት ደግሞ ታላቅ ደስታ ደስ አለው::» (1ዜና 29፣9-16)

ዳዊት ከደስታው ብዛት ከእግዚአብሔር ጋር የተነጋገረበት ይህ ቃል ደግሞ እጅግ ታላቅ ትምህርትን የሚሰጥ ነው::

*«ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና፣ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና ይህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማን ነኝ ?ሕዝቤስ ማን ነው?. . .አቤቱ አምላካችን ሆይ ለቅዱስ ስምህ ቤት እንሰራ ዘንድ ይህ ያዘጋጀነው ባለጠግነት ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው ሁሉ የአንተ ነው:: አምላኬ ሆይ ልብን እንድትመረምር ቅንነትንም እንድትወድ አውቃለሁ:: እኔም በልቤ ቅንነትና በፈቃዴ ይህን ሁሉ አቅርቤአለሁ:: አሁንም በዚህ ያለው ሕዝብ በፈቃዱ እንዳቀረበልህ አይቻለሁ. . .»*

እባክህ ይህን የተወደደ ቃል ጨርሰህ፣ ደጋግመህ አንብበው:: ወንድሜ ዛሬም ከአጠገብህ እየፈረሰ ያለው የእግዚአብሔር ቤት የሰው ልጅ ነው:: (1ቆሮ 3፣16) እናም በፈቃድህ ደስ እያለህ ፣ እግዚአብሔር የሰጠህን ስጠው:: ከሌለህ

ፍቅርህን መግበው:: ለመሆኑ ይህን እጅግ ውብ የሆነ ቃል አስተውለኸዋል? «ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና. . . .»

ልብ በል! የራስህ የሆነ አንድም ነገር የለም:: አንተ የእግዚአብሔር ነህ:: ያለህም ከእርሱ የተሰጠህ ነው:: (ኢሳ 43:1) የኢዮብንም ቃል በልብህ መዝገብ አኑረው:: «ራቁቴን ከእናቴ ማህፀን ወጥቻለሁ:: ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ:: እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሳ:: የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» (ኢዮ 1፣21)::

ስለዚህ አንተም እንደነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች እያሰብክ የምትሰጠው የተቀበልከው መሆኑን ዐውቀህ ስጥ::

❖ ግን እግዚአብሔር :- ድንቅ መካር ኃያል ሲሆን ከእኛ ከደካሞቹ ሊቀበል መፍቀዱ አይገርምህም? :: አቤት ትሕትና ! ዳዊት ይህ ነገር ቢያስገርመው «እኔ ማን ነኝ» ማለቱን አይተሃል:: እግዚአብሔር ሀሳባችንን እንድንገልጽ ዕድል ሠጠን:: ልክ ከሕፃን ልጁ ስጦታን እንደሚቀበል አባት አስበው:: ልጁ እያደረገ ያለው የፍቅር ስሜቱን መግለጽ ነው:: ስጦታው ግን አባቱ ከሠጠው -የተቀበለው ነው:: ዳዊትም «ከእጅህ የተቀበልነውን ሠጠንህ» ያለው እንደዚሁ ነው::

እግዚአብሔር መስጠትን የሚያስተምርህ እየሰጠ ነው :: ሕይወትን ሰጠህ፣ የሕልውናህም ዋስትና እርሱ ነው:: ሕይወትህን ለለአግባብ ብትመራው አሁንም በፍቅሩ ዋጀህ:: ዛሬ አንተ ያለህን ብትሰጥ ሕይወትህን ሰጠህ ይባላል:: ነገር ግን ሕይወትህም ከእርሱ የተቀበልከው ነው:: ስለዚህ አምላክህን «ጤናና ጉልበት ስጠኝ፣ እኔም የሰጠኸኝን በመስጠት አገለግላለሁ::» እያልክ ለምነው::

«አምላኬ ሆይ አንተን ለማገልገል ብነሳ ለአንተ የምጨምርልህ አንዳች ነገር እንደሌለ አምናለሁ:: ምክንያቱም ጤናውም ጉልበቱም ዕውቀቱም ያንተው ናቸው:: ከመነሻው ለአገልግሎትህ ያደረብኝ ፍቅር ከአንተው ነው:: እኔም ራሴ ያንተው ነኝ:: በሰጠኸኝ ሕይወት አንተን አገለግላለሁ:: ለድሆች፣ ለችግረኞች መጽናኛ እሆን ዘንድ አሁንም ቃልህን ስጠኝ:: የሠጠኸኝንም እንድሰጥ እርዳኝ::» በለው

## <u>እንዴት መስጠት አለብህ</u>?

### ❖ ክብርን ለመፈለግ አትስጥ

በአንደበትህም ይሁን በልብህ፣ በስሜትህም ይሁን በሀሳብህ የራስህ ነገር ኖሮህ እንደሰጠህ አስበህ አትኩራራ:: ለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን እንደትልቅ ማስረጃ ተጠቀም:: *«አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልክ ከሆነ ግን እንዳልተቀበልክ የምትመካ ስለምንድር ነው?»* (1 ቆሮ 4፣7)





ስለዚህ ስጦታ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተቀብለን የምንሠጠው እንጂ የራሳችን እንደሆነ በከንቱ የምንመካበት አይደለም::

### ❖ ስጦታህ (ምጽዋትህ) በምስጢር ይሁን

*«አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን፣ ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ:: በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል::»* (ማቴ 6፣4)

እግዚአብሔር ያለህ ምጽዋትህ ከሰዎች እንዲሰወር ብቻ ሳይሆን ከአንተም ከራስህ ጭምር ነው:: ይህን ያህል ሰጠሁ፣ ይህን አደረግሁ እያልክ እንዳትቆጥርም ነው:: የምትችለውን ሁሉ እያደረግህ ምንም እንዳላደረግህና ብዙ እንደሚቀርህ ካልተሰማህ ዲያብሎስ እየፈተነህ ነው:: ይልቁንም ዋጋህ ሁሉ በምድር እንዳይቀርብህ ጥንቃቄ አድርግ::

### ❖ በልግስና ስጥ

«የሚሠጥ በልግሥና ይስጥ» ሮሜ 12፣8:: ይህ ቀደም ሲል እንደ ግዴታ ቆጥረህ መስጠት እንደሌለብህ የተነጋገርነውን ለማጽናት ቅዱስ ጳውሎስ የሚናገረው ነው:: *«እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፣ መልካምን እንዲያደርጉ፣ በበጎም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ፣ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው፤፤» እያለ የመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስን ሲያበረታታም ታገኘዋለህና አንተም ይህን በመሰለው ሁሉ በርታ::* (1ጢሞ 6፣18)

*«በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፣ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል::»* (2ቆሮ 9፣6):: እነዚህን ቃላት ጌታችንም ለአንተ በሚገባህ መልኩ እንዲህ ሲል አስቀምጦልሃል:: *«ስጡ ይሰጣችሁማል፣ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና . . .»* (ሉቃ 6፣38)

እንግዲህ ስጦታን (ምፅዋትን) መስጠት ብቻ ሳይሆን ቸር መሆን ይጠበቅብሃል:: ምሳሌ ይሆንህ ዘንድ የዳዊትና የኦርናን ውይይት አስተውል:: ዳዊት ለእግዚአብሔር መሠዊያን ይሰራ ዘንድ ከኦርና አውድማውን ለመግዛት ፈለገና ጠየቀው:: *«መቅሠፍቱ ከሕዝቡ ላይ ይከለከል ዘንድ አውድማውን ከአንተ ገዝቼ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ልሠራ ነው»* አለው:: ኦርናም ዳዊትን ጌታዬ ንጉሡ እንደወደደ ወስዶ ያቅርብ፣ እነሆ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎች፣ ለሚቃጠል እንጨት የአውድማ ዕቃና የበሬ ቀንበር አለ:: ይህን ሁሉ ኦርና ለንጉሡ ይሰጣል አለው:: ኦርናም ንጉሡን:- አምላክህ እግዚአብሔር ይቀበልህ አለው::- - -» (2ሳሙ 24፣22):: ዳዊት ኦርናን የጠየቀው በሽያጭ ሲሆን ኦርና ግን በልግስና ሊሰጠው ወደደ:: ምክንያቱም ይህን ሁሉ ከእግዚአብሔር የባሕርይ ልግስና የተቀበለው እንደሆነ ያምናልና:: ነገር ግን ዳዊት ያለዋጋ መሥዋዕት ሊያቀርብ ስላልወደደ እንዲሸጥ ግድ

አለው (2 ሳሙ 24፤ 24-25) ነገር ግን ሁለቱም ያላቸውን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ደስተኞች ለጋሶችና ቸሮች ነበሩ።

ከዚሁ ጋር የአብርሃምንም ደግነት፣ እንግዳ ተቀባይነት አስታውስ። (ዘፍ 18፤6-8) ለአብርሃም መካፈል የደስታ ምንጩ ነበር። የደከመን ስለሚያሳርፍ የተራበን ስለሚያበላ፣ ሁሉን በእኩልነት ስለሚቀበል የዘለዓለም አምላክ ሥላሴ በቤቱ ተስተናገዱለት። እርሱ ለማንም ሊሰጠው የማይችለውን ታላቅ ስጦታ ልጁን ይስሐቅን ከሥላሴ ተቀበለ። ነገር ግን ልጁንም ቢሆን ለእግዚአብሔር ለመስጠት አላመነታም። ከእርሱ የተቀበለው ነውና። «አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ። . . .» ዘፍ 22፤1-19)

ወንድሜ አንተም ለተቸገሩ ቸርና ለጋስ ሆነህ እግዚአብሔር አብልጦ እንደማይሰጥህ መርምር (ሚል 3፤10)። ባለህ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ኑር። «እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር ከፍሬህም ሁሉ በኩራት፣ ጎተራህም እህል ይሞላል። መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች።» (ምሳ 3፤9)

❖ ያለህን መስጠት፣ በሙሉ ልብህ ክርስቶስን መከተል የምትችልበት ምስጢር ነው።

«ፍፁም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ።» (ማቴ 19፤21)። ሌላም ጌታችን ያለህ አለ። «ያላችሁን ሸጡ፣ ምጽዋትም ስጡ። ሌባ በማይቀርብበት፣ ብልም በማያጠፋበት በሰማያት የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ። መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚያ ይሆናል።» (ሉቃ 12፤33)

❖ <u>ምጽዋትህን ፍፁም ለማድረግ</u>፦ በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉ እንዲመለስልህ የምትጠብቀው ነገር አይኑር። ለመስጠት ስታስብም መጠየቅን አትጠብቅ። ብቻ የአንተ የሆነው የወንድምህ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር እንደሆነ እያሰብክ ለሚያስፈልጋቸው፣ የተቻለህን አድርግ። (ሉቃ 3፤11)

እግዚአብሔር ለእኛ ሳንለምነው የምንሻውን ዐውቆ የሚሰጠን አምላክ ነው። እናት የልጇን ፍላጎት ዐውቃ አስቀድማ እንደምታደርግለት ያለ ነው። አምላክህ ከአንተም የሚጠብቀው ይህንን ነው። በፍቅር የሠጠህን በፍቅር ስጥ። አንተም ለወንድም እህቶችህ እንደዚሁ አድርግ።

❖ **ለመስጠት ቀጠሮ አያስፈልግህም**፣ ወይም አትዘግይ። ምናልባትም ባንተ መዘግየት ለአደጋ የሚጋለጥ ሕይወት ይኖራልና። ጥበበኛው ሰሎሞን ይህን በተመለከተ የተናገረውን ስማ። «ለተቸገረው ሠው በጎ ነገርን ማድረግ አትከልክል፣ ልታደርግለት የሚቻልህ ሲሆን፣ ወዳጅህን ፦ ሂድና ተመለስ ፤ነገ እሰጥሃለሁ አትበለው ።» (ምሳ 3፤27)





## ምጽዋት ብዛት ወይስ ጥራት?

❖ የማትፈልገውን ሳይሆን ለአንተ ምርጥ የምትለውን መስጠት ልመድ። የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ ልብስ፣ ለመመገብ አስቸጋሪ የሆነ፣ የሻገተ ወይንም የደረቀ ምግብ መስጠት የተለመደ በሆነበት ዘመን ላይ ስላለህ የምታደርገውን ሁሉ ተጠንቅቀህ አድርግ። አንተ የማትለብሰው ስለማይለበስልህ ነው። የማትበላው በጤናህ ላይ ችግር ስለሚያስከትልብህ ነው። ታዲያ ወንድምህስ? የምትሰጠው ለሕመም የሚዳርገውን ነው? መሆን የለበትም። ይልቁንም ለወንድምህ ከምትበላው አካፍለው። ከምትለብሳቸው ሁለቱ ልብሶች አንዱን ስጠው። የሚጎዳውን ብዙ ነገር ከምትሠጠው የሚጠቅም ትንሽ ነገር ስጠው። ለአንተ የምትመኘውን ጥራት ለወንድምህም አድርግ። «ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው» ያለውን የእግዚአብሔር ቃል መለስ ብለህ አስብና፣ የምትሰጠውን ጎጂ ነገር ለክርስቶስ እንደምትሰጠው ተረ።

ከዚሁ ጋር አቤልና ቃየል ለእግዚአብሔር ያቀረቡት መሥዋዕት እንዴት እንደነበረ አስብ። «አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኩራትን ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ።» (ዘፍ 4፤4) ለምን መረጠለት? ብትል ፤ ካለው ሁሉ መርጦ የተሻለውን ስላቀረበ ነው። በሐዋርያት ሥራ 4፤34-35 ላይ ሠፍሮ የሚገኘውን የሐዋርያቱ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበረ የሚናገረውን ቃል አስተውለህ አንብበውና የአንተ ምጽዋት የአንተ ሥጦታ የትኛው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ራስህን ጠይቅ።

## <u>የእግዚአብሔር ድርሻ</u>

እግዚአብሔር ያለህን የሚካፈልህ ሊጠቀምበት ሳይሆን ሊባርክልህ ነው ። ለአንተ የማግኘትህ፣ የሀብትህም ምንጭ እርሱ ነው። ከበጎ ተግባር ሁሉ ተካፋይ ትሆንለት ዘንድ ይካፈልሃል። ስትሠጠው ልትጠቅመው ሳይሆን እውነተኛ ሥጦታን፣ ፍቅርን ሊያስተምርህ ነው። ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው ጌታ በአንተ አቅም የምትሠራው ትንሿ ነገር ታስደስተዋለች። ለእግዚአብሔር በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሳያጣ የሚቀበልህን የእግዚአብሔርን ትሕትና ትማራለህ። እርሱ ትሑት ስለሆነም አንተም ትሑት ትሆናለህ (ማቴ 11፤29)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን ስጦታና ሀብት በአሥራት በበኩራት መልክ ድርሻው አድርጎ ይቀበላቸው እንደነበረ እናስታውሳለን። እነዚህ ከየት አምጥተው መሥዋዕት አቀረቡ? እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነው። በቅንነት በፍቅር ያደረጉትን ወድዶ ተቀብሏቸዋል። ዛሬም በክርስትና ውስጥ አድጎ የምታገኘው ይህንኑ ነው። ክርስቶስ ራሱን ሰጥቶ መስጠትን አስተምሮሃል። ለሰው ሕይወቱን ከመስጠት ሌላ ምን ነገር ይኖረዋል? ሁሉን ያደረገው ሁሉን መስጠት

ያስተማረው ጌታ ድርሻው አድርጎ የጠየቀህ ግን እጅግ በጣም ቀላሉን ነው፡፡ ቀጣዩን ነጥብ ተመልከት፡፡

## *አሥራት*

ሕግ ከመፃፉ በፊት ሕግ ከመጻፉም በኋላ ትውፊትን መሠረት አድርጎ ሲተላለፍልን የቆየ እግዚአብሔርን የመታዘዣው መንገድ አሥራት ነው፡፡ ስለ አሥራት ከአባታችን ያዕቆብ የሰማነው ምንድን ነው?

ያዕቆብ ባደረበት ሥፍራ ላይ መሰላል በምድር ላይ ቷተክሎ ራሱም ወደሰማይ ደርሶ የእግዚአብሔርም መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት ተመለከተና እንዲህ አለ፡፡ «. . .እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፣ በምሄድባትም በዚህች መንገድ ቢጠብቀኝ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፣ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል፡፡ ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፡፡ ከሠጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጣለሁ፡፡» (ዘፍ 28፣1-22) ያዕቆብ አሥራትን አባቱ ለመልከጼዴቅ እንዳቀረበ በትውፊት ተላልፎለት አግኝቶ ነው፡፡ (ዘፍ 14፣20) «አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው»

### ❖ በእግዚአብሔር የታዘዘ ነው

ሙሴ ሕዝበ እሥራኤልን ይመራ በነበረበት ዘመን ላይ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡፡ *«ከእርሻህ በየዓመቱ ከምታገኘው ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ»* ( ዘዳ 14፣22)

«የምድርም አሥራት፣ ወይም የምድር ዘር ወይም የዛፍ ፍሬ ቢሆን የእግዚአብሔር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፡፡» (ዘሌ 27 ፣30) *«የእህልህን፣ የወይን ጠጅህን፣ የዘይትህንም አሥራት፣ የላምህንና የበግህንም በኩራት፣ የተሳልኸውንም ስእለት ሁሉ፣በፈቃድህም ያቀረብከውን በእጅህም ያነሳኸውን ቁርባን በደጆችህ ውስጥ መብላት አትችልም፡፡»* ( ዘዳ 12፣17/ ዘዳ 14፣23)

በአጠቃላይ ይህንን ሁሉ ቀራጮ እንዲህ ሲል በአጭሩ አስቀምጦታል፡፡ «ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ፡፡» (ሉቃ 18፣12)
ያዕቆብንም መላልሰህ አስበው *«ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር አንዱን እሠጣለሁ፡፡»* (ዘፍ 28 ፣22)

### ❖ *አሥራት የማይሠጥ እግዚአብሔርን እንደሰረቀ ይቆጠራል*

«ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃል? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል፡፡ እናንተም የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል፡፡ በአሥራትና በበኩራት ነው» (ሚልክ 3፣8-10)





### ለእግዚአብሔር የማይሰጥ

ሁሉን በፍቅር ለሚሰጥ ለእግዚአብሔር የማይሰጥ ነገር ቢኖር የአመፃ ገንዘብ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ፣ በቀሚያ፣ ድሃን በመበደል፣ ከሕጋዊ ባሰቤቱ በመንጠቅ የመጣ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ይጸየፈዋል፡፡ እግዚአብሔር በባሕርዩ ንጹሕ ነውና ንጹሕ ነገር ይወዳል፡፡ በወንጌል ያስተማረንም ይህንን ነው፡፡

*«የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘለዓለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ»* (ሉቃ 16፣9)

አሥራት የምትሠጠው ብዙ ስላለህ ብቻ እንደሆነ አታስብ፡፡ ያላትን ሁሉ የሠጠችውን መበለትም አትርሳት (ሉቃ 21 ፣4)

### የስጦታህ <u>ትንሹ አሥራት</u> ነው

አሥራት በመሠረቱ ከእሥራኤላውያን ወይም ከብሉይ ኪዳን የመጣልን ነው፡፡ ለእኛ ለክርስቲያኖች ግን ከዚህም በላይ የሚጠበቅብን አለ፡፡ *«ለሚለምንህ ስጥ»* (ማቴ 5፣41)

*«ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፡፡. . . ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፡፡»* (ማቴ 6፣19) ስለዚህ አንተም አሥራትን በማውጣት አትገደብ ፡፡ የተቸገሩትን እርዳ፡፡ የተራቡትን አብላ፡፡ የታረዙትን አልብስ ፡፡ በአጠቃላይ በበጎ ሥራ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሁን ፡፡ አሥራትን አውጥቻለሁና የሚገባኝን ፈጸምኩ ብለህ አታስብ፡፡ እንደዚህ ካሰብክ ለችግረኛው ጩኸት ጆሮህ የተዘጋ ይሆናል፡፡ አንተ ሰሚ ካልሆንክ ደግሞ እግዚአብሔርም አይሰማህም፡፡ *«የድሃውን ጩኸት እንዳይሠማ ጆሮውን የሚደፍን ሠው፣ እርሱ ራሱ ይጮኻል፣ አይሰማለትምም»* (ምሳ 21፣13) ፍቅርህ በልብህ ፍጹም ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ሂሳብ አትስራ፡፡ በጎ ሥራ የመሥራትን ዕድል ባገኘህበት አጋጣሚ ሁሉ ልብህ ክፍት ይሁን፡፡

### ❖ ምጽዋትህ ከቀራጩ የበለጠ ይሁን

ክብር ምሥጋና ለእርሱ ይሁንና ጌታችንም የተናገረህ ይህንኑ ነው፡፡
*«ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ካልበለጠ ወደመንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም»* (ማቴ 5፣20) ፡፡ ጻፎችና ፈሪሳውያን አሥራት ያወጡ ምጽዋት ይሰጡ እንደነበረ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ህግን በቃል ብቻ የምትተረጉም እንዳትሆን በምፅዋትህ፣ በፍቅር ስጦታህ ከእነርሱ የምትበልጥ ሁን፡፡ ፍጹምነትን ስትሻ ሁሌም ከድሆች እንደሚያገናኝህ አትዘንጋ (ማቴ 19፣21)

አሥራት በንብረትህ ውስጥ ብቸኛው የእግዚአብሔር ድርሻ አይደለም። ስለዚህ ስለሌላኛውም እንነጋገር።

## በኩራት

በኩራት ማለት እግዚአብሔር ከሰጠህ ሁሉ ላይ የመጀመሪያውን ለእርሱ መስጠት ማለት ነው። አቤልም ያደረገው ይህንኑ ነበር። (ዘፍ 4፡4) የሚገርምህ ደግሞ የተጻፈለት ሕግ ሳይኖር ነው ይህን ያደረገው። ምርጡን መረጠ፣ የመጀመሪያውን ለየ፣ ለእግዚአብሔርም ሠጠ። ስለዚህ እግዚአብሔር በሺኬል ፍቅር ደስ አለው። አሁን ግን ለእኛ የተጻፈልን የበኩራት ሕግ አለ።

«በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማህፀንን የሚከፍት በኩር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ የእኔ ነው።» (ዘጸ 13፡2) ። ከሰው በኩር የሆነ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል ይለይ ነበር። ኋላ በአሮንና በሌዊ ቤተሰብ ከመተካቱ በፊት ማለት ነው። ከእንስሳም በኩር የሆነው የእግዚአብሔር ነበረ፣ ነውም።

### ❖ በኩራት ከአሥራት የበለጠ ሥጦታ ነው

ምክንያቱም አሥራት ካለህ ሁሉ ከአሥር አንድ እጅ መስጠት ማለት ነው። (100 ብር ቢኖርህ 10 መስጠት እንደማለት)። በኩራት ግን በመጀመሪያ ያገኘኸውን ያለህን ብቸኛ ነገር መስጠት ማለት ነው።

ለምሳሌ ሐና አንድ ብቸኛ ልጅ ሳሙኤልን ወለደች፣ እሱን ለእግዚአብሔር ሠጠች። ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ዮሐንስን ብቻ በብዙ ስለት ወለዱ እሱን ሰጡ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለእመቤታችን አንድና ተከታይ የሌለው ልጇ ሲሆን እሱም ለራሱ ለመስዋዕትነት ቀረበ። የጌታችን በኩርነት ግን ተከትሎት የሚወለድ ኖሮ ሳይሆን፣ ለእናቱ በዘመን ሁሉ አንድ ልጇ ነው። በዕብራውያን /በእሥራኤላውያን ባህል ደግሞ ለበኩር ልጅ የሚሠጠው ደረጃ ፍቅርና ክብር ልዩ ነው። እና እነዚህን ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት እግዚአብሔርን ከሁሉ ነገር በላይ ማስቀደም፣ ማክበር ማለት ነው። ስጦታውም ከሥጦታዎች ሁሉ የሚበልጥ ሥጦታ ነው። የበኩራት ሕግ በበኩር ልጅ ስጦታ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የምድርን ዘር ፍሬ ከእፅዋት ከአትክልት የሚገኘውን ሁሉ የሚጨምር ነው።

*«የተመረጠውን የምድርህን ፍሬ በኩራት ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጣ »* (ዘጸ 23፡19)

*«ወደ ምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ፣ መከሩንም ባጨዳችሁ ጊዜ የእናንተን መከር በኩራት ነዶ ወደ ካህኑ አምጡ። እርሱም ነዶውን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሠምርላችሁ ይወዝውዘው»* (ዘሌ 23፡10) ፣ዘዳ 26፡2-10።





### ❖ የእንስሳንም በኩር ለመስጠት ታዟል

*«ማሕጸንን የሚከፍተውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለይ፣ ከሚሆንልህ ከብት ሁሉ ተባት ሆኖ አስቀድሞ የተወለደው ለእግዚአብሔር ይሆናል።»* (ዘዳ 13፡12)፣ (ዘዳ 34 ፡19)

የመጀመሪያህን (በኩርን) ለእግዚአብሔር ሰጠህ ማለት እግዚአብሔርን የመጀመሪያህ አደረግህ ማለት ነው። ስለዚህም ያለህ ሁሉ በእግዚአብሔር የተባረከ ይሆናል።

❖ በዚህ ባለንበት ዘመን ላይ የበኩራትን ሕግ እንዴት መፈጸም ይቻላል? ሕዝቡ ሁሉ በግብርና የሚተዳደርና የምድርን ፍሬ የሚሰበስብ አይደለም። ሁሉም ከብትና በግ እርቢ ነው ማለትም አይቻልም።

## ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን?

ለምሳሌ ተቀጣሪ ሠራተኛ ከሆንክ ከደመወዝህ የመጀመሪያውን እንደ በኩራት ለእግዚአብሔር መስጠት ትችላለህ። ነጋዴ ብትሆን የመጀመሪያ ትርፍህን መስጠት ትችላለህ። የመጀመሪያ የደመወዝ ጭማሪህን፣ የመጀመሪያ የትርፍ ሰዓት ክፍያህን፣ የመጀመሪያ የማነሳሻ ክፍያህን ለእግዚአብሔር ከሰጠህ የበኩራትን ሕግ ፈጸምክ ማለት ነው።

## ስእለት

ስእለት ከአሥራትና ከበኩራት በዓይነቱም በአፈጻጸሙም የተለየ ሥጦታ ነው ። ይህ አንተ ለእግዚአብሔር የገባኸውን ቃል የምትፈጽምበት ነው። በጭንቅ በመከራ ውስጥ ሆነህ ችግሮች እንዲቀሉልህ፣ እንዲያልፉልህ ለእግዚአብሔር ትሳላለህ። ተፈጽሞልህ ስታገኝ የገባኸውን ቃል ማለትም እሰጣለሁ ያልከውን ትሰጣለህ ። ስእለት ማለት ይህ ነው።

የተሳልከውን ሳታዘገይና ሳትለውጥ ስጥ። *«ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ የተሳልከውን ፈጽመው። ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባትሳል ይሻላል»* (መክብብ 5፡4-5)

ስእለት የገንዘብም የእውቀትም የሕይወትም መሆን ይችላል። ልትፈጽመው የማትችለውን ግን በፍጹም አትሳል። ከዚህ ይልቅ ፍላጎትህን ለእግዚአብሔር ገልጸህ በመንገር እንዲፈጽምልህ መለመን ይመረጣል። «ጌታዬ ሆይ እኔ ይህን አስባለሁ። መፈፀም መቻሌን ግን እጠራጠራለሁ። እኔ ደካማ ነኝና የሀሳቤን የማደርግበት ኃይልን አንተ ስጠኝ - - -» ብለህ ጠይቀው።

### ቁርባን /መባ/

ቤተ ክርስቲያን መባን ለሚያገቡ ሰዎች ሁሌም ጸሎት ማድረግዋን አታቋርጥም። ከዚህ ቋሚ ጸሎት አንተም ድርሻ ሊኖርህ ይገባል።

*«ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንለምናለን። ከሁሉ በላይ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን መባ ስለሚያገቡ፣ መሥዋዕቱን፣ ቀዳምያቱን ከአሥር አንዱን የመታሰቢያ ምሥጋና ብዙውና ጥቂቱን የተሰወረውና የተገለጸውን ይሰጡ ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጥ ዘንድ . . .»*

አቅምህ በፈቀደ መጠን አምላክህ ይመሠገንበት ዘንድ መብራቱን፣ዕጣኑን፣ ዘይቱን እንድትሰጥ የትሕትና አምላክ ፈቅዶልሃል። ይህን ባትችልና ባታደርግ ደግሞ ፈቃድህን ይቀበልሃል። በአጠቃላይ በአንተ ምክንያት እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ሁኔታ ተመቻችቶልሃል። አሁን ከአንተ የሚጠበቀው በተሰጠህ እድል መጠቀም ነው።

ወንድሜ በስጦታህ በርታ። መልካም ፈቃድህንም አሳድግ። ቅንነት፣ ሰላማዊነት፣ ፍቅር የክርስቲያናዊ ሕይወትህ መገለጫዎች ይሁኑልህ። ከተሰጠህ ላይ ከፍለህ በመስጠት ኑሮህን ከእግዚአብሔር ጋር አድርግ። በበጎ ምግባር እየኖርክ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስህን መንገድ አቅና። ጉዞህን ለሚያደናቅፍ ሌላ ስሜት ሁሉ ዕድል አትስጥ።

የተሰጠህን በመስጠት አምላክህን ደስ እንድታሰኝ እግዚአብሔር ይርዳህ።

*«በፊቴም ባዶ እጃችሁን አትታዩ»* (ዘጸ 23፣15) ዘጸ 34፣20





## ምዕራፍ ፫

## ንስሓ

ሰው ወደ እግዚአብሔር በመመለስ የሚጓዝበት ሌላው የሕይወት መንገድ ንስሓ ነው። በቤተክርስቲያናችን ትልቅ ሥፍራ ከሚሰጣቸው ሰባት ምስጢራት አንዱ የሆነው ይህ ምስጠረ ንስሓ በትክክለኛው መንፈሳዊ መንገድ የሚፈጸም ከሆነ በትክክል /በእርግጠኝነት ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል። ለንስሓ ኑዛዜ ወይም ኃጢአትን ገልጾ ለካህን መንገር ብቻውን ሳይሆን በቂ የሚሆነው በተለየ ሀሳብና በቁርጥ ውሳኔ እግዚአብሔር አምላክን በጸሎት ይቅርታውን በመጠየቅ ከኃጢአት ሸክም መገላገል፣ ዳግም ላለመበደል መሠረት መጣል ያስፈልገዋል። ይህ እንዴት ይቻላል ብለህ የምትጠይቅ ከሆነ አብረን እንቆይ :-

*ተከተለኝ :-*

ንስሓን ፍጹምና ምሉእ የሚያደርጉት ነገሮች ምን ምን ናቸው? ተነሳሒው ከኃጢአት ቀንበር ነጻ ለመውጣት በጉዞ ላይ ያለው ሰው በትክክል ሊፈጽማቸው የሚገቡ መሠረታዊ ነገሮች በንስሓ ውስጥ አሉ።

### 1. <u>ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝ</u>

ለዚህ ምሳሌ ሊሆን የቅዱስ ዳዊትን የንስሓ ዕንባ በመዝሙሩ ላይ ታገኛለህ።

*«አቤቱ እንደቸርነትህ መጠን ማረኝ*
*እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ።*
*ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ*
*ከኃጢአቴም አንጻኝ*
*እኔ መተላለፌን አውቃለሁና*
*ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና።*
*አንተን ብቻ በደልሁ*

*በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፣. . .»* መዝ 50 (51) እንደዚሁ አንተም እግዚአብሔርን ማረኝ ይቅር በለኝ እያልክ ይቅርታን ጠይቅ። አምላካችን ባስተማረን ጸሎት ላይም «እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን. . .» ብለህ ጸልይ ብሎሃል። በኃጢአትህ ምክንያት ሊመጣብህ ካለው ቁጣ እንዲታገስህ ብሎም እንዲምርህ ተማጸነው። *«አቤቱ በቁጣህ አትቅሰፈኝ*
*በመዓትህም አትገሥጸኝ*
*ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ*
*አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ ። . . .»* መዝ 6፣1-2

## 2- ኃጢአትን ለንስሓ አባት /ለካህን መናዘዝ

ካህን የእግዚአብሔርን ምሥጢራት አስፈጻሚ ስለሆነ ኃጢአትህን ንገረው:: ይህንን ቅዱስ ጳውሎስም አስረግጦ ጽፎልሃል:: *«እንዲሁ ሰው እኛን እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን::»* 1ቆሮ 4፥1- አስቀድሞም በነቢዩ ሚልክያስ ያደረው እግዚአብሔር ሲናገር «ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው» ይላል::

ኃጢአትህን ለካህን በምትነግርበት ጊዜ የሚሰማህን ኃፍረት መሸማቀቅ ሁሉ ችለህ የመመለስን ምሥጢር እንዲያስፈጽምልህ ስትጥር እግዚአብሔር ደግሞ ይህን ድርጊትህን እንደ ታላቅ መሥዋእትነት ቆጥሮልህ ኃጢአትህን ሁሉ ይደመስስልሃል:: /ዮሐ 20፥21፥23/ ማቴ 18፥18

ካህኑ ክርስቶስ በሠጠው በዚህ ሥልጣን መሠረት ከኃጢአት እሥራት መፈታትህን ያረጋግጥልሀል:: ሕይወት ለሚሆነው ሥጋና ደሙ እንድትበቃም ያደርግሃል:: (1ቆሮ 11 ፥27)

በሕይወትህ ውስጥ የሚታዩትን ጉድለቶች /መንፈሳዊ ድክመቶች እየተመለከተም እንዴት አሸናፊ መሆን እንደምትችል የሚመክርህ መንፈሳዊ መሪህ ካህን /የንስሓ አባት መሆኑንም አትዘንጋ::

ለካህን ኃጢአትን መናዘዝህ በራሱ የሚያተርፍልህ ነገርም አለው:: ኃጢአትን መልሰህ ስትናገረው ለአንተ ለራስህ ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ ይሰማሃል:: ይህም ዳግም እንዳትመለስበት ታላቅ ትምህርት ይሰጥሀል:: መጽሐፍ ቅዱስም የሚለው ይህንኑ ነው:: (እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ሰው ስለሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች::» (ያዕ 5፥16)

## 3:- <u>ኃጢአትህን ለበደልከው ሰው መናዘዝ</u>

ከኃጢአትህ በንስሓ ተመልሰህ አዲስ ሰው ለመሆን፣ የተስተካከለ መንፈሳዊ ሕይወትን ለመምራት በአንተ የተቀየመ/ የተበደለ ሰው እያዘነብህ እንዳይኖር እንዲሁም እንዳይሰናከልብህ ሁሉን ነገር ልትነግረው ይገባል:: በእርግጥ እንደበደልከው አምነህ ይቅር በለኝ በለው :: የሕይወት ባለቤት፣ የዓለማት ፈጣሪ ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ይህን በተመለከተ ያስተማረውንም ቀጥለህ ተመልከት:: «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፣ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፣ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ:: አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ:: በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ ::» (ማቴ 5፥23-25»





❖ ትናንት በድለህቸው የነበሩ ሠዎችን ዛሬ የምትጠይቃቸው ይቅርታ ነገ ሌሎችን ሠዎችም እንዳትበድል በውስጥህ ያስጠነቅቅሃል::

## <u>4- ኃጢአትን ለራስ መናዘዝ</u>

አንተ ራስህ ለራስህ ያላሳመንከውን በደልህን ለማንም ልትናገረው አትችልም:: እውነተኛው የበደለኝነት ስሜት በውስጥህ ከሌለ ብትናገረውም ከውስጥህ የመነጨ ለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ የለህም:: ኃጢአትን መናዘዝ ከራስ ለራስ የሚነሳ ነው:: ጥፋተኝነቱን ያላመነ ይቅርታ- መጠየቅ ይከብደዋልና በእውነት አምላኬን በድያለሁ፣ ስለእኔ የሞተልኝን ጌታ አስቀይሜዋለሁ ብለህ ከራስህ ጋር ካልታረቅህ በቀር ንስሐ ለአንተ ፍፁም ሊሆን አይችልም::

ብዙውን ጊዜ ከነኃጢአታቸው ሲሞቱ የምታያቸው ሰዎችንም ቢሆን ችግራቸው ምን ነበር? ብለህ ራስህን ብትጠይቅ መልሱ ከራሳቸው ጋር የሚያደርጉት ውስጣዊ ዕርቅ ጠፍቷቸው እንደሆነ መረዳት አይከብድህም:: እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ኃጢአትን እየሠሩ ሳለ እንኳን ምንም ስሕተትእንደማይፈጽሙ የሚያስቡ ናቸው:: ምናልባት እነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ ሚዛናቸው ለራሳቸው ትክክል አይደለም:: ሁሌም የሚቀናቸው ሥራቸውን ማፅደቅ ብቻ ነው:: ጠማማው እኔነታቸው (ego) ኃጢአታቸውን እንደመልካም ተግባር ከሽኖ ያሳያቸዋል:: ስለዚህ እኔ ልክ ነኝ፣ በፍፁም አልተሳሳትኩም፣ ይህን ለማድረግ ብዙ ምክንያት አለኝ . . . የመሳሰሉት መለያቸው ነው:: እነዚህ ሰዎች ንስሐ ምን ያህል እንደሚከብዳቸው ታየህ? በእርግጥ ከራሱ ጋር ላልታረቀ ሰው ንስሐ ከባድ ነው::

ኃጢአት በመልካም መሠል ሥራዎች ውስጥም ተደብቆ ሊኖር ይችላል:: ኃጢአተኞች በሥራቸው እንዲመጻደቁ የሚያደርጋቸውም ይህ ድብብቆሽ ነው:: ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም እንደዚሁ ነበሩ:: ራሳቸውን እንደ ሙሴ ሕግ ጠበቆች፣ የአባቶቻቸው ወራሾች፣ በራሳቸው ለራሳቸው ጻድቆች ሆነው የሚቀርቡ ነበሩ:: ባዶነታቸው የሚገባቸው አይደሉም:: የእውነትን ገደብ የጣሱ ደፋሮችም ነበሩ:: «ሳምራዊ እንደሆንክ ጋኔንም እንዳለብሕ በማለታችን እኛ መልካም እንል የለምን?» ሁሉ በእርሱ የሆነን የእውነት ጌታ ኢየሱስን ይህን እስከ ማለት ያስደፈራቸው ምንድን ነው? ብለህ እኮ ብትጠይቅ በውስጣቸው ያለው የማንነት ዕውቀት መዛባት ነው:: (ዮሐ 8፥48):: በኃጢአታቸው ኮሩበት:: ጌታን ጋኔን አለብህ አሉት:: ራሳቸውን አጸደቁ::

እንግዲህ ወንድሜ በዚህ መንፈስ ውስጥ ንስሐ ምን ያህል ከባድ መሆኑን ዕወቅ :: ስለዚህም አንተ ጉዞህ የተቃና እንዲሆን ከራስህ በመታረቅ ራስህን በማሳመን

ሸሽገህ ከፊሉን ብቻ ብትናዘዝ ልታገኝ የምትችለው ትልቅ ዋጋ እንዳመለጠህና አሁንም ክፉ ነቀርሳ በውስጥህ ተቀብሮ እንደቀረ አትርሳ።

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና አትፍራ (ኢያ 1፤)

የኃጢአቱን ሥርየት ተስፋ አድርጎ ንስሐ ለሚገባ ሰው ንስሐ ያለው ጥቅም እጅግ ብዙ ነው። ከብዙዎችም መካከል የሚከተሉትን ብንመለከት ጠቃሚ ነው።

## 1. የንስሐ መንፈሳዊ ጥቅም:-

ንስሐ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚያመጣው ለውጥ በሌላ በምንም ነገር ሊመጣ የማይችል ነው ። ኃጢአትን በመናዘዝና ተገቢውን የንስሐ ምክር በመፈጸም የሚገኘው ጥቅም በገንዘብ ሊገዛ የማይችል፣ በዓለማዊ ዕውቀት የማይደረስበት፣ ኃይል ጉልበት የማይለውጠው ነው።

በንስሐ ከኃጢአትህ ሸክም ሙሉ ለሙሉ ተገላግለህ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ታገኛለህ። «ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖታችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ። የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ። የሥጋንም ልብ እሠጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ።» (ሕዝ 36፤26)

ውንድሜ ኃጢአትህን በሥጋዊ አካልህ ግላልጠህ ለካህን ስትነግረው መንፈሳዊ አካልህ መታደስን ታገኛለች። ነፍስህ ትነፃለች ትቀደሳለች። ልጅነትህንም ታረጋግጣለህ የመንግሥተ ሰማያት ተስፋህ ጽኑ ይሆናል። በመጨረሻም ሰዓት *«የአባቴ ቡሩካ ወደ እኔ ና»* ይልሃል። (ማቴ 25፤34)

## 2. የንሥሐ ሥነ ልቦናዊ ጥቅም

የሰው ልጅ አዕምሮ በተፈጥሮው የሠራው ክፉ ነገር የሚጸጽተው፣ ቆይቶ የሚቆጨው፣ ተመላልሶ እየታየ እረፍት የሚነሳው ነው። ይህን የመሰለ ሀሳብ በተጫነውና ባስጨነቀው ቁጥር የአዕምሮ (የሕሊና) ሰላም ይፈልጋል። ሁሌም ቢሆን ለሚታመንለት ሰው ችግሮቹን፣ ድክመቶቹን ተናግሮ እፎይ ማለትና መፍትሔ መፈለግ ይመኛል። ካህን ደግሞ ለዚህ የተዘጋጀ ነው። የኃጢአቱን ክብደት ነግሮ ሊያሳቅቀው ሳይሆን መፍትሔ ሊነግረው ነው። ስሕተቱን እያጎላ ተስፋ ሊያስቆርጠው ሳይሆን ሊያጽናናው ነው። ስለዚህ በንስሓ፣ ኃጢአትን ለካህን በመናገር ውስጥ የአዕምሮ ሰላም፣ ከጸጸትና ከቁጭት መገላገል ይገኝበታል። ከንስሓም በኋላ እንዲሁ ከፍተኛ የሕሊና ዕረፍት ስለሚገኝ በቀጣዩ ሕይወት ላይ የመወሰን፣ ኃጢአትና ጽድቅን የመለየት ጥንካሬ ይገኝበታል።

ኃጢአት ያስጨንቃል:- «ከቁጣህ የተነሳ ለሥጋዬ ጤና የለውም ከኃጢአቴም የተነሳ ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም። ኃጢአቴ በራሴ ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና።» (መዝ 37 (38) ፤ 3)





ንስሐ ደግሞ በምንም ሊገኝ የማይችል ሠላም ይሠጣል። «ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት እርሱም ዘንበል አለልኝ ። ጩኸቴንም ሰማኝ ከጥፋት ጉድጓድ ከረግረግም ጭቃ አወጣኝ፣ እግሮቼንም በድንጋይ ላይ አቆማቸው። አረማመዴንም አጸና አዲስ ዝማሬን ለአምላካችን ምሥጋና በአፌ ጨመረ።»

(መዝ 39፤(40)፤1)

## 3. የንስሐ ማህበራዊ ጥቅም

በንስሓ የራሱን (የውስጡን) ሰላም ያረጋገጠ ሰው ከወገኖቹ ጋር ተስማምቶ መኖር አይከብደውም። ለሁሉም እኩል የሆነ ሚዛናዊ አመለካከት ስለሚኖረውም ሰዎች ሁሉ ለእርሱ ጥሩ ናቸው። ከዚህም በላይ እርሱ የበደለው፣ ያስቀየመው ሰው ቢኖር እንኳ በንስሳ ስለታረቀው ማህበራዊ ሕይወቱን የሚበጠብጡ ጉዳዮች አይኖሩም። በሥራው፣ በትምህርቱ፣ በትዳሩ . . . በሁሉም መስክ የተመሠገነ ይሆናል። የቀደመውና ከኃጢአት ጋር የተቆራኘው ስሙ ሲነሳለትና ለታደሰው ስሙ ተስማሚ የሆነ ስም ሲሰጠው ከሕብረተሰቡ ጋር ያለውን ሰላም ያጠናክርለታል።

## 4. የንስሐ አካላዊ ጥቅም

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ሰውነታችን የኃጢአት ውጤት በሆኑ የተለያዩ ነገሮች ሊጎዳ ይችላል። የቤተ ሳይዳው ሕመምተኛ ለዚህ ምሳሌ መሆን ይችላል። (ዮሐ 5፤4)። ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን ከመናዘዝ ጋር ለበሽተኞች የቀንዲልን ምስጢር ያዘጋጀችውም ከዚህ የተነሳ ነው ። በሽተኛው ኃጢአቱን ለካህን ነግሮ የኃጢአቱን ሥርየት በነፍሱ ሲያገኝ፣ በኃጢአቱ ምክንያት የመጣበት አካላዊ ችግርም እንዲሁ የሚታለፍ አይሆንም። ካህናት ወደ እርሱ ሄደው ይጸልዩለታል፣ ከተቀደሰው ዘይትም ቀብተው ይፈውሱ

*«ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች ወደእርሱ ይጥራ፣ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፣ የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል፣ ጌታም ያስነሣዋል። ኃጢአትንም ሰርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል።»* በንስሐ የተያዘ ሕይወት የኃጢአት ፍላፃ አያቆስለውም። » (ያዕ 5፤14)

*«ኃጢአቱን የሚሠውር አይለማም። የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።»* (ምሣ 28 ፤13)

ኃጢአት ከእግዚአብሔር የሚለይ፣ ከዘለዓለም ሕይወት የሚያርቅ መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያጨልም ክፉ በሽታ ነው። ከንስሐም ውጪ ምንም መድኃኒት የለውም። ኃጢአት ይገላል። ያውም የኃጢአት ሞት -የሞት ሞት ነው። ነገር ግን ሁሉንተናህ በእጁ የሆነ እግዚአብሔር ሞትህን አይፈቅድም። በኃጢአት ስትኖር ከእግዚአብሔር ፈቃድና እቅድ ውጪ መኖርን መረጥክ ማለት ነው።

# ምዕራፍ ፱

## ሥጋ ወደሙ

## (የጌታችንን ሥጋና ደም መቀበል)

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን ደህንነት ከምትፈጽማቸው ምሥጢራት አንዱ ቅዱስ ቁርባን ነው። በዚህ ምሥጢር ተረድተው የሕይወትን ምሥጢር ያገኙ ብታል። በዚህ ምሥጢር የእግዚአብሔር ሰዎች የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሳሉ።

ቁርባን ማለት፡- በሱርስት ቋንቋ መባ፣ስጦታ ማለት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙን የሠጠን ከእኛ በሆነ ዋጋ ሳይሆን በእርሱ ቸርነት በጸጋው ስለሆነ ቁርባን የሚለው ቃል ለሥጋ ወደሙ ሊሰጠው ችሏል። ይህ ምስጢር ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መጓዝ ከሚችሉባቸው መንገዶች ዋነኛው ነው።

*«ከሰማይ የወረደ ኅብስት እኔ ነኝ። ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው»* (ዮሐ 6፡32-36)

የዘለዓለም አምላክ ክርስቶስ *«ሥጋዬን ብሉ ፣ደሜንም ጠጡ»* ሲለን ለሥጋዊ ጥቅም ላይ ብቻ በተወሰነ መልኩ አይደለም።

### ❖ ሥጋ ወደሙ የነፍሥ ምግብ ነው

ለዘለዓለም ሕይወት፣ ለመንፈሳዊ ዕድገት ይሆነን ዘንድ ሞታችንን ሞቶ ሥጋውና ደሙን የሠጠን ጌታ *«የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነው»* ብሏል። (ዮሐ 6፡33) ይህ የሕይወት እንጀራ *«እንካችሁ»* ብሎ የሠጠን ሥጋውና ደሙ ነው። በእርሱ አምኖ የአባቱን ፈቃድ ፈጽሞ ለተቀበለው የዘለዓለም ሕይወትን ያወርሳል

*«ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ። ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል። እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።»* (ዮሐ 6፡50)

«አባታችን ሆይ» እያልክ በምትጸልይበት ጊዜ ሁሉ *«የእለት እንጀራችንን በየዕለቱ ሥጠን»* እያልክ ትጸልያለህ። ነገር ግን ልብ ብለህ አስተውለኸዋል? የምትጠይቀው እንጀራ የነፍስህንም ጭምር እንጂ ለሥጋህ ብቻ የሚሆነውን መሆን የለበትም። የነፍስ ምግብ ደግሞ የጌታችን ሥጋና ደም መሆኑን እየተነጋገርን ነው። አሁን አንተ ወደ እግዚአብሔር በምታደርገው ጉዞ ውስጥ ወሳኙ የአንተ ዝግጁ ሆኖ መቅረብ እንጂ የነፍስህ ምግብ ተዘጋጅቶልሃል።





ከዚህ በላይ ምን ትናፍቃህ? ከዚህ የሚበልጥ ፍቅርስ አለ ብለህ ታስባለህ? በፍፁም! ስለዚህ ፍቅሩን በፍቅር መልስ። የሠጠህን ተቀበል። ጌታህ ካንተ ጋር ለመኖር በርህን ያንኳኳል። የልብህ መዝጊያዎች ይከፈቱ። የዘለዓለም አምላክ ከአንተ ጋር ይኑር።

### ❖ ከአምላክ ጋር የመኖር ምሥጢር ሥጋ ወደሙ ነው

*«በእኔ ኑሩ፣ እኔም በእናንተ. . .»* (ዮሐ 15፡4)

አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ በልምላሜ ፣ በሕይወት መቆየት እንዲችል ከግንዱ የሚደርሰው ምግብ መቋረጥ የለበትም። ከግንድ የተለየ ቅርንጫፍ ይጠወልጋል፣ ይደርቃል። የእኛም ከጌታችን የተለየ ሕይወት እንደዚሁ ነው ። እኛ ቅርንጫፎች ስንሆን ሕይወት የምናገኝበት ግንዳችን እርሱ ነው። ከርሱ ከተለየን መንፈሳዊ ሕይወታችን ይጠወልጋል፣ ይደርቃል። ለዚህ ነው ለእኛ አሳቢ የሆነው ጌታ «በእኔ ኑሩ» ሥጋዬን እየበላችሁ፣ደሜን እየጠጣችሁ ሕይወታችሁን እያስመሰማችሁ አብረን እንኑር ያለን።

ወንድሜ የአንተ የመኖር ምሥጢር ምንድን ነው? በእርግጥ ሌላ እንደሌለ አውቃለሁ። ከአምላክዋ የተለየች ነፍስ የሞተች ናት ። ስለዚህ በዚህ ሕያው ቃል መሠረት የኃጢአት ሸክምህን በንስሐ አስወግደህ ሥጋና ደሙን ብትቀበል ኑሮህ ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን አረጋገጥክ ማለት ነው። ዘወትር ወደቅድስት ቤተ ክርስቲያን ገብተህ በምትጸልይ፣ በምትቀድስና በምታስቀድስበት ጊዜ ሁሉ ካህኑ ስለዚህ ምሥጢር የሚናገራቸውን ቃላት በተመስጦ፣ በአንክሮ ተከታተል።

«እምናለሁ፣ አምናለሁ፣ እምናለሁ፣ መለኮቱ ከሰውነቱ አንዲት ሰዓት እንኳ እንደ ዐይን ቅጽበትም እንዳልተለየም እታመናለሁ ስለእኛ ሰጠው እንጂ። ለሕይወትና ለመድኃኒት ለኃጢአትም ማስተሥረያ ሊሆን አምነው ለሚቀበሉ ሰዎች ስለእኛ አሣልፎ ሰጠው እንጂ።» (ቅዳሴ)

ይህ ካህኑ የሚናገረው ቃል ነው። አንተም በእርግጠኝነት ለመዳንህ አምነህ የምትቀበለው፣ ምንም አቻ የሌለው የፍቅር ስጦታ መሆኑን አምነህ ተቀበል። ማን ነው ከእኛ መካከል እነዚህን ሦሥት ነገሮች ማለትም የዘለዓለም ሕይወትን፣ መድኃኒትን፣ የኃጢአት ሥርየትን በሌላ መንገድ ሊያገኝ የሚችል? ልብ በል፡- ጌታችን የሚሰጠን ሁሉ ዓለም ልትሰጠን የማትችለውን ነው። ከኃጢአታችን በንስሐ ያገኘነውን ነፃነትና አዲስ ሕይወት ከሥጋና ከደሙ ጋር እንቀበላለን። ምክንያቱም «ነገር ሁሉ በደም ይነፃል። ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብ 9፡22) ለእኛም ከሥጋ ወደሙ ውጪ መዳንም ሥርየትም የለንም። ዘለዓለማዊው መሥዋዕት ጌታችን

አይኖረውም:: የምትችለውን ሁሉ አድርገህ፣ አምላክህም የቸርነቱን እንዲያደርግልህ በመጠየቅ ቅረብ::

ለዚህ ምን ያስፈልግሃል?

## 1. የተሠበረ ልብ

❖ ትሕትና የመንፈሳዊነት ትክክለኛው ምልክት ነው :: ምን ጊዜም ቢሆን ላንተ ያልተገባውን እግዚአብሔር በቸርነቱ እንደሠጠህ አስብ ::

«የሁሉን ልብ የምታውቅ በቅዱሳን መካከል የምትኖር ቅዱስ አምላክ ሆይ ኃጢአት የሌለብህ አንተ ብቻ ነህ፣ ኃጢአትን የምታስተሠርይ ይቅር ባይም አንተ ነህ:: ጌታ ሆይ ለዚህ የተቀደሠ ምስጢር አለመገባቴን አውቃለሁ:: በክብርህ ፊት ልቀርብና አፌን እከፍት ዘንድ አልደፍርም:: ነገር ግን በይቅርታህ ብዛት ጸጋህን ሰጥተህ ለክብርህ የተገባሁ አድርገኝ፣ መተላለፌን ሁሉ ይቅር በለኝ» እያልክ ከካህኑ ጋር ጸልይ::

አንተ ለአምላክህ የተሰበረ ልብህን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብ፣ አምላክህም ስለአንተ የሠዋውን ሥጋውን ያፈሰሰውን ደሙን የዘለዓለም ሕይወት እንዲሆንህ ይሰጥሃል::

## 2- ንስሓ

ለመሆኑ ከዚህ በላይ የተገባህ ሊያደርግህ የሚችል ሌላ መሥፈርት ያለ ይመስልህ ይሆን? የለም:: ልብ በል! አምላክህ ይህን ተናግሯል:: *«የተገባቸውም ስለሆኑ ነጭ ልብስ ለብሠው ከእኔ ጋር ይሔዳሉ::»* (ራዕ 3፣5) ይህን ነጭ ልብስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 22 ላይ ከተጻፈው ጋር አዛምደህ ተረዳው:: ነጭ ልብስ በወንጌሉ የሠርግ ልብስ በሚል የተገለጸው ለሠርጉ ቤት (ለመንግስተ ሰማያት) የሚሆን ቅድመ ሁኔታ ንስሓ ነው፡ በነጭ ልብስ እድፍ ጉድፍ ገንኖ እንደሚታይ ኃጢአትን በንስሓ ሳያጠሩ ሥጋው ደሙን መቀበልም እንደዚሁ ነው:: ስለዚህ በቅድስቲቱ ቤተ ክርስቲያን ቀና ሥርዓት መሠረት አንተ ይቅርታን ጠይቅ:: አምላክህ ይቅር ሊልህ የታመነ ነው:: በተጨማሪ ስለንስሐ (ምዕራፍ ስምንትን) ብትመለከት ላንተ ጠቃሚ ነው::

ንስሐ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ከጌታችን የትሕትና ስራ መነሻነት መረዳት ትችላለህ:: ሕብሥቱን ሥጋዬ ነው ፣ ወይኑን ደሜ ነው ብሎ ለሐዋርያት ከመሥጠቱ በፊት እግራቸውን አጠባቸው:: እንዲህም አላቸው:: «የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም:: ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው:: እናንተም ንጹሐን ናችሁ፡- ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም::» (ዮሐ 13፣10):: የተለየውን ይሁዳን ይመለከታል:: ንጽህ ባለመሆኑ ምክንያት ሥጋውን





ደሙን አልሠጠውም:: ዛሬስ «ንጹሕ የሆነ ከሥጋው፣ ከደሙ ይቀበል ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል» በሚል በካሕኑ ሲታወጅ ትሰማ የለም! ነገር ግን ፍፁም ንጹሕ መሆንን በመጠበቅ እንዳልሆነ ልብ በል::

ይሁን እንጂ ከቂም ከበቀል ከተንኮል ከመሳሰሉት ሰይጣናዊ ተግባራት በንስሓ መጠበቅ ለሥጋና ለደሙ ቅድመ ሁኔታ ነው::

## 3-አካላዊ ንጽሕና

ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ሰውነታችን፣ ልብሶቻችን ንጹሐን መሆን አለባቸው:: እንደዚሁም ጾምን መጾም ያስፈልገናል:: በብሉይ ኪዳን ዘመን እሥራኤል ትእዛዝ ለመቀበል ያደረጉትን ዝግጅት አንተ የጌታን ሥጋ ለመብላት ደሙን ለመጠጣትና ፍፁም የደኅንነት ባለቤት ለመሆን ከምታደርገው ዝግጅት ጋር እያነጻጸርክ ምን ያህል የአንተ እንደሚከብር አስተውለው:: *«ሰው በልቶት የማይሞት እውነተኛ የሕይወት ምግብ ነው»::* (ዮሐ 6)

ራሱን ለዚህ ታላቅ ዕድል እያዘጋጀ ያለ ማንም ሰው በአካልም በመንፈስም ንጹሕ መሆን አለበት:: ከዚሁ ጋር ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መታቀብ፣ ለሴቶች ወርኃዊ ሁኔታዎችን ማሳለፍ፣ የሚቆስሉ፣ ጉዳት የደረሰባቸው የአካል ክፍሎች እስከሚጠገኑ መጠበቅና የመሳሰሉት ይገኛሉ:: በተጨማሪም በተፈጥሮ ያሉ ውስጣዊ የሆኑ ሥጋዊ የስሜት ግፊቶችን ለመቆጣጠር ጾም አስፈላጊ ነው :: በቤተ ክርስቲያናችን ሕያው በሆነው ትውፊት እየተጠቀምንበት እንዳለው ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ለ15 ሰዓታት ከምግብና ከመጠጥ መከልከል ከላይ ለጠቀስናቸው ጥንቃቄዎችና ራስን ለመግዛት ጠቃሚ ነው::

ጾም ሥጋዊም መንፈሳዊም ጠቀሜታ ያለው ሀብት ነው:: በእያንዳንዱ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ጸጋዎች እናገኝ ዘንድ ይረዳናል:: ነገር ግን እነዚህ ቅድመ ዝግጅቶች በድንገት ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን፣ የጤና ችግር የገጠማቸውን፣ አቅማቸው የማይፈቅድ ሕፃናትን አይመለከትም::

## 4-የሕሊና ንጽሕና

ሕሊና በራሱ በክፉና በበጎ ነገር መካከል የሚፈርድ ዳኛ ነው:: ለክፉዎች የእግር እሳት፣ በምግባረ ሰናይ ለሚኖሩ ዕፎይታ የሚሆነው ሕሊና ራሱ ነው:: ስለዚህ ሕይወት የሆነውን የጌታችንን ሥጋና ደም ለመቀበል ስንዘጋጅ በሕሊናችን ውስጥ የቀረ የሚጸጽት የሚያብገነግን ነገር መኖር የለበትም:: አሁንም በድጋሚ ይህን ንጽሕና ሊሰጠን የሚቻለው ንስሐ ነው:: አንተም ከነገርህ ሁሉ በፊት የበደልከውን ሰው መካስ፣ የቀማኸውን መመለስ፣ የተጣላኸውን መታረቅ፣ ቅድሚያ የምትሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት:: *«. . . አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ::. . .»* (ማቴ 5-

23) ፍጹም የሆነ የሕሊና ሰላም የሚገኘውከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን ለማውረድ ቅድሚያ ከወንድሞቻችን ጋር ያለውን ችግር ሁሉ ማስወገድም አስፈላጊና ቸል የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ *«ከእግዚአብሔር ጋርታረቁ . . .»* (2 ቆሮ 5፥20) ማንንም ሰው ብትንቅ፣ ማንንም ሰው ብትጠላ የናቅኸውና የጠላኸው ከሰውየው ባሻገር እግዚአብሔርን ነው፡፡ *«ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ ዕወቁ፡፡»* (ዮሐ 15 ፥ 18)

በአጠቃላይ የሕሊና ሰላም ከጠላቶችህ ጭምር በመታረቅ ብሎም በመውደድ ነው፡፡ «በሠማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ. . .» (ማቴ 5፥43-46)

እነዚህን እና ሌሎችንም ቅድመ ሁኔታዎች ማድረግ የሚገባው ሰው ሳያደርገው *ሥጋ* ወደሙን ቢቀበልስ?

*መጽ*ሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን *መ*ልስ እለው፡፡

«ሰው ግን ራሱን ይፈትን፣ እንዲሁም ከእንጀራው (ከ*ሥጋ*ው) ይብላ፡፡ ከጽዋውም (ከደሙም) ይጠጣ፡ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን *ሥጋ* ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና ፡፡ ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፡፡ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል፡፡ ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፡፡. . .»(1 ቆሮ 11፥28-34) ትሕትና እጅግ አስፈላጊና ዋናው የክርስትና መለያ እንደመሆኑ መጠን አንተም *ሥጋ* ወደሙን ለመቀበል በምታደርገው ዝግጅት ውስጥ ትሕትናን ገንዘብ ማድረግ ይጠበቅብሃል፡፡ «ጌታዬ ሆይ ይህ ሁሉ ክብር ለእኔ የተገባ ሆኖ ሳይሆን ለመዳን የሚያስፈልገኝ ስለሆነ ነው፡፡ ከእኔ ብቃትም ሳይሆን ከአንተ ምህረትና ቸርነት፣ ለሰው ልጆች ካለህ ፍቅር የተነሳ ነው፡፡ ቅድስና የአንተ ነው፡፡ እኔንም ወደ ጽድቅ መንገድ የምትመራኝ መንገድህን ያሳየኸኝ አንተ ነህ፡፡ ከእኔ የሆነ ምንም ነገር የለም፡፡ የምቀበለው *ሥጋ*ና ደምህ ለሕይወትና ለመድኃኒት እንዲሆነኝ እንጂ በኃጢአቴ እንዳይፈርድብኝ በደሌን ሁሉ ይቅር በለኝ . . .» እያልክ በትሕትናና በተሠበረ ልብ ቅረብ ፡፡

ከክብር ሁሉ በላይ ክብር የሚገባውን ቅዱስ *ሥጋ*ውንና ክቡር ደሙን ከተቀበልክም በኋላ ኃጢአትን ዳግም ላለማድረግ ወስን፡፡ ለዚህ ደግሞ ቀድሞ ያደረግኸው ዝግጅትና ኋላ የምታደርገው ጥንቃቄ ከፍተኛ እገዛ ያደርጉልሃል፡፡ በ*ሥጋ*ና በደሙ ተወስነህ የምትኖረው ሕይወትም ከኃጢአት ጋር የተለያየህበት ሕይወት ይሆንሃል፡፡ በብዙ መንፈሳዊ ተግባራትም እንድታድግ ይረዳሃል፡፡ ለምሳሌ ጾምን፣ የ*ሥጋ* ንጽሕናን፣ ንሥሐን፣ ሰላማዊ ሕይወትን፣ ትሕትናን፣ ጸሎትን





በሕይወት እንድትኖራቸው ያደርግሃል፡፡ እነዚህም ከመቀበልህ በፊት ወይም ስትቀበል አልያም ከተቀበልክ በኋላ ብቻ ሳይሆን በዘመንህ ሙሉ የምታከናውናቸው ይሁኑ፡፡

- ቅዱሱን በተቀበልክበት ለውነትህ ርኩሰትን አትቀበል፡፡
- ሕይወትን በተቀበልክበት አፍህ ክፋትን አትናገር፡፡

በተቀደሰው ተቀድሰሃልና ለቅድስና ከማይመቹ ተግባራት ሁሉ ተቆጠብ፡፡ አሁን እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው አንተም ከእግዚአብሔር ጋር ነህ፡፡ *«ከጌታህ ፍቅር የሚለይህ አይኑር፡፡»* (ሮሜ 8፥35)

# ምዕራፍ ፲

## አገልግሎት

አገልግሎት ለእግዚአብሔር ወይም ለሰው የሚሠሩት ሥራ ማለት ነው። አገልግሎት ለእውነተኛ ክርስትና ምስክር የሚሆን፣ ከጥሩ ሕይወት የሚፈልቅ ምግባር ነው። አገልግሎት አምልኮተ እግዚአብሔርን መግለጫ ነው።

አገልግሎት ለጥቂቶች ብቻ የተሠጠ ርስት ሳይሆን ክርስቲያን ሁሉ ግዴታውንም ጥቅሙንም መጋራት የሚችለው ሀብት ነው። የሚሠራውን በማወቅ በአግባቡ አምላኩን ለሚያገለግል ሰው አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ የሕይወት መንገድ ነው። አገልግሎት በእግዚአብሔር ከሚያምኑ ክርስትናን ከተረዱ ሁሉ የሚጠበቅ በጎ ምግባር ነው። አገልግሎት ወጣት-አረጋዊ፣ ያገባ-ያላገባ ብሎ የማይመርጥ ሕይወት ነው። ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን ከአገልጋይነት በፊት ስለአገልግሎት በቂ ዕውቀት ያስፈልጋል። ባለማወቅ ወደዚህ የተመረጠና የተቀደሰ ሕይወት ገብተው የሚጎዱበትም ስለማይጠፉ ጥንቃቄ ያሻዋል።

«እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሰራው ኃጢአት ነው።» (ያዕ 4፥17) ኃጢአት ከበጎ ነገር በተቃራኒ መሥራት ብቻ አይደለም። በጎውን አውቆ አለመሥራትም ኃጢአት ነው። መንፈሳዊ ሰው እንደተፈጠረበት የእግዚአብሔር አርአያ ዘወትር በጎውን ብቻ የሚሠራ እና በነገር ሁሉ ክርስቶስን የሚመስለው ነው። *«እርሱም መልካም እያደረገ፣ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና።»* (ሐዋ 10፥38)

አንተስ እንዴት ነህ? ሥራህ ከየትኛው ወገን ነው?

❖ *መንፈሳዊ ሰው ለራሱ ብቻ የሚኖር አይደለም።*

«ለራሱ ብቻ የሚኖር ሰው አልኖረም ማለት ነው» የሚል አባባል አለ። ስለዚህ አንተም እንደዚህ ከሆንክ የተሸፈንክበትን ሼል ሰብረህ ውጣና ወገኖችህን አግኛቸው። ፍቅርህ ለሁሉም በሁሉም እንዲሆን «የእኔነት» አጥርን አልፈህ ውጣ። እግዚአብሔር በአንተ መንገድ ለላካቸው ሁሉ ጥሩ መሆን፣ መልካምን ማድረግ የሕይወትህ መመሪያ ይሁን። በፍቅር መኖርን ስትለምደው ልብህ ለሁሉ አሳቢ ሲሆን የአገልግሎትህም አድማስ እንዲሁ ይሰፋል።

አገልግሎት በባሕርዩ ለእግዚአብሔርና ለሰው ልጆች በልብ ውስጥ የታመቀውን ፍቅር ገልጦ የማሳያ መንገድ ነው። በአጭሩ አገልግሎት የፍቅር መንገድ ነው። እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ እንድትወድ ታዞሃል። (ዘዳ 6፥5) በሐዲስ ኪዳንም በተደጋጋሚ





ተነግሮሃል። (ማቴ 22፥37፥39) ፍቅር ሀሳባዊ የሆነ ነገር ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስም *«ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ፣ በቃልና በአንደበት አንዋደድ»* ይላል (1ዮሐ3፥18)

❖ ፍቅር በተግባር የሚታየው በአገልግሎት ነው። እግዚአብሔርን ከወደድከው ፈቃዱን ለሕዝቡ ሁሉ በመግለጽና በማሳወቅ ውደደው። ሰዎችንም የምትወድ ከሆንክ የሚድኑበትን ስትነግራቸው በቃለ እግዚአብሔር ስታገለግላቸው ነው።

እያንዳንዱ ሰው ለሌላው በሚያደርገው ነገር ውስጥ ፍቅር ትርጉም ያገኛል። ፍቅር መስዋዕትነትን ይጠይቃል። አገልግሎትም መሥዋዕትነት ነው። በአገልግሎትህ ገደብ አይኑር። ደሃ ሃብታም፣ ትንሽ-ትልቅ፣ . . . አትበል። ለሚያስፈልገው ሁሉ ተናገር። ዝም አትበል። እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲድንለት ይፈልጋልና።

### የአገልግሎት ዓይነቶች

እጅግ ብዙ የአገልግሎት ዓይነቶች ቢኖሩም ጎልተው የሚታዩት መንፈሳዊና ማሕበራዊ የሆኑት ናቸው።

### መንፈሳዊ አገልግሎት

ስለመንፈሳዊ አገልግሎት ያዕቆብ ይህን የመሠለ ቃል ተናግሮለታል። *«ወንድሞቼ ሆይ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ»* (ያዕ 5፥20)

ቅዱስ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ «ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፣ በእነዚህም ጽና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።» (1ጢሞ 4፥16) ነፍስን ማዳን የሚመለከተው በቀጥታ መንፈሳዊ አገልግሎትን ነው። ምክንያቱም የዚህ አገልግሎት ምንጩ፣ ትጥቁ፣ ምግቡ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

❖ አገልግሎት ማህበራዊ መልክም አለው።

### ማህበራዊ አገልግሎት

በመጨረሻው ቀን ጌታችን የሚናገራቸው ቃላትም ይህንን አገልግሎት የሚያንጸባርቁ ናቸው። «ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና። ተምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።» (ማቴ 25-35-40)

*« . . . እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት።»*

በማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም በጎ ተግባር ክርስቶስን ለማገልገል እንደተደረገ ነው። ወደ መንፈሳዊነትም የሚመራ ብዙ አቅጣጫ አለው *«ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር ዘንድ ይህ ነው ። ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፣ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው ።»* (ያዕ 1 ፣27)

በሰዎች መካከል ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም እኩል የሚሠጥ አገልግሎትን ካየን ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃም መሻገር እንችላለን ። ድንበር ሳይገድባቸው፣ ዘር ቀለም ሳይለዩ በደረሱበት ቦታ ሁሉ ለሰው ልጆች በፍቅር እርዳታ የሚያደርጉ በርካታ ድርጅቶች አሉ ። ከእነዚህም መካከል የዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማህበር፣ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ተቋማት፣ ሰዎች ለሰዎች የእርዳታ ድርጅት . . . የመሳሰሉት ይገኙበታል። የተፈጥሮ አደጋና፣ ሰው ሰራሽ እልቂት ሳያስፈራቸው ሰውን ለመርዳት ሲሯሯጡ ስታይ አንዳች የሰብአዊነት ስሜት በውስጥህ ያጭርብሃል። ምግብ ውሃ አጥተው በሞት አፋፍ ለሚገኙ ወገኖች ፈጥነው ሲደርሱ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው አገልግሎት ምን ያህል ሠፊ እንደሆነ ታስባለህ። ይህን ሁሉ ለማድረግ የመረጡት፣ ይህን ለሕይወት አስጊ የሆነ የአገልግሎት መስክ የመረጡት ለምን ይመስልሃል? ትክክለኛው የሰብአዊነት ስሜት እየተሰማቸው ፣ ከውስጥ እየገፋቸው ነው።

❖ በእርግጥ እነዚህን የመሳሰሉት ድርጅቶች ከቤተክርስቲያን ጋር ግንኙነት የላቸውም፣ ታዲያ እንዴት ለእኛ ሀሳብ ተስማሚ ሆነ?

ምናልባት የአንተም አዕምሮ ይህንኑ ጥያቄ ያነሳ ይሆናል። ነገር ግን በተግባር ተመሳሳይ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። አንተ ራስህ ይህን መሰሉን ተግባር እንድታከናውንለት እግዚአብሔር ጠርቶሃል። በምሳሌም መስሎ አስተምሮሃል። *«ደጉ ሣምራዊ»*። በወንን የተነጣጠሉትን፣ ተራርቀው የሚኖሩትን ያቀራረበ የፍቅር ተግባር በፈጸመው ሰው ምሳሌ አሳይቶሃል። በእርግጥም ፍቅር ሰውን ከሰው አይለይም። *(ሉቃ 10፣30-37)*

ማንም ሠው ቢሆን ክርስትናን የተቀበለ ሆኖ ሳለ «እኔ ለአገልግሎት አልተጠራሁም» ማለት የለበትም። ይህ ሰው ለፍቅርስ አልተጠራሁም ማለት ይችላል? ፍቅር በአገልግሎት እንደሚገለጽ ደግሞ ቀደም ሲል አይተናል። ነገር ግን አገልግሎትህን ቤተ ክርስቲያን ማወቅ አለባት። ለሁሉ የተሰጠው ጸጋ እንደየአቅሙና እንደየችሎታው የተለያየ ነው ። ሰው ሁሉ ለመስበክ አልተጠራም። እንደ አገልግሎት ሠፊነት ጥሪውም ብዙ ዓይነት ነው። *«ካልተላኩ እንዴት ይሠብካሉ? ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም»* (ሮሜ 10፣15)





እንግዲያውስ አንተም የተሰጠህን ጸጋ ለይና በቤተክርስቲያን አማካይነት ወደ አገልግሎት ተሠማራ። እግዚአብሔር ምንም የማይችል ሰው ፈጥሮ አያውቅምና እንደማትችል አታስብ። ለአንተ የተሰጠ አንድ ጸጋ አለ። የአገልግሎት ፍቅር ያለው፣ ጸጋውን የለየና ቤተ ክርስቲያን ያሰማራችው ሰው ለአገልግሎት ሥፍራ አይመርጥም። ቤቱ፣ ሠፈሩ፣ የሥራ ቦታው፣ ትምህርት ቤቱ፣ በአጠቃላይ ሁሉም ቦታ የአገልግሎት መድረኩ ነው። ለሚጠፉት መዳንን ይሰብካል፣ ሕግ ለሚጥሱ የእግዚአብሔርን ሕግ አብርቶ ያሳያል፣ የተቸገረን ይረዳል፣ የታመመን ይጠይቃል . .የቻለውን ሁሉ ያደርጋል። በአጠቃላይ በማንኛውም ሰዓትና ቦታ ያገኘው ሁሉ ከእርሱ አንድ ነገር ይቀበላል።

## የአገልግሎት መንፈሳዊ ፋይዳ

### ❖ አገልግሎት የአገልጋይን መንፈሳዊ ሕይወት ያጠነክራል

የአገልጋዩ መንፈሳዊነት ደግሞ አገልግሎቱን ያሠምርለታል። በአገልግሎት ትሰጣለህ፣ ትቀበላለህ። ለዚህ ነው አገልግሎትን ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ መንገድ አድርገን እያየን ያለነው። ለተገልጋዮችህ ፍቅርህን ከልብህ ስትሰጣቸው እነርሱ ደግሞ ከአገልግሎት ለሚገኘው መንፈሳዊ እርካታ መንስዔ ይሆኑሃል። በአገልግሎት የምታገኘው ከሰጠኸው በላይ ነው። ያዘነውን ስታፅናና፣ ለተቸገረው መፍትሔ ስትሰጥ፣ የሕይወትን መንገድ ስትመራ በመንፈስ የምታደርገው ሐሴት ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ ነው።

### ❖ አገልግሎት የሥነ ምግባር ትምህርት ቤት ነው

በዚህ ሕይወት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መሥራት ለአንተ ትልቅ ክብር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የአገልግሎት ሕይወቱን እንዴት እንደገለጸው ተመልከት። «ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነን» (1 ቆሮ 3፣9)። በአገልግሎት ውስጥ አንተ ከእግዚአብሔር ጋር ስትሠራ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሠራል። በዚህም ብዙ ብዙ ድንቅ ነገሮችን ታያለህ። በአስቸጋሪ ጉዳዮች ሁሉ እየገባ መፍትሔ ሲሰጥ ታገኘዋለህ። ሰውና እግዚአብሔርን ለማገልገል ያልተነሱ ሰዎች እድገታቸውን በራሳቸው የሚያቀጭጩ ምስኪኖች ናቸው ። ያለአገልግሎት የመንፈስ ፍሬዎች ሊገኙ አይችሉም። ከአገልግሎት ፍቅርን፣ትሕትናን መማር ይቻላል።

### አገልግሎት የጸሎት ትምህርት ቤት ነው

ብዙ አገልግሎት በሠጠህ ቁጥር የእግዚአብሔርን ርዳታ መፈለግህ ይጨምራል። በዚህ ጊዜ ያለህ አማራጭ መጸለይ ነው። ችግሮች ባይታዩህ እንኳን አገልግሎትህ እንዲባረክልህና፣ እግዚአብሔር ብቻህን እንዳይተውህ ትጸልያለህ። አገልግሎትህ የልምድ እንዳይሆንብህና መንፈሳዊነቱን

## ማጠቃለያ

መንፈሳዊ ሕይወት ከቁሳዊና ሥጋዊ አስተሳሰብ የመለየትና ከእግዚአብሔር ጋር የመሆን ምሥጢር ነው። ኃጢአት ደግሞ ይህን ሕይወት የሚያንሳቁል ክፉ በሽታ ነው። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ያለያያል፣ የከበረንን ጸጋ ዋጋ እንዳይኖረው ያደርጋል። የኃጢአት ጉዳት መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን፣ ሥነልቡናዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊም ነው።

በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ የተመለከትናቸው ነጥቦች ይህን ሁሉ መሠናክል አልፈን ወደ እግዚአብሔር የምንጓዝባቸው ምሥጢራት ናቸው። በእነዚህ የታገዘ ክርስቲያን በጥበብና በእውቀት ያድጋል፤ ኃጢአት ያሰናከለበትን ነገር ሁሉ ያስተካክላል። የእግዘአብሔርን ጥሪም ይፈጽማል።

«ወደ እኔ ኑ» (ማቴ 11፣ 28) በሚለው ቃል መሠረት በተዘጋጁልን መንገዶች ወደ እግዚአብሔር እንጓዝ ። ወደእርሱ የተጓዘውን የማያሳፍረው ጌታችን የጉዟችን ፍፃሜ የሆነውን የማያስቆጭ ዋጋ ይሰጠናል። አሁንም በዚህ ላይ ባለን ጽኑ እምነት እንዝበርታ። በፊታችን ወዳለው የዘለዓለም ተስፋ እናትና እንጂ ወደኋላ እንመለስ (ዕብ12፣1 )

አንተም ከዚህ በላይ የተቀመጡልህን ማለትም በስድስቱ ምዕራፎች የቀረቡልህን መንገዶች ለማወቅ ሳይሆን ለሕይወት የምትጠቀምባቸው መሆን አለብህ። ዕውቀት ብቻውን ያስታብያል። ነገር ግን በፍቅር የምታደርገው ይህ ሁሉ መንፈሳዊ ልምምድ ያጸናሃል፣ ያበረታሃል። ሁሉን እያደረግህ በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ በራስህ ኃይል እንዳልሆነ እመን።

በሁሉም ለሁሉም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይርዳን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ጠንካራ እምነት ሊመጣ የሚችለው የእምነት ጀግኖች አባቶቻችን የሠሩትን አብነት በማድረግ ነው። እስከ ሞት ድረስ ለሃይማኖት የታመኑ ሲሆኑ፣ በፆም በፀሎት ተወስነው ሲኖሩ፣ የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ በትዕግስትና በደስታ ሲቀበሉ ስናነብ የምናገኘው እጅግ ብዙ ነው። ባላቸው ኃይል እና እውቀት ሁሉ ቤተክርስቲያንን ጠብቀዋል። በዚህ ምክንያት ለሚመጣባቸውም ምንም አይነት መከራ ፅኑዎች ሆነው በግዞትና በእስር ቤት ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ኖረዋል። ቤት አልባ ሆነው ማረፊያ እንዳጡ በስደት በየሀገሩ ተንከራተዋል . . .

“ለረጅም ጊዜያት ፀንተህ በመታገስ ለፍፃሜ የማታደርሰው እቅድ ሁሉ ፍሬ ቢስ ነው።” ማር ይስሐቅ

ከመጽሐፉ የተወሰደ

አስተያየት ለመስጠት
በስልክ ቁጥር 0911 88 42 58
ይደውሉ።

አከፋፋይ፡ 0911 64 77 26

Cover Design:- Yohanane Printing & Advertising
Mob. 0912 09 22 28/ 0912 72 93 72

ዋጋ 20.00 ብ

ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ